አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐግብር

# የዛይ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ይዘት ትንተና

በ

ዮናስ ወልዴ

2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የዛይ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ይዘት ትንተና

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐግብር

ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ሰላማዊት መካ

በ

ዮናስ ወልዴ

2005 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐግብር

# የዛይ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ይዘት ትንተና

በ

ዮናስ ወልዴ

2005 ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

| አማካሪ | ፊርማ |
| --- | --- |
| ______________ | ______________ |

| ፈታኝ | ፊርማ |
| --- | --- |
| የውስጥ ______________ | ______________ |
| የውጭ ______________ | ______________ |

# ምስጋና

ይህ ጥናታዊ ጽሁፉ እስኪጠናቀቅ ድረስ በማረምና ገንቢ አስተያየት በመስጠት በቅንነት ለረዱኝ አማካሪዬ ለወ/ሮ ሰላማዊት መካ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ለጥናቱ የሚጠቅሙኝን መረጃዎች ስትሰጡኝ ለነበራችሁ መረጃ አቀባዮቼ እንዲሁም የደብረ ጽዮን ነዋሪዎች ላደረጋችሁልኝ ቅን ትብብር ሁሉ በጣም አመሰግናለሁ። በተለይ መምሬ ገ/መስቀል ማረፊያ ቤት መስጠትዎ ሳያንስዎ ዳገት ቁልቁለት ሳይሉ ከመንደር መንደር አብረውኝ የተንከራተቱን መቼም አልረሳውም። እግዜር ውለታዎን ይክፈልልኝ።

ይህን ጥናት ማከናወን እችል ዘንድ የገንዘብ ድጋፍ ያደረገልኝን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን አመሰግናለሁ። ግማሽ ቀን እየሰራሁ እንድማር የፈቀደልኝን የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጽ/ቤት እንዲሁም የስራ ባልደረቦቼ ስታደርጉልኝ ለነበረው ትብብር ሁሉ በጣም አመሰግናለሁ።

ውድ ቤተሰቦቼ ምን ብዬ እንደማመሰግናችሁ እንጃ ብቻ ግን የማያልቀውን ፍቅራችሁን ሰጥታችሁ እዚህ ስላደረሳችሁኝ አመሰግናለሁ። በተለይ እህቴ አስናቀች ወልዴ ለህይወቴ መሳካት ቀዳሚውን ስፍራ ትይዣለሽና ሁሌም አመሰግንሻለሁ። ውድ ጓደኞቼ የስንታችሁን ስም ጠርቼ ላመስግናችሁ ይሆን? ብቻ ግን የሁላችሁም ቅን እገዛ ስላልተለየኝ አመሰግናለሁ።

# ማውጫ

ገጽ

ምስጋና ........................................................................ i
የዛይ ደሴትና የአካባቢው ካርታ ........................................................ v
አጠቃሎ ........................................................................vi
ምእራፍ አንድ ........................................................................1
መግቢያ ........................................................................ 1
1.2. የጥናቱ አላማ ........................................................................ 3
1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................................................ 3
1.4. የጥናቱ ወሰን ........................................................................ 4
1.5. የመረጃ አሰባሰብና የአጠናን ዘዴዎች ........................................................ 4
1.5.1. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ........................................................ 4
1.5.2. የመረጃ አቀባዮች የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........................................ 5
1.5.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ ........................................................ 5
1.6.ጥናቱን ለማከናወን የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን ........................ 6
1.6.1. ቅድመ ዝግጅት ........................................................ 6
1.7. በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ አቅጣጫዎች ........................10
ምእራፍ ሁለት ........................................................................11
2.1. የዛይ ማህበረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ ........................................................11
2.2. መልከዓ ምድራዊ ገጽታ ........................................................................13
2.3. ቋንቋና ሐይማኖት ........................................................................14
2.3.1. ቋንቋ ........................................................................14
2.3.2. ሐይማኖት ........................................................................14
2.4. የህዝብ ብዛት እና ኢኮኖሚ ........................................................15
2.4.1. የህዝብ ብዛት ........................................................................15
2.4.2. ኢኮኖሚ ........................................................................15
ምእራፍ ሶስት ........................................................................16
ክለሳ ድርሳን ........................................................................ 16
3.1. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ........................................................................16

3.2. ቃላዊ ዝርው ተረክ ....................................................................17

3.3. ተግባራዊ አቀራረብ (Functional Approach) ..............................................19

3.4. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..............................................................21

3.4.1. በውጭ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተሰሩ ጥናቶች ..............................................................23

3.4.2 . በኢትዮጵያ ስነ ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተሰሩ ጥናቶች ..............................................................26

**ምእራፍ አራት** ..............................................................29

የዛይ ማህበረሰብ ዝርው ቃል ተረኮች ትንተና ..............................................................29

4.1. የዛይ ማህበረሰብ ጥንተ አመጣጥ ..............................................................29

4.1.1. የዛይ ማህበረሰብና ያእቆብ ..............................................................29

4.1.2. የዛይ ማህበረሰብና ከእስራኤል አገር መምጣት ..............................................................31

4.1.3. የዛይ ማህበረሰብ ወደ ዝዋይ ደሴት መምጣት ..............................................................35

4.2. ነገስታትና የዛይ ማህበረሰብ..............................................................39

4.2.1. የዛይ ማህበረሰብና አፄ ይኩኑ አምላክ ..............................................................39

4.2.2. የዛይ ማህበረሰብና አጼ ምኒሊክ ..............................................................41

4.2.3. የዛይ ማህበረሰብና አጼ ኃይለስላሴ..............................................................43

4.3. ከሐይቁ ጋር ተያይዘው የሚተረኩ ተረኮች ..............................................................45

4.3.1. የዝዋይ ሐይቅ አፈጣጠር ..............................................................45

4.3.2. የዝዋይ ሐይቅ ቅድስና..............................................................46

አቶ ነገዎ ሸጎሮ በትረካ ላይ( መጋቢት 18 ቀን 2004 ዓ.ም) ..............................................................48

4.3.3 የዝዋይ ሀይቅና «ባእድ አምልኮ»..............................................................48

4.4. የዝዋይ ደሴትና ቅድስና..............................................................49

4.4.1. የመካን መውለድ ..............................................................50

4.4.2. «እርኩስ መንፈስ»ና ፈውስ ..............................................................51

4.4.3. ደብረ ጽዮን ደሴትና የአልጋ ቁራኛ ፈውስ ..............................................................52


4.5. ስነ ምግባርና የዛይ ማህበረሰብ..............................................................53

4.5.1. ትእዛዝ አለማክበር ..............................................................53

4.5.2 እግዚአብሔርን መፍራትና ከቁጣ መዳን..............................................................54

ምእራፍ አምስት ............................................................................ 56
ማጠቃለያ ............................................................................ 56
ዋቢ ጽሁፎች ............................................................................ 58
ሀ. የአማርኛ ምንÄች ............................................................................ 58
ለ. የእንግሊዝኛ ምንÄች ............................................................................ 59
አባሪ አንድ፡- የተረኮች ስብስብ ............................................................................ 62
አባሪ ሁለት ............................................................................ 76
1.የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር ............................................................................ 76
1.1. ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ............................................................................ 76
1.2. ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች ............................................................................ 77
1.3. ተተኳሪ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች ............................................................................ 78
1.4. አባሪ ሶስት የፎቶ ግራፍ ዝርዝር ............................................................................ 79

## የዛይ ደሴትና የአካባቢው ካርታ




ምንጭ፡- Survey Report of the Zay People in Ethiopia ከሚለው መጽሀፍ የተወሰደ

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የዛይ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው። ጥናቱ ከቤተ መጻህፍት ከተሰበሰቡ መረጃዎች በተጨማሪ ጥናቱ ስለሚካሄድበት ማህበረሰብና አካባቢ አጠቃላይ ገጽታ፣ በማህበረሰቡ ስለሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታና በተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃዎች ተሰብስበዋል።

መረጃ የተሰበሰበው ከአስራ ሰባት የመረጃ አቀባዮች ሲሆን ከእነዚህ መካከል ሰባቱ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ናቸው። መረጃዎቹ በመቅረጸ ድምጽ፣ በፎቶ ካሜራና በማስታሻ ደብተር ተይዘዋል። ከመስክ የተገኙትን መረጃዎችም ተግባራዊ አቀራረብን (Functional Approach) መሰረት በማድረግ ለመተንተን ተሞክሯል።

በጥናቱ የማህበረሰቡ ጥንተ አመጣጥ፣ የዝዋይ ሀይቅ አፈጣጠርና ቅድስና፣ የዝዋይ ደሴትና ቅድስና እንዲሁም ስነ ምግባርን የሚያሳዩ በሚል ይዘታቸውን መሰረት በማድረግ ለመመደብ ጥረት ተደርጓል።

በጥናቱ ውጤት መሰረት የዛይ ማህበረሰብ አባላት ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸውን ጥንተ አመጣጣቸውን፣ የዝዋይ ሀይቅ አፈጣጠርና ቅድስናን በመግለጽ ከሌሎች ሀይቆች የተለየ ቅዱስ አድርገው ለማሳየት፣ የማህበረሰቡም አባላት የሚኖሩበት ደሴት ፈውስ የሚገኝበት እንዲሁም ታዋቂ የታሪክ ሰዎች ከእነሱ ጋር ያላቸውን ዝምድና በመግለጽ ማንነታቸውን አግዝፈው ለማሳየት እንደሚጠቀሙባቸው በጥናቱ ታይቷል።

# ምእራፍ አንድ

## መግቢያ

ከዛይ ማህበረሰብ ጋር ተያይዞ በውጭና በአገር ውስጥ ምሁራን የተሰሩ ጥቂት ጥናቶች ይገኛሉ። ጥናቶቹ ከሞላ ጎደል የሚያተኩሩት በማህበረሰቡ ቋንቋና ኢኮኖሚ ላይ ነው። ይሁን እንጂ በፎክሎር ዙሪያ የተሰራ አንድም የጥናት ስራ አላገኘሁም። ከዚህ በመነሳት በዚህ ጥናት የዛይ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ይዘታቸውን ለመመርመር ይሞከራል።

ለዚህ ጥናት በተመረጠው ርእስ ዙሪያ በተለያዩ አጥኚዎች የተሰሩ ጥናቶች ቢኖሩም በዛይ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ዙሪያ ግን አጥኚው ባለው መረጃ መሰረት ምንም አይነት ጥናት አልተካሄደም። ስለዚህ በዚህ ጥናት የዛይ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ይዘት በመተንተን ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ ለመመርመር ይሞከራል።

ጥናቱ አምስት ምእራፎች አሉት። የመጀመሪያው ምእራፍ ለጥናቱ መግቢያ ሊሆን የሚችል ሃሳብ የቀረበበት ሲሆን የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ አላማውን ለማሳካት የተነሱ ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የመረጃ አሰባሰብ እና አተናተን ዘዴ፣ የመረጃ ሰጪዎች የናሙና አመራረጥ ዘዴ፣ ለመስክ ክንውን የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን፣ እንዲሁም በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እቅጣጫዎች ተካተዋል።

በምእራፍ ሁለት ደግሞ ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን የሚያሳዩ መረጃዎች ተካተዋል። በምእራፍ ሶስት በክለሳ ድርሳናት ስር የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትና ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ተካተው ቀርበዋል። የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ውስጥ ከዚህ ጥናት ጋር በርእሰ ጉዳያቸው ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው የተባሉ በውጭ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል እንዲሁም በኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የቀረቡ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች ከጥናቱ ጋር ያላቸውን ተመሳስሎና ልዩነት በሚመለከት ዳሰሳ ተደርጎባቸዋል። በተጨማሪም ይህ ጥናት በተከናወነበት አካባቢ ላይ በተለያዩ ክፍለ ትምህርቶች የተሰሩ የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች በማህበረሰቡ ዙሪያ ምን ጥናት ተሰራ የሚለውን ለማሳየት ያህል ደሰሳ ሳይካሄድባቸው ለጥቆማ ያህል ቀርበዋል። በተጨማሪም በዚሁ ምእራፍ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት በሚለው ርእስ ስር የተለያዩ ምሁራን ቃላዊ ዝርው

ተረክንና ተግባራዊ አቀራረብን አስመልክተው ያነሷቸው ንድፈ ሀሳቦች ተካተው ቀርበዋል።

በምእራፍ አራት የዛይ ማህበረሰብ አባላት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ይዘታቸው ትንተና የተደረገበት ሲሆን ተረኮቹ ምን ይዘት እንዳላቸውና ያላቸው ማህበራዊ ፋይዳ ለማሳየት ተሞክሯል። በምእራፍ አምስት ደግሞ የጥናቱ ማጠቃለያ፣ የዋቢ ጽሁፎች ዝርዝርና አባሪዎች ተካተዋል።

## 1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማከናወን ያነሳሱኝ ሶስት ምክንያቶች ናቸው። አንደኛው ምክንያት *«ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ»* የሚለው መጽሐፍ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የዛይ ማህበረሰብ አባላት ታቦተ ጽዮንን ይዘው ከአክሱም እንደመጡና ለብዙ ጊዜም በቦታው ላይ መኖራቸውን ሳነብ እነዚህ ሰዎች ቀድመው ከነበሩበት ስፍራ መጥተው በደሴት ላይ ሲኖሩ ስለ እራሳቸው ምን ይሉ ይሆን? የሚል ጥያቄ ያጭርብኝ ስለነበር በዚህ ትምህርት ክፍል ገብቼ የመማር እድል ሳገኝ የመመረቂያ ጽሁፌን ማህበረሰቡ ላይ እንድሰራ አነሳስቶኛል።

ሁለተኛው አነሳሽ ምክንያቴ ጓደኛዬ ብሩክ ያሬድ በዛይ ደሴት ዙሪያ መንፈሳዊ ይዘት ያለው የዶክመንተሪ ፊልም ለመስራት ሄዶ ሲመልስ ስለማህበረሰቡ ቀደም ሲል ካነበብኩት መፅሐፍ በተጨማሪ ስለማህበረሰቡ አመጣጥና አኗኗር ሌላ መረጃ ስለጨመረልኝ የመመረቂያ ስራዬን በማህበረሰቡ ላይ እንዳደርግ የመነሻ ምክንያት ሆኖኛል።

ከዚህ ሌላ "Theoretical and Critical Understanding of Folklore" የሚለውን ኮርስ በምማርበት ጊዜ በፎክሎር ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶችን የማየት እድል አጋጥሞኝ ነበር። በዚህ ጊዜ በዛይ ማህበረሰብ ፎክሎር ዙሪያ የተሰራ አንድም ጥናት አላገኘሁም ነበር። በዚህ ምክንያትም ጊዜው ደርሶ የጥናት ርእስ በምመርጥበት ጊዜ የጥናት ስራዬ ርእስ በማህበረሰቡ ቃላዊ ዝርው ተረክ ላይ እንዲሆን ምክንያት ሆኖኛል።

## 1.2. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት አላማ የዛይ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በመሰብሰብ ይዘታቸውን መተንተን ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎችም ይኖሩታል።

- በማህበረሰቡ ቃላዊ ዝርው ተረኮች አማካኝነት ጥንተ አመጣጡ፣ ሃይቁና ደሴቱ እንዴት እንደተገለጹ ይመረመራል።
- ማህበረሰቡ በሚናገራቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች ውስጥ የሚተላለፉ ጉዳዮች ይተነተናሉ።
- በማህበረሰቡ የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ያላቸው ማህበራዊ ፋይዳ ይመረመራሉ፤
- ማህበረሰቡ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹን ለቀጣዩ ትውልድ የሚያስተላልፍበት ምክንያት ይፈተሻል።

የጥናቱን ዋና እና ዝርዝር አላማዎች ለማሳካት በጥናቱ የሚከተሉት ጥያቄዎች ይመለሳሉ።

- ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ ለማህበረሰቡ ምን ፋይዳ አላቸው?
- በማህበረሰቡ ውስጥ በሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች የማህበረሰቡ የዘር ሀረግ፣ ጥንተ አመጣጥ እንዲሁም ሀይቁና ደሴቱ እንዴት ይገለጻሉ?
- በቃላዊ ዝርው ተረኮቹ ውስጥ የሚተላለፈው ዋነኛ ጉዳይ ምንድ ነው?
- ማህበረሰቡ በቃላዊ ዝርው ተረኮቹን ለቀጣዩ ትውልድ ለምን ያስተላልፋል?

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት አላማውን መሰረት ያደረጉ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል።

- በተጠኚ ማህበረሰቦቹ ዙሪያ ሌሎች ጥናቶችን ለማድረግ ለሚፈልግ አጥኚ እንደ ግብአት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።
- ማህበረሰቡ በቃላዊ ዝርው ተረኮቹ አማካኝነት ምን ምን ጉዳዮችን እንደሚያስተላልፍ ለተመራማሪዎችና ለአንባቢዎች ግንዛቤ ይፈጥራል።
- በቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ጥናት ለማድረግ ለሚፈልግ የፎክሎር አጥኚ የመነሻ ሀሳብ ሊሰጥ ይችላል።

- የማህበረሰቡ ተረኮች መጠናታቸው ለፎክሎር ጥናት መስክ የራሱ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

### 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በዛይ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ በመመስረት የተረኮቹን ይዘት የሚመረምር ነው።
የዛይ ማህበረሰብ አባላት በተለያዩ ቦታዎች የሚኖሩ ቢሆኑም ይህ ጥናት ግን ትኩረት ያደረገው በዝዋይ ሀይቅ ላይ ከሚገኙት አምስት ደሴያት መካከል በብዛት ማህበረሰቡ አለበት የሚባለውና ስፋትም እንዳለው በሚነገርለት ደብረ ጽዮን ደሴት ላይ ብቻ ነው።

## 1.5. የመረጃ አሰባሰብና የአጠናን ዘዴዎች

### 1.5.1. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ይህ ጥናት አላማውን ለማሳካትና የምርምር ጥያቄዎቹን በሚገባ ለመመለስ ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል። Dorson (1972:465) አንድ የፎክሎር አጥኚ ለጥናቱ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ከመስክ፣ ከቤተ መጻህፍትና፣ ከታተሙና ካልታተሙ ጽሁፎች ማግኘት እንደሚችል ይገልጻሉ።

በቀዳማይ ምንጮች ከመስክ የመረጃ አቀባዮች በቀጥታ የተገኙ መረጃዎች ሲሆኑ ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታና፣ የቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በጥቅም ላይ ውለዋል።

ቃለ መጠይቅ በዋና የመረጃ መሰብሰቢያነት የተመረጠ ዘዴ ሲሆን የማህበረሰቡን ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ጠንቅቀው ያውቃሉ የሚባሉ የመረጃ አቀባዮችን በመምረጥ ተረኮቹን ሲተርኩ ሰፊ የድምጽ ቀረጻ ተከናውኗል። የተለያዩ አጋጣሚዎችን በመጠቀምና በመደበኛ ቃለ መጠይቅ ወቅት ግልፅ ያልሆኑና ማብራሪያ ለሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ኢ-መደበኛ ቃለ መጠይቅ በጥቅም ላይ ውሏል። በዚህም መሰረት ከአስራ ስምንት የመረጃ አቀባዮች አርባ ስድስት የሚሆኑ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ተሰብስበዋል። ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል ስምንቱ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ናቸው። ቁልፍ የመረጃ አቀባይ የተባሉበት ምክንያት ለጥናቱ የሚያስፈልጉ በርካታ መረጃዎችን የሰጡ በመሆናቸው

ነው። ቀሪዎቹ አስር የሚሆኑ የመረጃ አቀባዮች ደግሞ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ከሰጡት መረጃ በተጨማሪ የመረጃውን ክፍተት ለመሙላት እንዲያግዝ መረጃ የሰጡ ናቸው።

በመስክ ቆይታ ወቅት የማህበረሰቡን አኗኗር ለመገንዘብ የምልከታ ዘዴ በተግባር ላይ ውሏል። በዚህ ወቅትም ማስታወሻ በመያዝና ፎቶግራፍ በማንሳት መረጃዎችን ለማያዝ ጥረት ተደርጓል። በቃለ መጠይቅና በምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመረዳት ተተኳሪ ቡድን ውይይት ተደርጓል። በዚህ ዘዴም መረጃዎችን ለመሰብሰብ ማስታወሻና ፎቶ ካሜራ በጥቅም ላይ ውሏል።

### 1.5.2. የመረጃ አቀባዮች የናሙና አመራረጥ ዘዴ

የናሙና አመራረጡ የተከናወነው የማህበረሰቡን አጠቃላይ ታሪክ ያውቃሉ ተብለው የተጠቆሙ ሰዎችን በመምረጥ ነው። ከዚህ በተጨማሪ እድሜና ጾታን መሰረት በማድረግ በተለያዩ የእድሜ ደረጃ ላይ ያሉ ሁለቱም ጾታዎች መረጃ በመስጠት ሂደት ተሳታፊ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። ለጥናቱ አጋዥ የሚሆኑ መረጃዎችን እንዲሰጡ የተመረጡት አስራ ስምንት የመረጃ አቀባዮች ሲሆኑ በጥቆማ ከተመረጡት መረጃ አቀባዮች መካከል ደግሞ ሁለቱ ሴቶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ወንዶች ናቸው።

### 1.5.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ከላይ በጠቀስኳቸው ዘዴዎች የሰበሰብኩ ሲሆን በመስክ ቆይታዬ ወቅትም መረጃዎቹን በማስታወሻ ደብተሬ ላይ የማስፈር ስራ ሰርቻለሁ። በደሴቱ ላይ መብራት ባለመኖሩ በመቅረጸ ድምጽ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ከሰአት በኋላ ላይ የተወሰነ ጊዜ በመስጠት በማስታወሻ ደብተሬ ላይ ለማስፈር ሞክሬያለሁ። በዚህም በሰበሰብኳቸው መረጃዎች ላይ ክፍተት ሳገኝና ግራ የሚያጋባ ጉዳይ ሲያጋጥመኝ ወደ መረጃ አቀባዮቹ በመሄድ በድጋሚ ቃለ መጠይቅ በማድረግ ክፍተቱን ለመሙላትና ግራ ያጋቡኝንም ነገሮች መፍትሄ ለመስጠት ሞክሬያለሁ።

በመስክ ቆይታዬ ወቅትም የመረጃ ማሳባሰቡ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ ከመስክ የሰበሰብኳቸውንና በማስታወሻ ደብተሬ ላይ ያሰፈርኳቸውን መረጃዎች የመስኩ ምሁራን ከሚያነሳቸው ሀሳቦች ጋር በማጣመር ትንታኔ ሰጥቼባቸዋለሁ። ጥናቱ ትኩረት

ያደረገበትን ቃላዊ ዝርው ተረክ ለማህበረሰቡ ያለውን ፋይዳ ለመመርመር ተግባራዊ አቀራረብን እንደ መተንተኛ ተጠቅሚያለሁ።

## 1.6.ጥናቱን ለማከናወን የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን

### 1.6.1. ቅድመ ዝግጅት

ለጥናቱ የሚጠቅሙ መረጃዎችን ወደ መስክ  በመሄድ ከመሰብሰቤ በፊት የተለያዩ ቅድመ ዝግጅቶችን አከናውኛለሁ። ጥናቱን ከግብ ለማድረስም አካባቢውን ከሚያውቁ ሰዎች ጋር ውይይት ያደረግሁ ሲሆን ጥናቱ በሚከናወንበት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያም የተሰሩ የምርምር ስራዎችና የመስኩ ምሁራን ያዘጋጇቸውን የተወሰኑትን ማጻህፍት ለማንበብ ሞክሬያለሁ። እንዲሁም ወደ መስክ ሄጄ መረጃዎችን በአግባቡ ለመሰብሰብና በመስክ ቆይታዬም ወቅት ሊጠቅሙኝ የሚችሉ አጋዥ መሳሪያዎችን በግዥና በውሰት ለማሟላት ጥረት አድርጌያለሁ።

### 1.6.2. የመስክ ክንውን

ለመስክ የሚያገለግሉኝን ቅድመ ዝግጅቶች ካጠናቀኩ በኋላ መጋቢት 13 ቀን 2004 ዓ.ም ጉዞዬን ወደ መቂ አድርጌያለሁ። ወደ መቂ ልሄድ የቻልኩበት ምክንያት የደብረጽዮን ደሴትን የሚያስተዳድረው ዝዋይ ዱግዳ ወረዳ የሚገኘው አቡራ ከመቂ ወደ ውስጥ ተገንጥሎ በሚያስገባው መንገድ አስራ ስምንት ኪሎ ሜትር ገደማ ርቀት ላይ መሆኑን ቀደም ብዬ ያገኘሁትን መረጃ መሰረት  አድረጌ ነው። መቂ የደረስኩት ከረፋዱ አምስት ሰአት አካባቢ ነበር። እለቱ የገበያ በመሆኑ ከመቂ ተነስቶ ወደ አቡራ የሚሄድ የህዝብ ማመላለሻ አውቶብስ አግኝቼ ጉዞዬን ወደ እዛው አቀናሁ። አውቶብሱ ብዙ ተሳፋሪና እቃ በአንድ ላይ አጭቆ የጫነ ከመሆኑም በላይ በጣም ያረጀ ስለሆነ አቡራ ለመድረስ ከአንድ ሰአት ተኩል በላይ ጊዜ ፈጅቶበታል።

አቡራ የደረስኩት በምሳ ሰአት በመሆኑ የወረዳውን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሰራተኞች ማግኘት ስላልቻልኩ ከምሳ ሰአት በኋላ በድጋሚ በመሄድ ከትምህርት ክፍሉ የተጻፈልኝን የድጋፍ ደብዳቤ በመያዝና የመጣሁበትን አላማ በማስረዳት በማህበረሰቡ

ዙሪያ የተሰሩ የታተሙም ሆኑ ያልታተሙ ጽሁፎች ካሉ እንዲያውሱኝ ጠየኳቸው። በባህልና ቱሪዝም ቢሮው ያገኘኋቸው የቢሮው ሰራተኞች በተጠኚው ማህበረሰብ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች እንደሌሉ ነግረውኝ በወረዳው ኮሙኑኬሽን በኩል የተሰሩ ጥናቶች ካሉ ወደ ጽ/ቤቱ ሄጄ እንድመለከት መሩኝ። በተመራሁት መሰረትም የወረዳው ኮሙኑኬሽን ጽ/ቤት እዛው ጊቢ ውስጥ በመሆኑ ፊጥኜ ወደ እዛው አመራሁ። የጽ/ቤቱ ሰራተኛ ግን አዲስ ተቀጣሪ በመሆኑ ምንም አይነት ነገር እንደማያውቅና ከእሱ በፊት ለብዙ ጊዜ የሰራው ሰራተኛ በቅርብ የሚገኝ በመሆኑ እሱን እንደሚያገናኘኝ ነግሮኝ ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ ተመልሼ እንድመጣ ነግሮኝ ተለያየን።

በቀጠሮዬ መሰረት ከሰላሳ ደቂቃ በኋላ ወደ ጽ/ቤቱ አመራሁ። ነገር ግን በጽ/ቤቱ የኮሙኑኬሽን ባለሙያ ሆኖ ሲሰራ የነበረውን ሰው አግኝቼ የመጣሁበትን አላማ በመንገር በተጠኚው ማህበረሰብ ላይ የተሰሩ የታተሙም ሆኑ ያልታተሙ ጽሁፎችን ማግኘት እችል እንደሆነ ብጠይቀውም ከቦታው ርቀትና ከበጀት እንጻር አንድም ጥናት አለመሰራቱን ነግሮኝ ወደ ወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ሄጄ እንድጠይቅ ጠቁሞኝ ተሰነባበትን።

የወረዳው ኮሙኑኬሽን ጽ/ቤት ሰራተኛ የነበረው ሰው በጠቆመኝ መሰረት ጉዞዬን ወደ ወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት አደረኩ። የአስተዳደሩ ጽ/ቤት ቅርብ በመሆኑ ጊዜ ሳይፈጅብኝ በቶሎ ልደርስ ችያለሁ። አስተዳደር ጽ/ቤቱም እንደደረስኩ የዝዋይ ዱግዳ ወረዳ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ አቡበከር አዳን አግኝቼ ቀደም ሲል ሳደርግ እንደነበረው ከትምህርት ክፍሉ የተጻፈልኝን የድጋፍ ደብዳቤ በማሳየትና የመጣሁበትን አላማ በመንገር ትብብር እንዲደረግልኝ ብጠይቅም የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ሀላፊም እንደ ኮሙኑኬሽን ጽ/ቤቱ ሁሉ በማህበረሰቡ ላይ ምንም አይነት የታተመም ሆነ ያልታተመ ፅሁፍ እንደሌለ ነግረው አሰናብተውኛል።

ከአቡራ ወደ መቂ ለመሄድ ጊዜው ስለመሸና መጓጓዣ ማግኘት የማይቻል በመሆኑ እዛው ወረዳ ውስጥ ወደ ሚገኝ ማረፊያ ቤት ሄጄ አደርኩ። በቀጣዩ ቀን ወደ መቂ ለመሄድ ብነሳም እለቱ የገበያ ባለመሆኑ የህዝብ ማመላለሻ አውቶብስ ቶሎ ማግኘት አልቻልኩም ነበር። የሆኖ ሆኖ አውቶብሱ ዘግይቶ ቢመጣም እረፋፍጄ ወደ መቂ ከተማ ተጓዝኩ። መቂ እንደገባሁም ጊዜ ሳላጠፋ ወደ ዝዋይ ከተማ መሄድ ነበረብኝና ጉዞዬን ወደ ዝዋይ አደረኩ። ዝዋይ ከተማ እንደደረስኩም ጥናት ወደ ማደርግበት ደሴት የሚወስደኝ የሞተር ጀልባ ለመያዝ ወደ ሀይቁ ሄድኩ። ሀይቁ አካባቢ እንደደረስኩም

ወደ ደሴቱ የሚሄድ መጓጓዣ ማግኘት አልቻልኩም ነበር። የሞተር ጀልባዎቹ ሌላ ተሳፋሪ ባለመኖሩ እኔን ብቻ ወደ ደሴቱ ለማድረስ የሚጠይቁኝ ዋጋ እጅግ የተጋነነ ነበር። በመጨረሻ ላይ ግን አሳ ለማከፋፈል ወደ ዝዋይ መጥቶ ወደ ደሴቱ የሚመለስ የአሳ መጫኛ የሞተር ጀልባ አግኝቼ አሳ ጭኖባቸው ከነበሩ እቃዎች ጋር አንድ ላይ ጭኖኝ በግምት ከአንድ ሰአት ተኩል እስከ ሁለት ሰአት ያህል ከተጓዘ በኋላ ደብረ ጽዮን ደሴት አድርሶኛል።

ደብረ ጽዮን ደሴት አመሻሽቼ ከገባሁ በኋላ ማረፊያ መፈለግ ነበረብኝ። ሆኖም በደሴቱ ውስጥ ምንም አይነት የሆቴል አገልግሎት የሚሰጡ የንግድ ቤቶች የሉም። ስለዚህ ከጀልባው ከወረድኩ በኋላ ሻንጣዬን የያዘልኝ ልጅ የት ማረፍ እንደምችል ስጠይቀው የቤተ ክርስቲያኑን አስተዳዳሪ ሊያሳርፉኝ እንደሚችሉ በጠቆመኝ መሰረት እዛው እንዲያደርሰኝ ጠይቄው ወደ አስተዳዳሪው ቤት በመሄድ ላይ ሳለን እመንገድ ላይ አንድ ተለቅ ያሉ ሰው አገኙን። ከዚያም አብሮኝ ያለውን ልጅ በዛይኛ ቋንቋ ካናገሩት በኋላ እኔን ደግሞ ከየትና ምን ፈልጌ እንደመጣሁ በአማርኛ ጠየቁኝ። እኔም ወደ ደሴቱ የመጣሁበትን ምክንያት ከነገርኳቸው በኋላ ማረፊያ እየፈለኩ መሆኔን ነገርኳቸው። እሳቸውም እቤታቸው ማረፍ እንደምችል ሲነግሩኝ ምስጋና አቅርቤ እሳቸው ከፊት እኛ ደግሞ ከኋላ በመሆን ወደ ቤታቸው አመራን።

መምሬ ገ/መስቀል ቤታቸው ካደረሱኝ በኋላ ወደ ፍል ውሃ ሄጄ እንደምታጠብ ነግረውኝ ልብሴን እንድቀይር ለማረፊያ ትሆነኝ ዘንድ በሰጡኝ አነስተኛ ክፍል ውስጥ ትተውኝ ወጡ። ከዚያም ልብሴን ከቀየርኩ በኋላ ከመምሬ ገ/መስቀል ጋር ለተወሰኑ ደቂቃዎች ተጉዘን የአካባቢው ማህበረሰብ ፍል ውሃ ብሎ የሚጠራው ቦታ ላይ ደረስን። ፍል ውሃ ከሀይቁ በቅርብ ርቀት ሰፋ ባለ ሜዳ ላይ የሚገኝ ሲሆን ምንም አይነት መከለያ የሌለው የመታጠቢያ ስፍራ ነው። ጊዜው ጨለምለም ያለ በመሆኑ በጉድጓዱ ውስጥ የሚታጠቡ የአካባቢው ሰዎችን አገኘን። እኔም ልብሴን አውልቄ ፈራ ተባ እያልኩ ወደ መታጠቢያው ተቀላቀልኩ።

በማግስቱ ጠዋት እለቱ ቅዳሜ በመሆኑ ብዙዎቹ የማህበረሰቡ አባላት ይገኛሉ ወደ ሚባልበት ቤተክርስቲያን ተነስቼ አመራሁ።ቅዳሴው ከተጠናቀቀ በኋላም በመምሬ ገ/መስቀል አማካኝነት የተወሰኑትን የተዋወቅሁ ሲሆን ከተዋወኳቸው የማህበረሰቡ አባላት ጋርም ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ቀጠሮ በመስጠት ተሰነባብቻለሁ።

በማግስቱ እሁድ ከቅዳሜው ቀን በላይ ብዙ መረጃ አቀባዮቼን ያገኘሁበት ቀን ነበር። የማህበረሰቡ አባላት በየሳምንቱ እሁድ ከቅዳሴ ሰአት በኋላ ቤተ ክርስቲያን ጊቢ ውስጥ የሚያከናውኑት የሰንበቴ ማህበር ስለነበር እኔም እዛው በመገኘት ብዙዎቹ የመረጃ አቀባዮቼን ለመተዋወቅ ችያለሁ። በዚህ እለት በሰንበቴ ማህበሩ ላይ ተገኝቼ አብዛኞቹን የማህበረሰቡን አባላት በመምሬ ገ/መስቀል አማካኝነት በመተዋቂ ጥሩ ግንኙነት ልፈጥር በመቻሌ የተወሰኑ የመረጃ አቀባዮችን እዛው ቃለ መጠይቅ ያደረግሁ ሲሆን ሌሎችን ደግሞ ቀጠሮ በማስያዝ ቃለ መጠይቁን አከናውኛለሁ።

መረጃ ለመሰብሰብ እንደ ጥሩ አጋጣሚ ብዬ ከወሰድኩት ሰንበቴ በተጨማሪ የጽዋ ማህበር ላይ በመገኘት መረጃ የሰበሰብኩ ሲሆን የአካባቢው ማህበረሰብ ወደ ሚኖሩባቸው ማለትም ዱርመጃ፣ አቦሩብርና መስኖ ተብለው በሚጠሩት መንደሮች እየተዘዋወርኩ የአካባቢውን ታሪክ ጠንቅቀው ያውቃሉ ከሚባሉ የመረጃ አቀባዮች መረጃ ልወስድ ችያለሁ።

በመስክ ቆይታዬ ወቅት የማህበረሰቡ አባላት አጠቃላይ ማለት ይቻላል የሚመገቡት አሳ መሆኑን ለማየት ችያለሁ። ይህን ያነሳሁት ነገሩ አዲስ ሆኖ ሳይሆን ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት መረጃውን ለማሰባሰብ ወደ ስፍራው የሄድኩት የአብይ ጾም ወቅት በመሆኑ መምሬ ገ/መስቀል ቤት ያረፍኩ እለት ማታ እራት እንድንበላ የአሳ ወጥ በቀረበልኝ ጊዜ አሳ ጾም ነው ብዬ ስለማምን እንደማልበላ ስነግራቸው እሳቸውም «አሳ የባህር ሳኀመን ነው ዝም ብለህ ብላ» በማለታቸው እኔም የማምነውን ጾም አፍርሼ ማህበረሰቡን ለመመሳሰል አሳ ተመግቤያለሁ።

መረጃ የማሰባሰቡን ሂደት ለመጨረስ ስቃረብ በአንዳንድ ነጥቦች ላይ የቡድን ውይይት ለማድረግ ፈልጌ ቁልፍና ቁልፍ ያልሆኑ የመረጃ አቀባዮችን ሰብስቤ ለማነጋገር ሙከራ ባደርግም የማህበረሰቡ አባላት ታሪክ ያውቃሉ ከሚሏቸው የመረጃ አቀባዮች ጋር ተቀምጠው ውይይት ለማድረግ ፈቃደኛ አልሆኑልም ነበር። ነገር ግን ለቡድን ውይይቱ የተመረጡት መረጃ አቀባዮቼን በማግባባት የቡድን ውይይቱ ተከናውኗል።

ባጠቃላይ ከመጋቢት 13 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 2 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ ለጥናቱ የሚጠቅሙኝን መረጃዎች ሰብስቤ ሚያዝያ 3 ቀን 2004 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ተመልሻለሁ። በደሴቱ በቆየሁባቸው ጊዜያትም መረጃ ፈልጌ

ያነጋገርኳቸው ከማህበረሰቡ አባላት አብዛኞቹ የሚያውቁትን መረጃ ሁሉ ፍጹም ቅን በሆነ መንፈስ ሰጥተውኛል።

## 1.7. በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ አቅጣጫዎች

ይህን ጥናት ለማድረግ መስክ በቆየሁባቸው ጊዜያት የተለያዩ ችግሮች አጋጥመውኛል። ለጥናቱ የሚያገለግሉኝን መረጃዎች ለመሰብሰብና ላጋጠሙኝ ችግሮች የተለያዩ የመፍትሂ አቅጣጫዎችን በመጠቀም በመረጃ አሰባሰብ ወቅት ያጋጠሙኝን ክፍተቶች ለመሙላት ጥረት አድርጌያለሁ።

በመስክ ቆይታዬ ወቅት ካጋጠሙኝ ችግሮች መካከል አንዱ በማህበረሰቡ ውስጥ ለማንኛውም ወደ ደሴቱ ለሚመጣ ሰው የማህበረሰቡን አጠቃላይ ታሪክ ያውቃሉ የሚባሉ የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ናቸው ተብሎ ስለሚታመን መረጃ እንዲሰጡኝ የምጠይቃቸው ሰዎች ሁሉ ወደ እነሱ ይመሩኛል እንጂ እነሱ ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም። ይህን ችግር ለመፍታትም በተለያዩ አጋጣሚዎች የማገኛቸውን ሰዎች እቤታቸው ጭምር በመሄድ እያግባባሁዋቸው መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ።

ሁለተኛው ችግር በወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት አስተዳደርም ሆነ በኮሙኒኬሽን ጽ/ቤቱ በኩል በማህበረሰቡ ዙሪያ የተሰሩ ምንም አይነት የታተሙም ሆኑ ያልታተሙ ፅሁፎችን ማግኘት ያለመቻል ነበር። በማህበረሰቡ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶችን ለመፈለግ የተለያዩ ቢሮዎች ብሄድም ምንም አይነት ጽሁፍ ማግኘት አልቻልኩም። ይህን ችግር ለመቅረፍ በማህበረሰቡ ዙሪያ የተሰሩ ጥቂት ስራዎችን በግብአትነት ለመጠቀም ችያለሁ።

# ምእራፍ ሁለት

## 2.1. የዛይ ማህበረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ

በዚህ ርእስ ስር የዛይ ማህበረሰብ በደሴቱ ላይ የሰፈሩበትን ታሪካዊ አመጣጥ በሚመለከት ወጥነት ያለው መረጃ ባይገኝም የተለያዩ አጥኚዎች የማህበረሰቡን አመጣጥ በሚለከት ያነሷቸውን ሀሳቦችና በማህበረሱቡ አባላትም የሚታመንባቸው ሀሳቦች ይቀርባሉ። የማህበረሰቡን ታሪካዊ አመጣጥ ከማየታችን በፊት ማህበረሰቡ «ዛይ» የሚለውን ስያሜ እንዴት ሊያገኝ እንደቻለ እንመለከታለን።

የዛይ ማህበረሰብ ራሱን «ዛይ» በማለት የሚጠራ ሲሆን አካባቢውን ደግሞ «የዛይ ምድር» በማለት ይጠራል። ማህበረሰቡ በአካባቢው ኦሮሞዎች «ላቂ»[1] ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ማህበረሰቡ ግን ይህን ስም አይቀበለውም። «ዛይ» የሚለው መጠሪያ በተለያዩ ሁኔታዎች የተገኘ እንደሆነ ይናገራሉ።

የመጀመሪያው «ዛይ» የሚለው መጠሪያ የተገኘው በዮዲት ጉዲት ጦርነት ምክንያት ከአክሱም ተነስተው ታቦተ ጽዮንን ይዘው ወደ ስፍራው የመጡት ስደተኞች በመዝሙር 118 ላይ «ዛይ ብሂል ዝኩር እግዚአብሔር» (ዘወትር የሚወሳ፣ የሚታሰብ እግዚአብሔር) ያለውን ይዘው ምድሪቱን «ዛይ» ብለዋታል[2]። በሌላ በኩል «ዛይ»የሚለው ቃል ጥንተ መገኛው ዝዋይ የሚለው ቃል ነው የሚሉ ወገኖች አሉ። አክሱማውያን ወደ ስፍራው ሲመጡ ሙቀቱ በጣም እንዳስቸገራቸው ለመግለጽ በግዕዝ ቋንቋ «ዝ ዋዕይ» (ይህ ሙቀት) በማለታቸው ቦታው «ዝ ዋዕይ« የሚለውን ስያሜ አግኝቶ ሲኖር ቀስ በቀስ «ዛይ» ለመባል በቃ[3]።

ሶስተኛው «ዛይ» የሚለው መጠሪያን አስመልክቶ የሚታመነው ከታቦተ ጽዮን ጋር ወደ ደሴቱ የመጡት ሰፋሪዎች ቦታው እንደ ደረሱ የቦታው አቀማመጥ ስላስደሰታቸው ስሜታቸውን በግዕዝ ቋንቋ «ዝ-ዋይ» (ይህ አስደናቂ፣ አስገራሚ) በማለት እንደገለጹና የማህበረሰቡም ስያሜ ከዚህ ሊገኝ እንደቻለ ዘላለም(2001፣22) ያስረዳል።

---

[1] በኦሮምኛ ቀዛፊ ማለት ነው።
[2] መምሬ ዘርአጽዮን ሀ/ማርያም
[3] መምሬ ገ/መስቀል ሂርጳ

ሌላው የማህበረሰቡ መጠሪያ አመጣጥን አስመልክቶ ካህናት አክሱም ወደ ደሴቱ ሲደርሱ ቦታው በውሃ ተከቦ በማየታቸው በግዕዝ ቋንቋ «ዝ-ማይ» (ይህ ውሃ) በማለት ለቦታው ስያሜ ሰጡት፤ በጊዜ ብዛትም «ዝ-ማይ» የሚለው ስያሜ ዝዋይ በሚለው ተለወጠ በማለት ሀብተማርያም (1986፤186) ይገልጻሉ። «ዛይ» የሚለው መጠሪያ የህብረተሰቡ ብቻ ሳይሆን በሀይቁ ውስጥ የሚገኙት የአምስቱም ደሲያት የጋራ መጠሪያ መሆኑን ተስፋዬ (2000፤5) ያስረዳል።

ቀጥሎ የዛይ ህዝብ ታሪካዊ አመጣጥን በተመለከተ የተለያዩ ጥናቶች የሚያነሱትንና ማህበረሰቡም ስለ ታሪካዊ አመጣጡ የሚያምንባቸውን ነገሮች ማስቀመጥ ተገቢ በመሆኑ ያሉትን ሀሳቦች እንደሚከተለው ለማሳየት እሞክራለሁ።

የዛይ ማህበረሰብ አባላት ለመጀመሪያ ጊዜ በደሴቱ የሰፈሩት በዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዮዲት ጉዲት አማካኝነት በተነሳ ጦርነት ምክንያት መሆኑን ተስፋዬ (2000፤8) ያስረዳል። የአይሁድ እምነት ተከታይ የነበረችው ዮዲት በአክሱም ዘመነ መንግስት ቤተክርስቲያኖችን ትዘርፍና ታቃጥል ስለነበር በወቅቱ የነበረው የአክሱም ንጉስ አንበሳ ውድም ከቀሳውስቱና ከህዝበ ክርስቲያኑ ጋር በመሆን ወደ ሸዋ (መንዝ) እንደተሰደደና ከዚያም ወደ ዛይ ደሴት መግባቱን (ዝኒ ከማሁ) ይናገራል። ዮዲት ሀይሏ ተዳክሞ ካረፈች በኋላ ደብረ ጽዮን ደሴት ላይ ከነበሩት ስደተኞች ከፊሎቹ ታቦተ ጽዮንን ይዘው ወደ አክሱም ሲመለሱ ከፊሎቹ ግን እዛው ደሴት ላይ ቀርተዋል። በዚህ የተነሳም ማህበረሰቡ በደሴቱ ላይ እንዲሰፍር ምክንያት ሊሆን ችሏል ማለት ይቻላል። Henze (1973፤78) የመጀመሪያዎቹ የደሴቱ ሰፋሪዎች በ11ኛው ወይም በ12ኛው ክፍለ ዘመን መስፈራቸውን ይናገራሉ። ሆኖም በማህበረሰቡ አባላት ዘንድ በሰፊው የሚታመነው በዮዲት ጉዲት ጦርነት ምክንያት ታቦተ ጽዮንን ይዘው ወደ ደሴቱ መምጣታቸው ነው።

ሌላው ተስፋዬ (2000፤16-17) ከ16ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ የዝዋይ ሀይቅ አካባቢ የጦርነት ቀጠና እንደነበርና በዚህ ምክንያትም ከደሴቱ ውጭ የነበሩ ኦሮሞዎች በሽሽት ወይም በምርኮ ወደ ደሴቱ በመግባት ቀድሞ ከነበረው ህዝብ ጋር መቀላቀላቸውን ያስረዳል። ተስፋዬ የማህበረሰቡን ጥንተ አመጣጥ በሚመለከት እንደ ተጨማሪ ምክንያት የሚገልጸው በዛዮችና በኦሮሞዎች መካከል የነበረው አብሮ የመኖር ሂደት ያስከተለው ውህደት

መሆኑ ነው ። በአካባቢው የሰፈሩት ኦሮሞዎች ለከብቶቻቸው የግጦሽ መሬትና ውሃ ለማግኘት ሲሉ መስፈራቸው ቀስ በቀስ በሁለቱ ማህበረሰቦች ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ግንኙነቶች እንደተጀመሩና ክርስትናን ከተቀበሉ የቦረና ኦሮሞዎች ጋር ጋብቻ በመመስረት ግንኙነታቸው እየተጠናከረ መሄዱን ይዘረዝራል። በኦሮሞ ባህል መሰረት ጉዲፈቻና ሞጋሳ በሁለቱ ማህበረሰቦች መካከል ውህደት ለመፍጠርና አብሮ መኖርን ለማጠናከር ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተና ቀስ በቀስም ሰፋሪዎቹ ኦሮሞዎች በደሴቱ ላይ መኖር በመጀመራቸው በቀድሞ የዛይ ሰፋሪዎች ላይ በመደረብ አሁን ላለው የዛይ ህዝብ ታሪካዊ አመጣጥ አስተዋጽኦ ማበርከታቸውን አስፍሯል።

## 2.2. መልክዓ ምድራዊ ገጽታ

የዝዋይ ሀይቅ ከአዲስ አበባ 160 ኪ.ሜ ርቀት  ወደ ሀዋሳ በሚወስደው መንገድ ላይ ይገኛል። ሀይቁ 1620 ሜርት ከባህር ጠለል በላይ ሲሆን ጥልቀቱ በአማካይ አራት ሜትር ይሆናል። ሀይቁ በስምጥ ሸለቆ ከሚገኙ ሌሎች ሀይቆች ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ጥልቀት ያለው ነው (ተስፋዬ፣ 2000፣1  Henze 1973:76)።

የዝዋይ ሀይቅን በስተሰሜን የቦራ ተራራ፣ የመቂ ወንዝና ከተማ፣ በስተደቡብ ከቦጩሳ መንደር በስተጀርባ የአሊቶ ተራራ፣ የቡልቡላ ወንዝ፣ በስተምስራቅ የአሰላ ከተማ አዋሳኝ የገጠር መንደር(ቁልምሳ)ና በስተምእራብ ደግሞ የዝዋይ ከተማ ያዋስኑታል።

እንደ Henze ገለጻ በዝዋይ ሀይቅ ውስጥ አምስት ደሲያት የሚገኙ ሲሆን በእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ምክንያት የተፈጠሩ መሆናቸው የሚያመሳስላቸው ቢሆንም በቅርጽና በመጠን ግን ይለያያሉ። ደሴቶቹ ካላቸው አቀማመጥ አንጻር የደቡብ ምዕራብና የምስራቅ ደሴቶች ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ። በደቡብ ምዕራብ በኩል ገሊላና ደበረ ሲና የሚባሉት ደሲያት የሚገኙ ሲሆን በምስራቅ በኩል ደግሞ ደብረ ጽዮን፣ አብርሐምና ጌቱሰማኒ ይገኛሉ።

በዝዋይ ሀይቅ ከሚገኙት ደሲያት መካከል ትልቁ ደብረ ጽዮን እንደሆነ Henze (1973፣75) ይገልጻሉ። ደብረ ጽዮን በሀይቁ ውስጥ ካሉት ደሲያት ከየትኛውም ቦታ ላይ የሚታይ መሆኑ ልዩ ያደርገዋል። ደብረ ጽዮን ከአምስቱ ደሲያት መካከል ትልቁና ታሪካዊ ከመሆኑ ባሻገር የአክሱም ቀሳውስት በዮዲት ጉዲት የጭፍጨፋ ዘመቻ ወቅት ታቦተ ጽዮንን ይዘው በመሰደድ በዚሁ ደሴት ለ40 ዓመታት ተቀምጠዋል (ተስፋዬ፣

2000፣3)። መረጃ አቀባዩ መርጌታ ሰምረ ግደይም «ደብረ ጽዮን በዝዋይ ደሴቶች ውስጥ ከሚገኙት አንዱና ዋነኛው ነው። ትልቁ ደሴትም ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ታሪክና ቅርስ የሚገኝበት እንዲሁም የሃይማኖታችን መገኛ የሆነና የታሪክ አሻራ ያለበትነው።» በማለት ይናገራሉ።

## 2.3. ቋንቋና ሐይማኖት

### 2.3.1. ቋንቋ

የዛይ ማህበረሰብ በእለት ተእለት ግንኙነታቸው የሚጠቀሙበት ቋንቋ ዛይኛ ይባላል። ቋንቋው ከግዕዝ፣ ከአማርኛ፣ ከትግርኛ እንዲሁም ከጉራጊኛ የተውጣጣ እንደሆነና በርካታ የኦሮምኛ ቃላትንም በውስት ማካተቱን ተስፋዬ (2000፣6) ይገልጻል። የዛይኛ ቋንቋ ተናጋሪ ብዛትን የያዘ መረጃ ማግኘት ባይቻልም እነ Jordan (2011፣4) 4880 የሚሆኑ ሰዎች በአፍ መፍቻነት ዛይኛ ቋንቋን እንደሚናገሩ ይገልጻሉ። የዛይኛ ቋንቋ ከደቡብ ኢትዮ ሴማቲክ በተለይም ከምስራቅ ጉራጌ የቋንቋ ቤተሰብ እንደሚመደብ እንደሻው (2007፣3) ያስረዳል።

### 2.3.2. ሐይማኖት

በደሴቱ ላይ የሚገኙት የዛይ ማህበረሰብ ሙሉ በሙሉ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ናቸው። የማህበረሰቡ አባላት የእለት ተእለት ህይወታቸው፣ ስለ ዓለም ያላቸው አመለካከት እንዲሁም ስነምግባራቸው ሳይቀር የተቀረጸው በዚሁ ሀይማኖት መሆኑን ዘሪሁን (2001፣22) ይገልጻል።

ቀደም ሲል ወደ ደሴቱ የመጡት የማህበረሰቡ አባላት በእያንዳንዱ ደሲያት ላይ አንድ አንድ ታቦት ማስቀመጣቸውንና ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ያላቸው ቀናኢ አመለካከትም የቆየ እንደሆነና ደብረ ጽዮን ደሴት «ንጽህት የኦርቶዶክስ እምነት የሚመለክባት ነች» በማለት መረጃ አቀባዩ መምሬ ገ/መስቀል ሂርጳ ገልጸውልኛል። የዛይ ህዝብም ሀይማኖታዊ ታሪኩን በደሴቱ ላይ ከሰፈረበት ታሪክ ጋር አጣምሮ የሚመለከት ነው።

ዘሪሁን የማህበረሰቡ አባላትና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖት ትስስርን አስመልክቶ «የዛይ ማህበረሰብ አባላት ለኦርቶዶክስ እምነት የተሰጡ ናቸው፤

መለያቸውም ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት መስጠት ነው» ይላል። በደሴቱ ላይ የሰፈሩት ህዝቦች ስለ እምነታቸው ሲናገሩ በኩራት ነው። ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ መሆናቸውንና ፕሮቴስታንትና ሙስሊም በመካከላቸው አለመኖሩ እንደ ንጽህና ይቆጥሩታል፤ በዚህም የህይማኖቱን ንጽህና ለማሳየት ይጠቀሙበታል በማለት አስፍሯል።

## 2.4. የህዝብ ብዛት እና ኢኮኖሚ

### 2.4.1. የህዝብ ብዛት

የዛይ ማህበረሰብን የህዝብ ብዛት በሚመለከት መረጃ ማግኘት አልተቻለም። ሆኖም የማህበረሰቡ ብዛት ከ13-15000 እንደሚገመት ተስፋዬ (2000፣6) ያስቀመጠ ሲሆን መረጃ አቀባዬ መምሬ ገ/መስቀል ሂርጳ ደግሞ በደብረ ጽዮን ደሴት ላይ ብቻ 200 ገደማ አባወራዎች በአጠቃላይ ከ900-12000 የሚገመቱ ሰዎች እንደሚገኙ ነግረውኛል።

### 2.4.2. ኢኮኖሚ

የዛይ ማህበረሰብ የአሳ ምርትን እንደዋነኛ የኢኮኖሚ መሰረቱ ሲጠቀምበት ቆይቷል። አሳ ለማህበረሰቡ የህልውና መሰረቱ ነው። መረጃ አቀባዬ መምሬ ዘርአጽዮን ሀ/ማርያም በዝዋይ ሀይቅ ላይ ቢልጪ፣ ቆሮሶ፣ ኬንያና አምባዛ ተብለው የሚጠሩ የተለያዩ የአሳ ዝርያዎች መኖራቸውን ይናገራሉ። ቆሮሶ እየተባለ የሚጠራው የአሳ ዝርያ በማህበረሱ ዘንድ ለምግብነትና ለገቢ ምንጭነት ተፈላጊ መሆኑን (Henze 1973፣ 76 ዘሪሁን፣ 2001፣ 22) ይገልጻሉ።

በዛይ ማህበረሰብ ደሴት ውስጥ የሚታረሰው መሬት አነስተኛና ድንጋያማ ቢሆንም እንደ አንድ ኢኮኖሚ መሰረትነት ግን ግብርናም ተፈላጊ ነው። ቀደም ሲል በደሴቱ ውስጥ ጤፍ፣ ዳጉሳ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ጥጥና ምስር ይመረቱ የነበሩ ሰብሎች ሲሆኑ በተለይ ዳጉሳ በማህበረሰቡ ዘንድ ተወዳጅነት ያለው መሆኑን ተስፋዬ(2000፣32) ይናገራል። በማህበረሰቡ ዘንድ የአሳ ምርት ሲከናወን የነበረው ከሰብል ምርት ቀጥሎ ሲሆን አሁን አሁን ግን አማራጭ በማጣት የማህበረሰቡ አባላት ፊታቸውን ወደ ሰብል ምርት በማዞር ጤፍና በቆሎን እንደ ዋና የምግብ ምንጭነት ይጠቀሙበታል።

## ምእራፍ ሶስት

## ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምእራፍ ቃላዊ ዝርው ተረክን አስመልክተው የተለያዩ ምሁራን ያነሷቸው ሀሳቦች ይቀርባሉ። እንዲሁም ለጥናቱ መተንተኛ የተመረጠው ንድፈ ሀሳብና ከዚህ ጥናት ርዕስ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶች ተዳስሰው ያላቸው አንድነትና ልዩነት ይቀርባል።

### 3.1. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

የፎክሎር ባለሙያዎች ፎክሎር የሚለውን ጽንሰ ሃሰብ በተለያየ መንገድ ለመግለጽ የሚሞክሩ ቢሆንም ቀጥተኛና ጥቅል የሆነ ብያኔ ከመስጠት ይልቅ በዘርፉ ሊጠኑ የሚችሉትን ዘውጎች ይዘረዝራሉ (Sims 2005:9፣ ፈቃደ፣ 1991፣3)። ምክንያቱም በዘርፉ የሚገኙ ጉዳዮች እንደ አካባቢው ተፈጥሯዊ ሁኔታና እንደ የማህበረሰቡ ገጠመኝ፣ እምነት፣ እሴትና አመለካከት የተለያዩ በመሆናቸው ነው።

የፎክሎር ባለሙያዎች ቀስ በቀስ ፎክሎርን በዘውጎች አማካኝነት መከፋፈልና ማደራጀት ለፎክሎር ጥናት የተሻለ አማራጭ እየሆነላቸው መጥቷል። Sims (2005:13) ፍክሎርን ለመግለጽ ሁልጊዜም የምንጠቀምበት ቃላዊ፣ ቁሳዊና ልማዳዊ የተባሉ ክፍሎች መኖራቸውን ጠቁመው እነዚህ ሰፊ የሆኑ ክፍሎች በስራቸው በርካታ የፎክሎር ዘውጎችን እንደሚያካትቱ ይገልፃሉ።

Dorson (1972:3) የፎክሎርና የፎክ ላይፍ ጥናት ስነቃል (Oral Literature)፣ ቃላዊ ጥበብ (Verbal Art)፣ ቁሳዊ ባህል (Material Culture)፣ ሀገረሰባዊ ልማድ (Social Folk Custom) እና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት (Performing Folk Arts) ተብለው በአራት ሰፋፊ ክፍሎች እንደሚመደቡ ይናገራሉ።

የዘርፉ ምሁራን ግን ከፎክሎር አይነቶች መካከል በአንዱ ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ ጥናትን ማከናወን እንደሚገባ ይመክራሉ። ምክንያቱም በአንዱ የፎክሎር ዘውግ ውስጥ ሌላ የፎክሎር ዘውግ ሊገኝ ይችላል። ይህን አስመልክተው Sims (2005:17) Tolkenን በመጥቀስ የፎክሎር ዘውጎች አንዱ በአንዱ ውስጥ ሊገኝ ይችላል ይላሉ። በመሆኑም ይህ

ጥናት ከስነ ቃል ክፍሎች መካከል አንዱ በሆነው በቃላዊ ዝርው ተረክ ላይ ትኩረቱን ያደርጋል።

## 3.2. ቃላዊ ዝርው ተረክ

ቃላዊ ዝርው ተረክ የስነ ቃል አንዱ ክፍል ሲሆን ግጥማዊ ባልሆነ መልክ በቃል የሚተረክ፣ ተለጣጣቂነት ወይም ተከታታይነት ያላቸው ድርጊቶችና ሁነቶች የሚፈፀሙበት፣ የድርጊቱ ተሳታፊ የሆኑ ገፀ ባህሪያት የሚገኙበት እንዲሁም ድርጊቱ የሚፈጸምበትን ቦታና ጊዜ የሚያመለክት ታሪክ ነው Oring (1986:122) ይላሉ። Degh (1972፡58) በበኩላቸው ግጥማዊ ባልሆነ መልኩ የሚቀርብ ማንኛውም የስነቃል አይነት ቃላዊ ዝርው ተረክ ይባላል በማለት ይገልፃሉ ።

ተረክ ጥንታዊ፣ የሰው ልጅ የጽሁፍ ጥበብ ከመጀመሩ በፊት ጀምሮ የነበረ ሲሆን እያንዳንዱ ማህበረሰብ ስለአለም አፈጣጠር፣ ስለነገሮች አመጣጥ፣ ስለእምነቱ፣ ስለባህሉ፣ ስለማንነቱ ወዘተ ለመግለጽ ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ነው። Degh (1972:66) የተረክ ጥንታዊና ለሰው አዕምሮ ቅርብ መሆኑን ሲገልጹ «ተረክ ረጅም ዘመንን ያስቆጠረ፣ ለሰው ስሜት ቅርበት ያለው፣ተደማጭነት ያለው እና ከስልጣኔ ጋር አብሮ የሚጓዝ ነው» በማለት ነው።

በሌላ መልኩ Cormick (2011:772) ቃላዊ ዝርው ተረክን አስመልክተው በሰው የተፈጠረና ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የሚተላለፍ፣ ስላልተለመዱ ነገሮች ወይም እንግዳ ስለሆኑ ጉዳዮችና ስለ ልእለ ተፈጥሮ የሚያወሱ ተረኮችን በማንሳትና ከነባራዊው አለም ጋር በማስማማት ከተናጋሪ ወደ አድማጭ ለማስተላለፍ የሚያግዝ ነው ይላሉ።

ከዚህ በመነሳትም ቃላዊ ዝርው ተረክ የማህበረሰብና የግለሰብ መገለጫ የሆነ፣ በዝርው የሚቀርብ፣ የድርጊቱ ተሳታፊ ገጸ ባህሪያት ያሉት፣ ድርጊቱ የሚፈጸምበትን ቦታና ጊዜ የሚያመለክት፣ ረጅም ዘመን ያለውና ለሰው ስሜት ቅርብ የሆነ፣ ከሰው አእምሮ በላይ የሆኑ ነገሮችን ከነባራዊው አለም ጋር በሚስማማ መልኩ የሚያቀርብ የስነ ቃል ክፍል ነው ማለት ይቻላል።

ቃላዊ ዝርው ተረክን አስመልክተው ፈቃደ (1991፣20) ቃላዊ ዝርው ተረኮች የአንድን ማህበረሰብ ወይም ቡድን የአኗኗር ስርአት፣ የአበላል፣ የአለባበስ፣ የአነጋገርና የአካሂያድ ስርአት ያስተምራሉ፤ በዚህ ምክንያትም ህልውናቸው ተጠብቆ እንዲቆዩ ሆኗል ይላሉ። Oring (1986:133) ደግሞ ተረክ የማህበረሰብ እና የግለሰብ መገለጫ ሲሆን ሰፋ ያለውን የሰው ልጅ አስተሳሰብና ስሜት ያንጸባርቃል በማለት ይገልፃሉ።

ቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ላዩን ያላቸውን ትርጉም ብቻ በመመልከት የሚተዉ ሳይሆኑ የአንድን ማህበረሰብ ወይም ቡድን አይነኬ ባህልና ልማድ ጸንተው እንዲቆዩ በማድረግ እንዲሁም የተፈጥሮንና የፍጥረታትን ምንነት በመግለጽ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ምግባሮች ወደ ቀጣዩ ትውልድ በማስተላለፍ በኩል ከፍተኛ ሚና እንደሚ ጫወቱ Bascom (1964:21)ይገልጻሉ።

Prince (2007:11) ደግሞ ተረክ ቢያንስ የአንድ ሁነት (ለውጥ) ወካይ ተደርጎ ይወሰዳል በማለት ያስረዳሉ። Fludernik(2009፡1) ተረክ በሁሉም አካባቢ የሚኖርና በማንኛውም ሰው በየትኛውም አጋጣሚ ስለአንድ ነገር የሚተረክ እንደሆነ ይናገራሉ።

Oring (1986፣123) ሀገረሰባዊ ተረክ በሁሉም የስልጣኔ ደረጃ ላይ የሚገኙ ህዝቦች መገለጫ እንደሆነ ሲያስረዱ ተረክ ያልሰለጠነ ህዝብ ወይም የገበሬ ብቻ ሳይሆን በየትኛውም የስልጣኔ ደረጃ ላይ የሚገኝ የህብረተሰብ ክፍል መገለጫ ነው በማለት ያስረዳሉ። የOringን ሀሳብ በሚደግፍ መልኩ ፈቃደ (1991፣52) ተረክን አስመልክተው ሲገልጹ በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ያለ፣ በእለታዊ ህይወት በተለያየ መልክ የሚከወን ጉዳይ ነው በማለት ነው። Degh (1972:54) ደግሞ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ እንደሚነገሩና በየትኛውም አካባቢና ማህበራዊ ሁኔታ ሊቀርቡ እንደሚችሉ ያስረዳሉ።

Oring (1986:133) ጠቅለል አድርገው ተረክ የማህበረሰብና የግለሰቦች መገለጫ ሲሆን ሰፋ የለውን የሰው ልጅ አስተሳሰብና ስሜት ያንፀባርቃል በማለት ይገልጻሉ።

Bascom (1996:3-4) የቃላዊ ዝርው ተረክ አይነቶችን ሚት (Myth)፣ አፈታሪክ (Legend) እና ተረት (Folk tale) በማለት ይከፋፍሉታል። ይህን አከፋፈል ግን Ben Amos (1992፡101-102) አይቀበሉትም። እንደ Ben Amos አገላለጽ ቃላዊ ዝርው ተረክን ሚት፣ ሊጀንድና ተረት ብሎ መክፈል አለማቀፋዊ እንዳልሆነና የተለያዩ

ማህበረሰቦች ተረክን የሚከፍሉበት መጠንና አይነት ይለያያል ይላሉ። ከዚህ ሌላም የአንድ ቃላዊ ዝርው ተረክ መለያ ባህሪያት አድርጎ ለመመደብ ባህላዊ አስተሳሰቡ፣ አላማው፣ ስልቱና የተረኩ ትርጉም መታየት አለበት፤ ምክንያቱ ደግሞ ከባህል ባህል የሚለያዩ ብቻ ሳይሆኑ በጊዜ ሂደት በአንድ ህብረተሰብ ውስጥም መልካቸውን ሊቀይሩ የሚችሉ ናቸው ይላሉ።

Oring (1986:123) ቃላዊ ዝርው ተረክ የተለያዩ ባህሪያት እንዳሉ ይገልጻሉ። ከባህሪያቶቹ መካከል አንደኛው ቃላዊ ዝርው ተረክ የተለያዩ ቅጂዎች ሊኖሩት ይችላሉ የሚለው ነው። Oring የተለያዩ ተራኪዎች በተለያየ ሁኔታ ውስጥ ሲተረኩት ተረኩ ሊቀያየር ስለሚችል ቀዳሚው ይህ ነው ማለት አይቻልም ይላሉ። ሁለተኛው ባህሪ ደግሞ ቃላዊ ዝርው ተረክ በተተረከ ቁጥር እንደ አዲስ እየተፈጠረ የመሄድ ባህሪ አለው በማለት ያስቀመጡት ነው።

በሌላ በኩል የአንድን ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ለማጥናት ሲፈለግ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ነገሮችን አስመልክቶ Degh (1972:54) ተረኮቹ የሚያስተላልፉት መልእክት ምንድነው? ለተረኮቹ መፈጠርና መነገር ምክንያት የሆነው ጉዳይ ምንድነው? የተረኩ ባለቤቶችና ታዳሚዎች ተረኮቹን እንዴት ይመለከቷቸዋል? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት እንደሚገባ ይገልጻሉ።

### 3.3. ተግባራዊ አቀራረብ (Functional Approach)

በዛይ ማህበረሰብ ቃላው ዝርዊ ተረክ ላይ ትኩረቱን ያደረገው ይህ ጥናት መሰረት ያደረገው ተግባራዊ አቀራረብን ነው። ተግባራዊ አቀራረብ (Functional Approach) የአንድን ማህበረሰብ ስነቃል ፋይዳ ለመተንተን የሚያገለግል ሲሆን ለጥናቱ የተመረጠው ማህበረሰቡ ተረኮቹን ለምን ተግባር ያውላቸዋል? ተረኮቹ ለማህበረሰቡ አባላት የሚሰጡት ፋይዳ ምንድ ነው? እንዲሁም ማህበረሰቡ ተረኮቹን ለቀጣዩ ትውልድ የሚያስተላልፍበት ምክንያት ምንድነው? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት ይሞክራል።

Sims (2005:175) ተግባራዊ ጥናት የአንድን ቡድን ቃላዊ፣ተለምዷዊና ዕሁፋዊ ሰነዶች በመመርመር ሰዎች እነዚህን ጉዳዮች ለመጋራት ካላቸው ጥቅም አንፃር ለምንና

እንዴት በሚሉ ጥያቄዎች አማካኝነት ፊትሽ ተግባራቸውን የሚያሳይ ነው በማለት ይገልጻሉ።

በፎክሎር ተግባራት ጥናት ዙሪያ ተጠቃሽ ከሆኑት ምሁራን መካከል Bascom (1965:290-294) ይገኛሉ። እኝህ ምሁር ፎክሎር አራት ተግባራት እንዳሉት ይገልጻሉ። ተግባራቱም የማዝናናት፣ የባህልን ተገቢነት መግለጽ፣ የማስተማር እና የመቆጣጠር መሆናቸውን አስፍረዋል።

ባህልና ልማድ በሰው ልጅ ላይ ከጫነበት ደንብ፣ እንዲንቀሳቀስ ከወሰነበት ቁሳዊ የባህል ድንበር በተለያዩ ፎክሎሮች በመዝናናት የሚያመልጥበት ስልት ነው Bascom(1965)።ፈቃደ (1991፣18) ስነቃሎች አስደሳች የሆነ ምናባዊ አለምን በመፍጠር የሰው ልጅ በእለት ተእለት ኑሮው ከሚያጋጥመው አድካሚና አሰልቺ ህይወቱ ለጊዜውም ቢሆን እፎይታን እንዲያገኝ ይጠቅሙታል በማለት ይገልፃሉ። ፎክሎር ለየትኛውም ቡድን በተለይም የጽሁፍ ጥበብ ባልዳበረበት ማህበረሰብ ውስጥ የጎላ የማስተማር ሚና አለው። ፎክሎርን የሚፈጥረው ማህበረሰብ የተለያዩ የስነ ቃል ቅርጾችን በመጠቀም የህጻናትን አእምሮ በትምህርት ለማጎልበት፣ ወጣቶችን በስነ ምግባር ለማነጽ ባጠቃላይ የማህበረሰቡን እሴት በአባላቱ ውስጥ ለማስረጽ እንደሚጠቀምበት Bascom (1965: 293-294) ያስረዳሉ።

እንደ Bascom አገላለጽ ፎክሎር የተራቆንና የአድማጩን ማህበረሰብ ባህል ጠቃሚነት የመግለጽ፣ የመንፈሳዊ ተቋማቱንና የመንፈሳዊ ስርአቶቹን ተገቢነት የማረጋገጥ ተግባርን እንደሚጫወት ያስረዳሉ። ከማህበረሰቡ እምነትና አመለካከት ወይም ስምምነት የሚያፈነግጡ ግለሰቦች ላይ ጫና ለማሳደሪያነትና ለመቆጣጠሪያነት የሚያገለግል ነው ይላሉ።

ፈቃደ (1991፣7) በበኩላቸው የስነ ቃል አጠቃላይ ተግባር በአምስት አበይት ክፍሎች ማየት እንደሚቻል ይገልጻሉ። እነሱም የመግለጥ ተግባር፣ የማጠናከርና የመትከል ተግባር፣ የማምለጭ ተግባር፣ የማስተማር እንዲሁም የመግታት-የመቆጣጠር ተግባር ናቸው ይላሉ።

Ben Amos (1992: 114) የተረክ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ተረኩ ለማህበረሰቡ በሚሰጠው ፋይዳ ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል ይላሉ። ተግባራዊ ትንተናም መሰረት

የሚያደርገው ምልከታንና ተረኩን በመውሰድ ትርጉሙን በመተንተን ላይ እንደሆነ ያስረዳሉ። ተረኩ በማህረበሰቡ ውስጥ ያለውን የእስተማሪነት ሚና ለመገንዘብ ተረኩ በሚነገርበት ወቅት የነበረውን እውነታና የተረኩን ጭብጥ በሚገባ መመርመር ያስፈልጋል በማለት ይገልጻሉ። እንደ Ben Amos ገለጻ በተረኩ ተግባር አማካኝነት በሰዎች አእምሮ ውስጥ የሚያስከትለውን ፍርሃትና ጭንቀት ለመረዳት ማህበረሰቡ ለተረኩ የሚሰጠውን ትርጉም ከመረዳት ይልቅ በምልከታ ላይ የተመሰረተ ትንተና ሊካሄድ ይገባል ይላሉ።

በሌላ በኩል Oring(1986:68) የተግባራዊ ንድፈ ሀሳብን አስመልክተው የዘርፉ ምሁራን ፎክሎር ለሚፈጥረውና ለሚገለገልበት ማህበረሰብ ምን ትርጉም ይሰጠዋል? ወይም ምን መልእክት ያስተላልፍለታል? የሚለውን ጥያቄ በማንሳት ዘረፉ በአንድ ማህበረሰብ ወይም ቡድን ውስጥ ያለውን ተግባር ለማወቅ ይመረምራል በማለት ይገልፃሉ።

## 3.4. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ክፍል ተረክን ርእሰ ጉዳያቸው አድርገው ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በውጭ ቋንቋዎች እና በኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተሰሩ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ርእሰ ጉዳይ ጋር ቅርበት ያላቸው በመሆናቸው ይዳሰሳሉ። ከዚህ ጥናት ጋር በርእሰ ጉዳይ ጋር ተዛምዶ አላቸው ያልኳቸው ጥናቶች የሚከተሉት ናቸው። አብርሃም አለሙ "Jimma Ormo Oral Prose Narrative: A preliminary descriptive analysis" (2000 G.C) ባይለየኝ ጣሰው "An Ayuaa, Oral Prose Narrative: Ethnic Geners and Social Functions" (1999 G.C) ይሄነው ጀንበር "Generic classification of Amharic oral prose narratives of west Gojjam (1996 G.C) ሳህሉ ኪዳኔ፣ "Borana Oromo prose Narratives፡ A contextual study" (G.C 1996)፣ መልእክነህ መንግስቱ "The major themes and motif of southern Agaw folktales (1990 G.C) ፣ ተስፋዬ ገ/ማርያም፣ "A Study of Major Themes in Jablawi Folktales" (1990 G.C) አብዱል ቃድር ሀጂ ጃማ "Some Cultural Elements as Reflected in Somalia Folktales" (1982 G.C)። ሲሆኑ በኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ደግሞ የተሰሩት ቀጥሎ የሚቀርቡት ናቸው።

ከሁሉም በላይ «የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች እና ባህላዊ ስርዓቶች ጥናት» (2004 ዓ.ም) ምንዳ ገብሬ «የጌድኦ ልማዳዊ ሥርዓትና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው» (2000 ዓ.ም) ማን ያለው አባተ «የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው»(1999 ዓ.ም) አማረ ሞላ «የሸካቾ ብሔረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች ምደባ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና» (1999 ዓ.ም) የሚሉ ናቸው።

ይህ ጥናት የተሰራበት ማህበረሰብ ላይ በተለያዩ ትምህርት ክፍሎች የተሰሩ የሁለተኛና የመጀመሪያ ዲግሪ ጥናቶች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

በስነ ልሳንና በሶሲዮሎጂ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ የተሰሩ ጥናቶች እንደሻው ወ/ሚካኤል "A study of the Ethno linguistic Attitudes of Zay People: An investigation of the Language Ethnicity Relationship Among Zay" (2007) አምባው ደምሴ "The Phonolgy of Zay: Generative Approch" (1990) ጌቱ ሽኩር "Morphology of Zay" (1999) እንዲሁም በሶስዮሎጂ ዘሪሁን ዶዳ "Culture, Belife and Mental Illness Among Zay" (2001).

በታሪክና በስነ መለኮት ትምህርት ክፍል ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶች ተስፋዬ ኤዴቶ "Socio- Economic Life of the Zay with Especial Emphasis on the Fishing Industry" (1988) ቱማ ናዳሞ "The History of the Zay in the 19th and Early 20th Centuries" (1982) በስነ መለኮት ትምህርት ክፍል ዘላለም አሰፋ "A Brief History and Activities of Zeway Debre Tsion Monastery." (2001) የሚሉ የጥናት ስራዎች ናቸው።

እነዚህ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው በመሆናቸው በአካባቢው ላይ ማን ምን ሰራ የሚለውን መረጃ ለማሳየት ብቻ ጠቅሻቸዋለሁ። ምክንያቱም የእኔ ጥናት ምን ክፍተት ሞላ የሚለውን ለማሳየት ያስችለኛል ብዬ ነው።

ስለዚህ ከዚህ ጥናት ጋር በርእሰ ጉዳይ ቅርበት አላቸው ያልኳቸውን ጥናቶች በተሰሩበት ትምህርት ክፍል በመከፋፈልና ከቅርብ ጊዜ በመጀመር በቅደም ተከተል እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

የሚመረምር በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ሲሆን አካባቢያዊ ምደባን መሰረት በማድረጉ ልዩነት አለው።

ሳህሉ ኪዳኔ "Borana Oromo prose Narratives፡ A contextual study" (G.C 1999) በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ሲሆን የጥናቱ አላማም የተጠኚውን ማህበረሰብ ተረኮች ሰብስቦ የሚገኙበትን ሁኔታ በመግለጽ አይነታቸውን ማሳየት እንደሆነ አስፍሯል። ሳህሉ ከመሰከ የሰበሰባቸውን 74 የሚሆኑ ተረኮችን የአካባቢውን መጠሪያ በመጠቀም «ዱሪ ዱሪ»፣ «ማማክሳ» (የአዋቂዎች ተረቶች) እና «አርጋጌቱ» (ሚቶች እና ታሪኮች) በማለት በሶስት ክፍሎ አስቀምጧቸዋል። አጥኚው በአካባቢው መጠሪያ መሰረት የከፈላቸውን ተረኮች ጭብጥ፣ ገፀባህሪያትንና ቋንቋን መሰረት በማድረግ ትንታኔ ሰጥቶባቸዋል። ለስነ ቃል ጥናት በጥቅም ላይ ከሚውሉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካከል አንዱ ቃለ መጠይቅ እንደሆነ (Goldstein, 1964:76 Dorson,1972: 407-425) ቢታወቅም አጥኚው ግን ቃለ መጠይቅ ማድረግ አለማድረጉን አልጠቆመም። የሳህሉን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር አንድ የሚያደርገው በቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ማተኮሩ ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ የእኔ ጥናት የዛይ ማህበረሰብ ዝርው ቃል ተረኮች ላይ የይዘት ትንተና በማድረግ የተረኮቹን ማህበራዊ ፋይዳ የሚመረምር ሲሆን የሳህሉ ጥናት ግን የቦረና ኦሮሞ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በአውዳዊ አገባብና በዘውግ የሚመድብ መሆኑ ነው።

ይሂነው ጀንበር "A Generic Classification of Amharic oral prose Narratives of west Gojjam" (G.C 1996) በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ ዓላማ በምዕራብ ጎጃም የሚገኙትን ቃላዊ ዝርው ተረኮች መሰበሰብና መመደብ ነው። የአመዳደብ ስልቱ ተጠኝ ማህበረሰቡ ለተረኮቹ ያላቸውን አመለካከት፣ የአተራረክ ስልታቸውን፣ የገፀባህሪያቱን አቀራረፅ መሰረት በማድረግ እንደሆነ ገልጿል። የምደባው ስልት ተጠኝ ማህበረሰቡ ለተረኮቹ ያላቸው አመለካከትን፣ የአተራረክ ስልታቸውን፣ የገፀ ባህሪያቱን አቀራረጽ መሰረት ያደረጉ ናቸው። ይህነው ከመስከ የሰበሰባቸውን 140 ተረኮች የሀገረሰብ ተረቶች፣ አፈታሪኮችና ዘር ቆጠራ (genealogy) በማለት በሶስት ምድብ ከፍሎ አስቀምጧቸዋል። ተረቶች በየትኛውም የዕድሜ ክልል በሚገኙ የማህበረሰቡ አባላት የሚነገሩ ሲሆኑ፣ አፈታሪኮችና ዘር ቆጠራዎች ግን በእድሜ ባለፀጎች እንደሚቀርቡም

አስፍሯል። አጥኚው በሁሉም ባህሎች ውስጥ ያሉትን ሀገረሰባዊ ተረቶች ለመመደብ ወጥ የሆነ ህግ ስለሌለ አስቸጋሪ እንደሆነም ጠቅሷል።

መላክነህ መንግስቱ "The major Themes and motifs of southern Agew Folk tales" (G.C 1990) በሚል ርእስ ጥናቱን ለውጭ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ አቅርቧል። የመላክነህ ጥናት አላማዎች የደቡብ አገው ህብረተሰብ ተረቶች ያላቸውን ስነ ፅሁፋዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ መመርመር፣ ተረቶች በብሔረሰቡ ማህበረ ባህላዊ አካባቢ የሚጫወቱትን ሚና መወሰን፣ የህዝቡን ስነ ልቦናዊ፣ ስነ ምግባራዊ፣ኪናዊ አመለካከትና እምነት ማሳየት እንዲሁም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ግቡን እንዲመታ ጥናቱ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያበረክታል የሚሉ ናቸው። አጥኚው ትኩረትም የደቡብ አገው ሀገረሰብ ተረቶች ማህበረ ባህላዊ ጠቀሜታቸውን በጭብጣዊ ትንተና ስልት መመርመርና ዋናዋና የሚባሉ የመባያ/Motifs/ ጉዳዮችን መለየት የጥናቱ ትኩረት አድርጎ አስፍሯል።

መላክነህ ከመስክ የሰበሰባቸውን 60 ተረቶች ዋናዋና ጭብጦችን በሁለት ምድቦች የመባያ ጉዳዮችን ደግሞ በ12 ምድቦች ክፍሎ አስቀምጧል። አጥኚው ተረቶቹ ተደጋጋሚ ጭብጥ እንደሚታይባቸው ያስፈረ ሲሆን ተረቶቹ ወጣቶች አካላዊና አእምሮአዊ ችሎታቸውን በማሳደግና ሰብእናቸውን ለመቅረጽ እንደሚያገለግሉ አስፍሯል።

ተስፋዬ ገ/ማርያም "A Study of major Themes in Jablawi folktales" (G.C 1990) በሚል ርእስ ጥናቱን ለውጭ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ አቅርቧል። ተስፋዬ የጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው የጀብላዊ ሀገረሰብ ተረቶችን ጭብጥ በመተንተን የብሄረሰቡን አመለካከት፣ እምነትና እሴት በማድነቅ ማህበራዊ ትርጉማቸውን ለመወሰን ይረዳል የሚሉ አላማዎችን ይዟል።
አጥኚው 115 ተረቶችን ከመስክ መሰብሰቡን የገለጸ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ 72ቱን በ25 ጭብጦች ለይቶ ትንታኔ ሰጥቶባቸዋል። የተረቶቹ ጭብጦች ብቀላን፣ ስስታምነትን፣ ምቀኝነትን፣ ሞኝነትን፣ ደደብነትን፣ ስንፍና፣ ትእግስትን፣ ጨካኝነትን፣ አንድነትን፣ እውነትንና ፍትህን የሚሉ ርእስ ጉዳዮች ላይ ያተኩሩ መሆናቸውን አስቀምጧል። ከዚህ ሌላ ሚቶችን፣ አፈታሪኮችን፣ ፌብሎችን፣ የጀብላዊ ሀገረሰብ ተረቶች ስር ሊጠቃለሉ የሚችሉ ናቸው በማለት አስፍሯል።

አብድል ቃድር ሐጂ "Some Cultural Elements as Reflected in Somali Folktales" (G.C 1982) በሚል ርእስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍለ ትምህርት ጥናቱን አቅርቧል። አጥኚው የጥናቱን አላማ ያደረገው የሶማሌን ተረቶች ሰብስቦ በማጥናት የሶማሌን ማህበረሰብ ባህላዊና ስነ ልቦናዊ ገጽታዎች ማሳየት የሚል ነው። አጥኚው ከመስክ የሰበሰባቸውን ሰማንያ ሁለት ተረቶች በስምንት መድቦ ተንትኗል። ምደባን በሚመለከት በስነ ቃል ተረቶችን በይዘት መመደብ የተለመደ እንደሆነ የጠቀሰ ሲሆን አመዳደቡ በተረቶቹ ውስጥ ጎልቶ የሚታየውን ጭብጥ መሰረት ያደረገ መሆኑን ጠቁሟል ( ገጽ፣ 35)። አጥኚው በይዘት ያነሳቸው ብልህነትን፣ ጥበበኝነትን፣ ፍትህን፣ ሀይማኖትና ስነ ምግባርን፣ ጋብቻንና ሴቶችና ቅናትን የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን አስፍሯል። አብድል ቃድር መረጃ ለመሰብሰብ የመረጠው በሶማሌ ካምፕ ውስጥ ነው(1982፣23)። በካምፕ ውስጥ የሚኖሩ የሶማሌ ስደተኞች ደግሞ ሁሉንም የሶማሌ ማህበረሰብ ሊወክሉ ስለማይችሉ በመረጃ አሰባሰብ ረገድ ክፍተት ያለበት ይመስለኛል።

### 3.4.2 . በኢትዮጵያ ስነ ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተሰሩ ጥናቶች

ከሁሉም በላይ «የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች እና ባህላዊ ስርዓቶች ጥናት» (2004 ዓ.ም) በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቷን አቅርባለች። ከሁሉም ለጥናቷ አላማ አድርጋ የተነሳችው የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ለማህበረሰቡ አባላት ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ መመርመር፣ በማህበረሰቡ ውስጥ በሚነገሩት ቃላዊ ዝርው ተረኮች የማህበረሰቡ ስያሜ፣ አመጣጥ፣ የስራ ባህልና እምልኮ እንዴት እንደተገለፁ ማሳየት፣ የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹንና ባህላዊ ስርዓቶቹን ለአዲሱ ትውልድ የሚያስተላልፍበት ምክንያት መመርመር፣ በቃላዊ ዝርው ተረኮቹና በባህላዊ ስርዓቶቹ የሚተላለፉ ጉዳዮች መተንተንና የማህበረሰቡ አባላት በባህላዊ ስርዓቶቹ ላይ ያላቸው አመለካከት መፈተሽ የሚሉ ናቸው።

አጥኚዋ በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚነገሩት ቃላዊ ዝርው ተረኮች መካከል የማህበረሰቡ ስያሜ በሚመለከት የተወሰኑት ከአመጋገብ ስርዓታቸው፣ ከነገዱ አባት ስም፣ ከስራ ባህላቸውና በአካባቢው ካለ የእህል ፍሬ መጠሪያ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ማወቅ ማቻሏን ጠቅሳለች። በተለይ ከአመጋገብ ስርዓታቸው ጋር ተያይዞ የተሰጠው ስያሜ አመጣጡ ከሌላው የአካባቢው ማህበረሰብ ሊሆን እንደሚችልና ተጠኝ ማህበረሰቡን ዝቅ አድርጎ ለማሳየት የተጠቀመበት እንደሆነ ጥናቱ አመላክቷል በማለት አስፍራለች። ባህላዊ ስርአቶችን በሚመለከት ደግሞ ተጠኚው ማህበረሰቡ ከሌላው የአካባቢው ማህበረሰብ በተለየ ሁኔታ የአምልኮ፣ የግርዛትና የሰርግ ስርዓት እንዳለውና አምልኮታዊ ስርዓቱ የማህበረሰቡ አባላት ከጣና ሀይቅ እና ከአባይ ወንዝ ጋር ባላቸው የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ከወንዙ አስተዳዳሪ ወይም ከአቢናዝ ችግር እንደማይገጥማቸው እና አቢናዝ እገዛ እንደሚያደርግላቸው እንዲያምኑ የማድረግ ተግባር አለው በማለት በጥናቷ ማጠቃለያ ላይ ገልጻለች።

የከሁሉምን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ማህበራዊ ፋይዳ ላይ ትኩረት ማድረጉ ሲሆን የሚለየው ደግሞ ከሁሉ በጥናቷ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹን ከባህላዊ ስርአት ጋር አጣምራ ማየቷ ነው።

ምንዳ ገብሬ «የጌድኦ ልማዳዊ ሥርዓትና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው» (2000 ዓ.ም) በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ክፍል ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቱን አቅርቧል። ምንዳ ጥናቱን ለማከናወን ዓላማ አድርጎ የተነሳው በህብረተሰቡ ልማዳዊ ስርአቶችና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው ውስጥ ምን ግንኙነቶች እንዳሉ መመርመር፣ ዝርው ቃል ተረኮቹ በሚያበረክቷቸው ማህበራዊ ግልጋሎቶች አንጻር ሲመረመሩ ይዘታቸው በምን በምን ላይ እንደሚያተኩሩ ማሳየት፣ የተረኮቹን ጎሳዊ ምደባና አካባቢያዊ ስያሜዎቻቸውን ለይቶ ማውጣት የሚሉ መሆናቸውን አስፍሯል።

ዝርው ቃል ተረኮቹን «መማጎ» እና «ጢንጎ» ተብለው እንደተሰየሙ አስቀምጦ አንድነ ትናልዩነታቸውን ተመልክቷል። «መማጎ» ሽማግሌዎችና አዛውንቶች አለመግባባቶ ችን ለመፍታት እርቅ ሲቀመጡ እንዲሁም በልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ ውይይቶችን ሲያካሂዱ ሁኔታዎችን ፈር ለማስያዝ በነገር አዋቂዎች የሚነገር መሆኑን ገልጿል። «ጢንጎ» ደግሞ በመኖሪያ ቤቶች፣ በየዛፎች ጥላ፣ በየደጃፉ ላይ፣በእረኝነት

ቦታና ሀዘን ቦታዎች የሚነገር መሆኑን አስፍሯል። ተረኮቹ በእድሜ የተገደቡ እንደሆኑና አብዛኛውን ጊዜ ከስራ ሰዓት ውጪ የሚቀርቡ መሆናቸውን አስቀምጧል።

ማን ያለው አባተ «የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው» (1999 ዓ.ም) በሚል ርእስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቱን ለኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት አቅርቧል። ማንያለው ጥናቱን በአራት ምዕራፎች ከፋፍሎ ያቀረበ ሲሆን ጥናቱን ለማከናወን ዓላማ አድርጎ የተነሳው በቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳ ላይ ገላጭ ትንተና ማድረግና የቤንች ብሔረሰብ አባላት የቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮች ናቸው ብለው የሚጠቅሷቸውን ለይቶ መግለፅ መሆኑን አስፍሯል። የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮች «ቤንችቶስ» እና «ኤሽሽ » በመባል በማህበረሰቡ እንደሚመደቡ አስፍሯል። ማንያለው የቤንች ዝርው ተረኮች ከክወና አውዳቸው (ጊዜ)፣ ከፈጠራነታቸው፣ ከታሪኩ እውነተኛነትና ከትረካው ግብ አላማ አንጻር «ቤንችቶስ» እና «ኤሽሽ » ተብለው እንደሚመደቡ አስፍሯል።

የማንያለውን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የቃላዊ ዝርው ተረኮቹን ማህበራዊ ፋይዳ የሚመለከት መሆኑ ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ የማንያለው ጥናት የተረኮቹን አካባቢያዊ ምደባ መመልከቱ ነው።

አማረ ሞላ «የሽካቾ ብሔረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች ምደባ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና» (1999 ዓ.ም) በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ አቅርቧል። አጥኚው ጥናቱን ለማከናወን ዓላማ አስርጎ የተነሳው የሽካን ብሔረሰብ ተረቶች በመሰብሰብ መድቦ ከአከናውን ስልትና ከይዘት አንፃር መተንተን እንዲሁም ተረቶቹን ሰንዶ ለመጪው ትውልድ ቅርስ ማቆየት እንደሆነ አስፍሯል። አጥኚው ሰባ አራት ተረቶችን መሰብሰቡን ያሰፈረ ሲሆን ለምደባ መሰረት ያደረገው አካባቢያዊ መጠሪያውን ነው። ይዘቱን የመደበው ደግሞ በተረቶቹ ውስጥ ያለውን ፍሬ ሀሳብ መሰረት በማድረግ ነው። የአማረን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር አንድ የሚያደርገው በይዘት ላይ ተመስርቶ ትንታኔ መስጠቱ ሲሆን የሚለየው ደግሞ የአማረ ጥናት በተረቶች ላይ ትኩረት ያደረገና የአካባቢ ምደባን የተከተለ መሆኑ ነው። ቀጥሎ ከመስከ በተሰበሰቡ የዛይ ማህረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ትንተና ይካሄዳል።

# ምእራፍ አራት

## የዛይ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ትንተና

በዚህ ክፍል የዛይ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ይዘት ትንታኔ የሚሰጥ ሲሆን ትንታኔው የሚሰጠውም ተረኮቹ ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ መሰረት በማድረግ ነው። Ben Amos ተግባራዊ ትንተና በሚከናወንበት ጊዜ በምልከታና ተረኩ ወስዶ ትርጉሙ መተንተን እንደሚቻል ባስቀመጡት ሀሳብ መሰረት ይሆናል። ተረኮቹ አካባቢያዊ መጠሪያን መሰረት ያላደረጉት ማህበረሰቡ ለቃላዊ ዝርው ተረኮቹ የሚሰጠው አካባቢያዊ ስያሜ ባለመኖሩ ነው። ከማህበረሰቡ የተሰበሰቡትን ቃላዊ ዝርው ተረኮች ጥንተ አመጣጥ፣ የዛይ ማህበረሰብና የዝዋይ ሀይቅ፣ ደብረ ጺዮን ደሴትና ቅድስና፣ ከስነ ምግባር ጋር ተያይዘው የሚተረኩ በሚል ተመድበው የተለያዩ ማንጸሪያዎችን በመጠቀም ትንታኔ ይሰጥባቸዋል። ተረኮቹ ለማህበረሰቡ አባላት ያላቸውን ፋይዳ መመርመር የጥናቱ ትንታኔ አብይ ጉዳይ ነው።

### 4.1. የዛይ ማህበረሰብ ጥንተ አመጣጥ

በዚህ ርእስ ስር ትንታኔ የሚሰጥባቸው ርእሰ ጉዳዮች የማህበረሰቡ አባላት ጥንተ አመጣጣቸውን አስመልክተው የሚተርኳቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች ናቸው። ተረኮቹ ስለዘር ሀረጋቸው፣ ከአገረ እስራኤል የመጡበትን ምክንያት እንዲሁም ከአክሱም ተነስተው ወደ ዝዋይ ደሴት ለምን ሊመጡ እንደቻሉ እንዲሁም የነገስታት ወገን ከመሆን ጋር ተያይዘው የሚተረኩ ናቸው። በዚህ መሰረትም ተረኮቹ የቀረቡትና ትንታኔ የተሰጣቸው ያእቆብና የዛይ ማህበረሰብ፣ የዛይ ማህበረሰብና እስራኤላዊነት፣ ወደ ዝዋይ ደሴት ከመምጣት ጋር ተያይዘው የሚተረኩና የነገስታት ወገን ከመሆን ጋር ተያይዘው የሚተረኩ በሚል ርእስ ተከፋፍለው ቀርበዋል።

#### 4.1.1. የዛይ ማህበረሰብና ያእቆብ[4]

የዛይ የማህበረሰብ አባላት ጥንተ የዘር ሀረጋቸውን አስመልክተው ሲጠየቁ ከሚተርኳቸው ተረኮች አንዱ የዘር ሀረጋቸው በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው ያእቆብ ጋር በማስተሳሰር የሚተርኩት ነው። የዘር ሀረጋችን የያእቆብ ነው የሚለውን

---

[4] የይስሐቅ ልጅ ብኩርናን ከወንድሙ ከዔሳው የወሰደ (ዘፍ.20፣27)

እምነታቸውን አጠንክረው ለመግለጽ ሹሉዳ በማህበረሰቡ ውስጥ እንደማይበላ ይናገራሉ። በተረኩ ውስጥ የቀረበው የያእቆብ ዘር የመሆን ጉዳይ በማህበረሰቡ ውስጥ በሰፊው የሚታመን ሲሆን የዘር ሀረግን በሚመለከት የሚተረኩት ተረኮችም መሰረታዊ ይዘታቸው ተመሳሳይ ነው። በመሆኑም የዛይ ማህበረሰብ የዘር ሀረግ ከያእቆብ ጋር የተሳሰረ መሆኑን አስመልክተው አቶ አብሳ ናዳሞ በተረክ ሀያ አንድ ላይ

> የዛይ ህዝብ ሹሉዳ[5] አይበላም። ያእቆብ ከመላክ ጋር ሲታገል ጭኑን ይዞ አደነዘዘው። በዛ ጊዜም አንተ ከእግዚአብሔር ጋር ታግለህ አሸንፈሃል ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል አለው። በዚህ ምክንያት እስራኤላውያን ሹሉዳ አይበሉም። እኛም የእስራኤል ወገኖች በመሆናችን ሹሉዳ አንበላም።
> (መጋቢት 21 ቀን 2004 ዓ.ም ፣ ደብረ ጽዮን ደሴት)

በማለት ይናገራሉ።

ተረኩ በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ ዘፍጥረት ላይ ካለው ከያእቆብ ታሪክ ጋር ተመሳስሎ ያለው ነው። ያእቆብ ሁለቱን ሚስቶቹን፣ ልጆቹንና ባሪያዎቹን ይዞ የያቦቅን ወንዝ ከተሻገረ በኋላ አንድ ሰው ታግሎታል። ከዚያም እንዳላሸነፈው ሲመለከት የጭኑን ሹሉዳ ይዞ አደንዝዞታል። ያእቆብም በጭኑ ምክንያት እንዳነከሰና የእስራኤል ልጆችም እስከ ዛሬ ድረስ የወርችን ሹሉዳ እንደማይበሉ ( መጽሐፍ ቅዱስ፣ 27፣22- 32) ይገልጻል።

በተመሳሳይም መረጃ አቀባዬ መምሬ ዘርአጽዮን ሀ/ማርያም በተረክ ስምንት ላይ «ከእስራኤል የመጣን በመሆናችን ሸሉዳ አንባልም። ምክንያቱም ያእቆብ ከወንድሙ ከኤሳው ጋር ተጣልቶ ወደ አጐቱ ወደ ላባ ሲሄድ ወድቆ ሸሉዳውን ስለተመታ በዚህ ምክንያት እኛም ሸሉዳ አንባልም። (መጋቢት 17 ቀን 2004 ዓ.ም፣ ደብረ ጽዮን ደሴት) በማለት ይተርካሉ።

ከላይ የቀረቡትን ተረኮች ስንመለከት በተረክ አንድ ላይ ያእቆብ ከእግዚአብሄር መላክ ጋር ታግሎ እንዳላሸነፈና በመጨረሻም ስሙ መቀየሩን፣ እንዲሁም የእግዚአብሄር መላእክ የያእቆብን ጭን ይዞ በማደንዘዙ ምክንያት የእስራኤል ወገኖች ሹሉዳ እንደማለይበሉ እንመለከታለን። በተረክ ስምንት ላይ ደግሞ የቀረበው ዛዮች ከእስራእል አገር እንደመጡና ያእቆብ ሲወድቅ ሹሉዳው በመመታቱ ምክንያትም የማህበረሰቡ አባላትም ሹሉዳ እንደማይበሉ ተገልጿል። ከተረኮቹ ይዘት መረዳት የሚቻለው

---

[5] ሹሉዳ፣ ታናሽ የሚባለው የስጋ ብልት ውስጥ የሚገኝ ቀይ ስጋ፣ በግዕዝ ጸከ ይባላል። (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣1948፣ 1224)

የማህበረሰቡ አባላት የዘር ሀረጋችን ያእቆብ ነው ብለው እንደሚያምኑና የሹሉዳ ስጋ አለመብላታቸውንም በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ከቀረበው ከያእቆብ ታሪክ ጋር አጣምረው እንደሚመለከቱ ነው።

የማህበረሰቡ አባላት የዘር ሀረጋቸውን አስመልክተው የሚተርኳቸው ተረኮች ይዘታቸው ሲታይ ጥንተ አመጣጣችን በሀይማኖት ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ከሚሰጠውና ከታወቀ ወገን ነው የሚል ሀሳብ ለማስረጽ ታስበው የቀረቡ ይመስላሉ። ያእቆብ እግዚአብሔርን «ካልባረከኝ አለቅህም» (ዘፍ.27፣32፣26) ብሎ ተባርኳል። በመሆኑም ተረኩ ከግዚአብሔር በረከትን ማግኘቱ ከተጠቀሰው ከያእቆብ ጋር በማስተሳሰር መቅረቡ የተባረክን ነን ብለው እንደሚያምኑና ማንነታቸውንም አግዝፈው ለማሳየት እገዛ ያደርግላቸዋል ማለት ይቻላል።

በሌላ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ በማሸነፉ እሥራኤል ከተባለውና የእገረ እስራኤል መጠሪያን ካስገኘው ከያእቆብ ጋር የዘር ሀረጋቸውን አያይዘው ማቅረባቸው በፍቅር የተሞላና በፍቅር ማሸነፍ የሚችል ማሕበረሰብ ነው የሚል ሀሳብ ለመትከል ታስቦ የቀረበ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም የዘር ሀረጋቸውን ከታዋቂ ወገን ጋር አስተሳስረው ማቅረባቸው በየትኛውም ጊዜና አጋጣሚ ሊደርስባቸው ከሚችል የስነ ልቦና ችግር ለማምለጫነት ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

መረጃ አቀባዩ አቶ ኡርጌሳ ፉሮ ማህበረሰቡ በሬ ወይም በግ ሲያርድ የወርችን ስጋ አውጥቶ የጥላል ወይም ከሌላ ስፍራ ለሚመጡ የማህበረሰብ አባላት ይሰጣል እንጂ በጭራሽ አይበላውም ብለው ነግረውኛል። እንደውም አንድ የዛይ ማህበረሰብ አባል በእርቅ ጊዜ እንኳ ሹሉዳ ካለ እንደመሀላ ስለሚቆጠር አይታረቅም ብለውኛል። የማህበረሰቡ አባላት የሹሉዳ ስጋ አለመብላቱና ለመሀላነት መጠቀሙ ለሌላው የህብረተሰብ ክፍል የያእቆብ ወገኖች ነን የሚለውን እምነታቸውን ለመግለጽና ለማሳመኛነት የሚጠቀሙበት ነው ማለት ይቻላል።

### 4.1.2. የዛይ ማህበረሰብና ከእስራኤል አገር መምጣት

የዛይ ማሕበረሰብ አባላት ጥንተ አመጣጣቸውን በሚመለከት ከሚተርኩት ተረክ መካከል አንዱ ከእስራኤል አገር ወደ ኢትዮጵያ እንዴት ሊመጡ እንደቻሉ

የሚናገሩበት ነው። የማሕበረሰቡ አባላት ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደመጡም በተረክ ሀያ ሶስት ላይ ዘርአጽዮን ሀ/ማርያም እንደሚከተለው ይተርካሉ።

የዛይ ማህበረሰብ የመጣው ከእስራኤል ነው። የመጣውም ማክዳ የምትባል ሴት ነበረች። አባቷ አንጋቦስ ነው። አንጋቦስ የተባለውም በደቡብ ክፍል ዘንዶ ስለገደለ እሱን ሾሙት ይላል። ማክዳ የምትባለዋ እስላም ነች። አንጋቦስ ሲሞት እደ ነገሰች ታምሬን የሚባል እስራኤል አገር የሚነግድ አንቺ ዝም ብለሽ ተቀምጠሻል፤ ኸረ ባክሽን የሰለሞንን ጥበብ ተመልከቺ ብሎ ሲጐተጉታት ሀዝብ አስከትላ ከኢትዮጵያ ወርቅ ጭና ወደ ሰለሞን ሄደች። ከዚያም ቤተ መንግስት ከገባች በኋላ ሁሉንም አዙሮ አሳያት። ሰለሞን ፈልጓት ነበርና ጨው የበዛበት ምግብ እንድትመገብ አደረጋት። በኋላም ውሃ እንድትጠጣ መሀላ አስገብቷት ነበር። ይህ ውሃ ከጠጣሽ መሃላሽን አፈረሽ ማለት ነው አላት ካልጠጣሽ ግን እኔም አልፈልግሽም አላት ጨው የበዛበት ምግብ በመብላቷ ውሃ ጥሙ ሲያስተኛ ሲላት ውሃውን ለመጠጣት ወደ እሱ ክፍል ስትገባ ተገናኛት ከዚያም ትንሽ ቆይቶ ምን አላት በአጋጣሚ እግዚአብሔር ልጅ ከሰጠኝ ብሎ ፎቶ ግራፍ አንስቶ ሰጣት በዛ ጊዜም ንግስት አዜብ ወይም ንግስት ሳባ የተባለችው ከሱ ጋር ከተገናኘች በኋላ ነው። ከዛ በፊት ማክዳ ነው ስሟ። ከዚያም እዚህ/ኢትዮጵያ ስትገባ መፀነሷን ስታውቅ ምን ይለኛ ኢትዮጵያ አለች። ሚኒሊክ የተባለው በኋላ ነው ቀዳማዊ ሚኒሊክን ከወለደች በኋላ እዚህ ያደረገው የሰለሞንን ፎቶ ግራፍ እያየ ነው ሳዶቅ የሚባል መምህርት ኦሪት እስራኤል አገር ታቦተ ፅዮንን የሚያጥን ልጁ አዛሪያስ የሚባል ጋ እንደሚኖር ሚኒሊክ ይላካል። እዛም ከ12ቱም ነገደ እስራኤል በሰለሞን ላይ ሰላማዊ ሰልፍ ያደርጋሉ ድንገት አንተ ብትሞት ይህ ኢትዮጵያዊ እስራኤልን ሊገዛ ስለሚችል ወደ እናቱ አገር ወደ ኢትዮጵያ ላከው ይሉታል። እሱም ጥበበኛ ስለሆነ የበኩር ልጆችሁን እናንተ አምጡ አላቸው ቀዳማዊ ምኒሊክ እዛ ላለመኖር እነሱም የበኩር ልጃቸውን ይሰጣሉ። ሳዱቅል አዛሪያስን ሰጠ። አዛሪያስ ደግሞ ታቦተ ፅዮን ያለችበት ቦታን ያውቃል። በኋላ ታቦተ ሚካኤልን ነገ ይዛችሁ ትሄዳላችሁ ሲባሉ በጠፍ ጨረቃ ገብተው የሚካኤልን ለታቦተ ፅዮን ያለብሱና የታቦተ ፅዮንን ደግሞ ለሚካኤል ያለብሱና ለሊት ጠፍተው አክሱም ይገባሉ። እየሩሳሌም በንፋስ እውታር ስትታመስ ታድራለች። ሳዱቅ ተጠሪ ነውና ሰለሞን ጠርቶት አንተ ዛሬ እኮ እየሩሳሌም በንፋስ እውታር ስትታመስ አደረች። ያችን ፅላት ሰርቀዋት ሄደው ይሆን እንዴ? አለው። ሳዱቅም ሄዶ ሲመለከት ልብሱ የታቦተ ፅዮን ነው፤ ፅላቱ ግን የሚካኤል ነው።ከዚያ በኋላ አክሱም ገብተው ለረጅም ጊዜ ኖሩ ይባላል።

(መጋቢት 15 ቀን፣ 2004 ዓ.ም፣ ደብረ ጽዮን ደሴት)

በተረኩ ማሕበረሰቡ ከእስራኤል እንዴት ሊመጣ እንደቻለ፣ እንዲሁም ወደ ኢትዮጵያ የመጡትም የበኩር ልጆች መሆናቸው ተጠቅሷል። ተረኩ ከክርስቶስ ልደት በፊት

የሰለሞንን ጥበብ ለማየት ወደ እስራኤል አገር በመሄድ ቀዳማዊ ሚኒሊክን ወልዳለች ተብሎ ከሚነገረው የንግሥት ሳባ አፈ ታሪክ ጋር ጥንተ አመጣጣቸው በተዛምዶ የቀረበበት ነው።

ከተረኩ እንደምንረዳው የማህበረሰቡ አባላት ከእስራኤል መጥተናል፣ እስራኤላዊም ነን ብለው እንደሚምኑ ነው። ይህን ሀሳብ በሚያጠናክር መልኩ መምሬ ገ/መስቀል ሂርጳ በተረክ አርባ ሰባት ላይ እንደሚከተለው ይተርካሉ።

> ኢትዮጵያ ከእስራኤል ጋር ተዋለደ የሚባለው ቀዳማዊ ሚኒሊክን ተከትለው ከመጡት ጋር ነው። እንደ ሌላው እኮ አይደለንም መሬትም ቁምር እስራኤል ውስጥ አለን። ለመቀበርም ሆነ ለመቀመጥ እንችላለን። የአፅቀ ስላሴ ዘሮች የመጡት ከእስራኤል ነው።
>
> (መጋቢት 27 ቀን2005 ፣ደብረ ጽዮን ደሴት)

በተረኩ የማሕበረሰቡ አባላት ከእስራኤል መምጣታቸው ተገልጿል። እስራኤል አንዷቷ ሃይማኖት ክርስትና የተመሰረተችባትና የተሰበከችባት በመሆኗ ቅድስት አገር እየተባለች ትጠራለች (አባይነህ፣2002፣5)። ተረኩ የማሕበረሰቡ አባላት ቅድስት ከሆነች አገር የመጣን ቅዱስ ህዝቦች ነን ብለው ማንነታቸውን ለማገንባት እገዛ የሚያደርግላቸው ነው። እንዲሁም ክርስትናን ለመመስረት ቀዳሚ ህዝቦች ነን የሚል ሀሳብ ለመትከል ታስቦ የቀረበ ይመስላል። በሌላ በኩል ቀጣዩ ትውልድም በክርስትና ቀዳሚ ነኝ ብሎ እንዲያምንና እምነቱንም እንዳቀይር ለማስተማር እገዛ ያደርግላቸዋል።

በሌላ በኩል ወደ ኢትዮጵያ የገቡት የበኩር ልጆች መሆናቸው በተረኩ ተጠቅሷል። በኩር በማህበረሰቡ ዘንድ የተለየ ክብር እንደሚሰጠው መረጃ አቀባዩ አቶ ኡርጌሳ ፉሮ ነግረውኛል። መስከረም 16 ቀን የማህበረሰቡ አባላት በቤተክርስቲያን አካባቢ የደመራ በአልን ያከብራሉ። በዚህ ጊዜ ችቦ ሊለኩስ የሚችለው የበኩር ልጅ መሆኑን፣ እንዲሁም በተረክ 38 ላይ እግዚአብሔርን በማመናቸው ከመአት ዳኑ ተብለው የተገለጹት ብሩክና ሎጥን መሰረት በማድረግ በማህበረሰቡ ውስጥ የበኩር ልጅ ሲወለድ እንደ ብሩክና ሎጥ ከመአቱ ያውጣው ተብሎ እንደሚመረቅ ገልጸውልኛል።

አባይነህ (1992፣ 140-142)በኩር የመጀመሪያ ልጅ የሆነ ነው። በኩር ለእግዚአብሔር የተለየ ከሰውም የተመረጠ ነው። የበኩር ልጅ አባቱ ሲሞት ሌሎቹ ከሚወርሱት እጥፍ

ይወርሳል። አባቱ ወደ ሌላ ስፍራ በሄደ ጊዜ ቤተሰቡን ያስተዳድራልበቤተ መንግስት ደግሞ አልጋ ወራሽ ነው በማለት አስፍሯል። ብኩርናን በሚመለከት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለእግዚአብሔር በልዩ ሁኔታ የተሰጠ እንዲሁም ለቅጣት እንኳ የሚሆነው የበኩር ልጅ መሆኑን ማየት ይቻላል። «እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ በሎ ተናገረው፦ በእስራኤል ልጆች ዘንድ ከሰውም ከእንስሳም ማሕጸንን የሚከፍት በኩር ሁሉ ለእኔ ቀድስልኝ፤ የእኔ ነው» (ዘጸ.፣13፣1-3)። እንዲሁም በግብጽ ምድር የበኩር ልጆች በሞት ተቀጥተዋል። እኩለ ሌሊት በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር በዙፋን ከተቀመጠው ከፈርኦን በኩር ጀምሮ በግዞት እስካሉት እስከ ምርኮኞቹ በኩር ድረስ የግብጻውያንን፣ በግብጽ ምድር የተገኘውን በኩር ሁሉ፣ የእንስሳውንም በኩሮች ሁሉ መቷል (ዝኒከማሁ፣22፣ 29)።

የማሕበረሰቡ አበላት ከእስራኤል መጥተዋል ብለው ከሚሏቸው የበኩር ልጆች ማመካከል የእነሱ የዘር ሀረግ የትኛው እንደሆነ የጠየኳቸው መረጃ አቀባዮቼ በሙሉ በትክክል ይሄኛው ነው ብለው መናገር አልቻሉም። ሆኖም የማህበረሰቡ አባላት ከእስራኤል አገር ከመጡት ከአስራ ሁለቱ የበኩር ልጆች ውስጥ ከአንዱ የበኩር ልጅ ጋር የዘር ግንዳቸውን አስተሳስረው ይተርካሉ። ይህም በመሆኑ አንድም በእግዚአብሔር ዘንድ የተመረጥን በመሆናችን ከሌሎች የማህበረሰብ አባላት በቅድስና እንበልጣለን ለማለት ታስቦ የቀረበ ይመስላል። አንድም የበኩር ልጅ በማንኛውም አጋጣሚ አገርን

የማስተዳደርና የመምራት ብቃት ያለው እንዲሁም ብቃቱ የተመሰከረለት ነው የሚል ይዘት ያለው ነው። ይህን ተረክ በመተረክ በቤተ መንግስት ስልጣንም ሆነ በመንፈሳዊ ምርጫ የማህበረሰቡን አባላት ቅድስናና ብቃት ከፍ በማድረግ ከሌሎች ማህበረሰቦች እራሳቸውን ልዩ አድርገው እንዲመለከቱ እገዛ ያደርግላቸዋል።



*መምሬ ገ/መስቀል ሂርጳና  አቶ አብሳ ናዳሞ በትረካ ላይ( መጋቢት 28 ቀን 2004 ዓ.ም)*

## 4.1.3. የዛይ ማህበረሰብ ወደ ዝዋይ ደሴት መምጣት

የዛይ ማሕበረሰብ አባላት ወደ ደሴቱ ከመምጣታቸው በፊት በሰሜን ኢትዮጵያ አክሱም ይኖሩ እንደነበርና በዘጠነኛው ክፈለ ዘመን በተነሳ ጦርነት ምክንያት ወደ ዝዋይ ደሴት እንዴት ሊመጡ እንደቻሉ በተረክ አስራ ሰባት ላይ አቶ ሽጉሀ ገ/ማርያም እንደሚከተለው ይተርካሉ።

> የዛይ ሕዝብ ወደ ደሴቱ የመጣው በዮዲት ጉዲት ጊዜ ነው። በዛ ጊዜ ዮዲት ጉዲት ቤተ ክርስቲያን ታቃጥል ስለነበር አልቻልናትም ብለው ሸሹ። ከሰሜን ተነስተው እንኮበር የሚባል አገር ተቀመጡ ጦርነቱ ከሰሜን ወደ መሐል አገር ሲመጣና ዮዲትም እየደረሰች ነው ሲባል ከሷ ለማምለጥ ሲሉ ወደ ደሴቱ መጡ። ከእንኮበር ተነስተው ብዙ ሕዝብ አስከትለው የመጡት ሦስት ወንድማማቾች[6] ናቸው። መቂ ሲደርሱ አንዱ አቡራ (ሰንጐ) የሚባል ቦታ ቀረ። አንዱ ደግሞ ወደ ጉራጌ አገር ሄደ። እነ አጥቀ ሥላሴ[7]ግን ረግረግ ቆርጠው በረግረጉ[8] ላይ ተቀምጠው በንፋስ እየተገፉ ታቦተ ጽዮንን እንደያዙ ደሴቱ ገቡ። ደሴቱ ውስጥ እንደገቡም መቀመጫቸው የት እንደሆን ለማረጋገጥ እስቴ[9]

---

[6] ሁለቱ የተባሉት አምሃ ስላሴና ትእምርተ መስቀል የሚባሉ እንደሆኑ መረጃ አቀባዮቹ ነግረውኛል። አምሃ ስለሴ ሰንጎ የሚባለው ቦታ ላይ ቀረ የተባለው ሲሆን  ትእምርት መስቀል ደግሞ ወደ ጉራጌ አገር ሄዷል ተብሎ የተገለጸው ነው። ሁለቱ ወንድማቾች  በተለያየ ቦታ ላይ እንዴት ሊቀሩ እንደቻሉ በአባሪው ላይ ተቀምጧል።

[7] አጥቀ ስላሴ ታቦተ ጽዮንን በመያዝ ወደ ደብረ ጽዮን የመጣ መንፈሳዊ አባትነው (ተሰፋዬ 2000፣10)።

[8] ረግረግ፣ በውስጡ ውሃ በላዩ ጭቃና ቀጤማ፣ ሙሽ ያለበት ስፍራ፣ ሲረግጡት የሚያረገርግ የሚያንቀጠቅጥ መሬት ( ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ 1948፣ 1135)

ሰበቱ መጀመሪያ ያረፉበት ተራራ ላይ እሳት እምቢ አላቸው ከዚያም ወደሌላኛው ተራራ ላይ ወጥተው እስቱ ሲሰብቱ እሳት አገኙ። መቀመጫችን ይህ ነው ብለው ለ40 አመታት ታቦተ ጽዮንን ይዘው ተቀመጡ።

(መጋቢት 19 ቀን 2004 ዓ.ም፣ ደብረ ጽዮን ደሴት)

ተረኩ በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ለአክሱም መንግሥት መውደቅ እንደ ምክንያት ከምትነሳው ከዮዲት ታሪክ ጋር ዝምድና ያለው ነው።

በተረኩ የዛይ ማህበረሰብ ከአክሱም ተነስቶ ወደ ዝዋይ ደሴት እንዲመጣ ምክንያት ሆኗል ተብሎ የተገለጸው በዮዲት አማካኝነት የተነሳ ጦርነት ነው። ማህበረሰቡ በደሴቱ ላይ ሰፈረናል ብለው ከሚተርኳቸው ተረኮች በተቃራኒ ሙሉቀን (ተርጓሚ) (2005፣ 73) በዝዋይ ደሴት ላይ የሚገኙት ዛዮችን አስመልክቶ ከአክሱም ተነስተው ወደ ደቡብ ተጉዘው መኖር የጀመሩት ከ10ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ መሆኑን ለማሳመን ሲሞክሩ የጽላተ ሙሴን ታሪክ ማያያዝ ታሪካዊ ጠቀሜታ እንዳለው በማመናቸው ነው ይላል። በ14ኛው ክፍለ ዘመን ዝዋይን የጎበኙት ፊሊጲስና አኖሬዎስ በዝዋይ ደሴቶች ያሉ ነዋሪዎች ሀይማኖት ያልነበራቸውና የሞቱም ሆኑ በቁም ያሉ እንስሳትን የሚመገቡ እንደነበሩና ሰዎቹንም ክርስቲያን ያደረጓቸው ሚሲዮናውያኖቹ መሆናቸውን ይገልጻል።

Sergew (1972:227-228) ግን ይህን ሀሳብ በተቃረነ መልኩ ዮዲት ስልጣን ከያዘች በኋላ ቤተ ክርስቲያናት እንዲወድሙ በማድረጓ አክሱም የነበሩ ካህናት ታቦተ ጽዮንን ይዘው ወደ ዝዋይ በመሄድ በደሴቱ ላይ ለ40 አመታት እንደቆዩና ዮዲት ከሞተች በኋላ አንበሳ ውድም ሰላምና መረጋጋት በመፍጠሩ ቀሳውስቱ ታቦተ ጽዮንን በመያዝ ወደ አክሱም መመለሳቸውን ይገልጻሉ።

ተረኩ ለምን ይተረካል? ለማህበረሰቡ አባላትስ ምን ትርጉም ይሰጠዋል? እንዲሁም በተረኮቹ ውስጥ የተገለጹት ተምሳሌቶች ምን ትርጉም አላቸው? የሚሉ ነጥቦችን ተረኩን መሰረት በማድረግ ትንታኔ እሰጥባቸዋለሁ። በፎክሎር ባለሙያዎች ዘንድ ሊነሱ የሚገቡ ጉዳዮች በማለት Oring እና Bascom የተባሉ ምሁራን የገለጹት ፎክሎር ለሚፈጥረውና ለሚገለገልበት ማህበረሰብ ምን ትርጉም ሊሰጠውና ምን መልእክት ሊያስተላልፍለት ይችላል የሚለው በዋናነት የሚነሳ ጥያቄ መሆኑን ነው።

---

[9] እስቱ፣ ያስታ ወገን፣ያስታ እሳት የሚወጣው ማንኛውም እንጨት ወይም ካስታ የወጣ እሳት( ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ 1948፣145)

በተረኩ ውስጥ በዮዲት ጉዲት ተነስቶ በነበረው ጦርነት ምክንያት ታቦተ ጽዮንን ይዘው ወደ ደሴቱ መምጣታቸው ተጠቅሷል። በዚህ ተረክም ሆነ ቀደም ሲል ከእስራኤል አገር መጣን ብለው ከሚተርኩት ተረክ መረዳት የሚቻለው የማህበረሰቡ አባላት እያንዳንዱ ከቦታ ቦታ የተዘዋወሩበት ታሪክ ተያይዞ የሚተረከው ከታቦተ ጽዮን ጋር መሆኑን ነው። በመሆኑም ለታቦተ ጽዮን ብቸኛ ተቆርቋሪና ታቦተ ጽዮንና የማሕበረሰቡ አባላት የረጅም ጊዜ ትስስር አላቸው የሚል ሀሳብ ለማጽናት የቀረበ ነው። በተጨማሪም ማህበረሰቡ ቅርስ እንዳይጠፋና እንዳይወድም ከየትኞቹም የማህበረሰብ አባላት የተለየ ኃላፊነት የሚሰማው ነው የሚል ይመስላል። ከዚህ ሌላ የታቦተ ጽዮን ብቸኛ ባለቤቶች እኛው ነን በማለት ቀጣዩ ትውልድም ይህን ሀሳብ አጽንቶ እንዲቀጥል ይጠቅማቸዋል።

ተረኩ ሙሴ እስራኤላውያን ወገኖቹን ከግብጽ ምድር ይዞ ሲወጣ ካለው የጉዞ ታሪክ ጋር ቅርርብ ያለው ይመስላል። ሙሴ ህዝቡን ከባርነት ለማላቀቅ ተቆርቋሪና መሪ ሆኖ ለ430 ዓመታት ከነበሩበት ግብጽ ይዞ ሲወጣ የዛይ ማህበረሰብ መሪ አጥቀ ስላሴ ደግሞ ህዝቡና ቅርሱ በጦርነት ምክንያት እንዳያልቁ ከፊት ለፊት በመሆን እየመራ ሄዷል። ሁለቱም የማህበረሰቡ መሪ መሆናቸው የሚያመሳስላቸው ይመስላል። እንዲሁም ሙሴም ሆነ አጥቀ ስላሴ በእግር ለመሻገር የማይደፈርን ሀይቅ ወይም ባህር በአንዳች ተአምር ህዝባቸውን ይዘው ተሻግረዋል። ሙሴ የእስራኤልን ህዝብ እየመራ በመንገድ ላይ ሳለ እግዚአብሔር ለሊቱን ሁሉ የምስራቅ ንፋስ አምጥቶ ባህሩን አስወግዶለታል(ዘጸ.፲14፲21) የዛይ ማህበረሰብ መሪ አጥቀ ስላሴ ደግሞ ህዝቡን በረግረግ ላይ አስቀምጦ በንፋስ እየተገፋ ወደ ደሴቱ ገብቷል። የሁለቱም መሪዎች ረዳት የሆነውና ከፊት ለፊታቸው የተጋረጠባቸውን ውሃ ከእነ ህዝባቸው እንዲሻገሩ ረዳቸው ተብሎ የተገለጸው ንፋስ ነው። የማህበረሰቡ አባላት ወደ ደሴቱ ልንገባ የቻልነው እግዚአብሔር ከጎናችን ሆኖ ነው ብለው እንዲያምኑ አድርጓቸዋል ማለት ይችላል። መምሬ ገ/መስቀል የማህበረሰቡ አባላት ከአክሱም ተነስተው ወደ ዛይ ደሴት የመጡበትን ሁኔታ አስመልክተው «ቀን እየተኙ ሊሊቱን ይሄዳሉ። አገርም ሆነ መንገድ አያውቁም፤ በእግዚአበሔር ኃይል እየተመሩ ነው እዚህ የደረሱት» ብለው ነግረውኛል።

ከዚህ ሌላ በግብጽ አገር በባርነት ለነበሩ እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ጸጋ ለዛይ ህዝብም ተሰጥቶታል የሚል ሃሳብ ለማጽናትና በእግዚአብሔር የተመረጠ

ህዝብ ነው ብለው እንዲያስቡ፣ የማህበረሰቡንም ማንነት በዚህ መንገድ ከሌላው የተለየ አድርገው እንዲመለከቱ ያደርጋቸዋል ማለት ይቻላል። እንዲሁም የዛይ ማህበረሰብንና ታቦተ ጽዮንን ወደ ደሴቱ ይዞ ገብቷል ተብሎ በተረኩ የተገለጸው አጥቀ ስላሴን መሰረት በማድረግ እኛም የራሳችን ሙሴ አለን ለማለት ታስቦ የቀረበ ሊሆን ይችላል።

አጥቀ ስላሴ ከህዝቡ ጋር ወደ ደሴቱ ከገባ በኋላ መቀመጫው ወይም መኖሪያው የት እንደሆነ ለማረጋገጥ እሳት እንደፈለገና በመጨረሻም ላይ ከአንዱ ተራራ ላይ እሳት በማግኘቱ እዛው ሊቀመጥ እንደቻለ በተረኩ ተጠቅሷል። እሳት በማህበረሰቡ ውስጥ ምን ባህላዊ ትርጉም እንዳለው የጠየኳቸው መረጃ አቀባዬ መምሬ ገ/መስቀል ሂርጳ የነገሩኝ እሳት በመንፈስ ቅዱስ እንደሚመስል እንጂ በባህሉ የተለየ ትርጉም እንደሌለው ነው። አጥቀ ስላሴ መኖሪያ ቦታውን ለመምረጥ እሳትን እንደ አንድ ጠቋሚ መሳሪይ ተገልግሎበታል። እግዚአብሔር ለሙሴ በኮሬብ ተራራ ላይ ተገልጦ ያነጋገረው በእሳት አምሳል ነው። «የእግዚአብሔር መላእክ በእሳት ነበልባል በእሾህ ቁጥቋጦው መካከል ታየው» (ዘጸ.፣3፣2)። ዛዮችም በደሴቱ ላይ ልንኖር የቻልነው በመንፈስ ቅዱስ ታግዘንና ቦታውም ተመርጦልን ነው ብለው እንዲያምኑ አድርጓቸዋል። እንዲሁም አዲሱ ትውልድም በእግዚአብሔር የተመረጠ ቦታ ላይ እየኖርኩ ነው ብሎ እንዲያምንና ከሌላው ማህበረሰብም በቅድስና የተለየሁ ነኝ ብሎ እንዲያስብ እገዛ ያደርግላቸዋል።

በሌላ በኩል የዛይ ማህበረሰብ አባላት ታቦተ ጽዮንንና ቅርስ ለመጠበቅ ከአገር አገር ሲንከራተቱ ኖረው ታቦተ ፅዮን ወደ አክሱም ስትመለስ እነሱ ለምን ዛይ ደሴት ብቻቸውን ያለ ታቦተ ጽዮን ሊቀሩ ቻሉ? ወይስ ታቦተ ፅዮንን ወደዚህ ደሴት አምጥዋት የነበሩት ሌሎች ሰዎች ናቸው? እነዚህ ሰዎች ታቦተ ፅዮን ከመምጣቷ በፊት በዚህ ደሴት የነበሩ ሰዎች ይሆኑ ይሆን እንዴ? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳት ይቻላል። መረጃ አቀባዬ መመሬ ገ/መስቀል ሂርጳ ግን የማህበረሰቡ አባላት ከጦርነቱ በኋላ ተመልሶ ወደ መጡበት አክሱም ያልሄዱት በአምስቱም ደሲያት ላይ ቤተክርስቲያን በማቋቋማቸና ሀብት ንብረት በማፍራታቸው ነው ብለውኛል። ከዚህ ሀሳብ በተቃረነ መልኩ ግን ሌላኛው መረጃ አቀባዬ መርጌታ ሰምረ ግደይ በተረክ ሶስት ላይ ይኩኖ አምላክ ይህን ደሴት ለቀን መሄድ የለብንም ይህ ደሴት ደብረ ጽዮን (የጽዮን መደበቂያ) ነው። ነገ አንድ ችግር ቢፈጠር መልሰን የምንመጣበት ነው። ሁላችንም ለቀን እንሂድም ብሎ ሁሉንም የእጅ ባለሙያዎች በደሴቱ ውስጥ አስቀምጦ ወደ አክሱም መሄዱን ይገልጻሉ።



አቶ ሽጉሀ ገ/ማርያም በትረካ ላይ(መጋቢት 28 ቀን 2004 ዓ.ም)

## 4.2. ነገስታትና የዛይ ማህበረሰብ

የዛይ ማህበረሰብ አባላት ቀደም ሲል ከነበሩ ነገስታት ጋር የጠበቀ ዝምድና እንደነበራቸው ይተርካሉ። በዚህ ርዕስ ስርም ማህበረሰቡ ከይኩኖ አምላክ፣ ከአፄ ሚኒሊክና ከአፄ ኃይለስላሴ ጋር ያላቸውን ዝምድና አስመልክተው የሚተርኳቸው ተረኮች እንደሚከተለው ይተነተናሉ።

### 4.2.1. የዛይ ማህበረሰብና አፄ ይኩኑ አምላክ

የዛይ ማህበረሰብ አባላት አፄ ይኩኑ አምላክ የተወለደው ዛይ ደሴት ላይ እንደሆነ ይናገራሉ። አቶ ቆፒያ በራርሶ በተረክ አንድ ላይ እንደሚከተለው ይተርካሉ።

> አፄ ይኩኖ አምላክ የተወለደው በዝዋይ ደሴት ላይ ሲሆን የክርስትና ስሙም ተስፋ እየሱስ ነው። ወደ ኃይቅ እስጢፋኖስ ለትምህርት ሄደ። ተክለሀይማኖት አግኝተውት ከየት እንደመጣ ሲጠይቁት ከዝዋይ ደሴት መምጣቱን ነገራቸው በዚህ ጊዜ ለጥያቄያችን መልስ ተገኘ አሉ። በቃ አንተን መንግስት አደርግሀለው አሉት። ከዚያም ሊያደራርሩት ይዘውት ሄዱና አባቶቻችን ታቦተ ፅዮንን በእግዚአብሔር ኃይል ያመጧትን ያለ መንግስት መቀመጥ የለባትም። ይህች ታቦት እንዳትዘረፍ ማን

ይጠብቃታል በማለት እግዚአብሔር ኃይል ይሁንህ ብለው ቀብተው አነገሡት። ከዚያም በኋላ ይኩኑ አምላክ የኢትዮጵያ ንጉስ ሆነ።
(መጋቢት 21 ቀን 2004 ዓ.ም፣ ደብረ ጽዮን ደሴት)

በተረኩ ይኩኑ አምላክ የተወለደው ዝዋይ ደሴት ላይ መሆኑንና በኋላም ለትምህርት ወደ ሀይቅ እስጢፋኖስ መሄዱ ተገልጿል። እንዲሁም ሀይቅ እስጢፋኖስ ያገኙት ተክልሃይማኖት ይኩኑ አምላክ ከየት እንደመጣ ጠይቀው ከዝዋይ ደሴት እንደመጣ መናገሩንም ከተረኩ እንመለከታለን።

የተለያዩ የታሪክ ድርሳናት ደግሞ ይኩኑ አምላክ የተወለደው ሸዋ ውስጥ ሲሆን አባቱ እንዳይገደልበት ስለፈራ ወደ ኃይቅ ወስዶ ለአባ እየሱስ ሞአ በአደራ እንደሰጠው፣ ከጊዜ በኋላ አቡነ ተክለሀይማኖት ወደ ኃይቅ ሲመጡ ይኩኑ አምላክን ተመልክተው ማንነቱን ሲጠይቁ የቀዳማዊ ሚኒሊክ ዘር መሆኑን እየሱስ ሞአ እንደነገሯቸውና በዚህ ጊዜም አቡነ ተክለሀይማኖት ይኩኑ አምላክ እንዳይገደል በመስጋት ወደ ሸዋ እንዲሄድ እየሱስ ሞአን በማሳመን ወደ ሸዋ ይዘውት እንደተመለሱ ይገልጻሉ። እንዲሁም አቡነ ተክለሀይማኖት እየተዘዋወሩ ወንጌል በሚሰብኩበት ጊዜ ስልጣን ለዛጉዬ ሳይሆን ለሰለሞን ስርወ መንግስት እንደሚገባ ይናገሩ ነበር። በኋላም ከናአክቶ ለአብ ጋር ስልጣን ለዛጉዬ እንደማይገባና ስልጣኑ ለቀዳማዊ ሚኒሊክ ዘር እንዲሆን ስምምነት በማድረግ ነአክቶ ለአብ ስልጣኑን ለይኩኑ አምላክ እንዲሰጥ ሆኗል።
(ተክለፃዲቅ፣ 1951፣1-2 ገድለ ተ/ሃይማኖት፣1989፣67)

ቀደም ሲል የተጠቀሱት የታሪክ ድርሳናት ይኩኑ አምላክ የተወለደው ሸዋ ውስጥ መሆኑን አስፍረዋል። የማህበረሰቡ አባላት በሚተርኩት ተረክ ደግሞ ይኩኑ አምላክ የተወለደው ዝዋይ ደሴት ላይ ነው ተብሎ ተጠቅሷል። የታሪክ ድርሳናቱ ላይ ይኩኑ አምላክን በሚመለከት የተቀመጠውን ሀሳብ ማንሳቱ ከዛይ ማህበረሰብ አባላት ተረክ ጋር ምን ተዛምዶ አለው የሚለውን ለማሳየት ይረዳኛ እንደሆነ እንጂ የተረኩን ትክክለኛ መሆን አለመሆን ለማጣራት ፈልጌ አይደለም። ምክንያቱም አንድ ተረክ እውነት ይሁን ወይም ፈጠራ ሊወሰን የሚገባው በተራኪውና በአድማጩ(የታዳሚው) አመለካከት በመሆኑ Bascom (1965፡7) ይገልጻሉ።

የማህበረሱ አባላትም አጼ ይኩኑ አምላክ የተወለደው ዝዋይ ደሴት ላይ ነው ብለው ነው የሚያምኑት። ማህበረሰቡም የተወለደው ተብሎ መተረኩ አስፈላጊነቱ ምንድ ነው የሚል

ጥያቄ ማንሳት የሚቻል ይመስለኛል። ተረኩ የሰለሞን ስርወ መንግስትን በድጋሚ እንዲያንሰራራ ምክንያት ሆኗል የሚባለው ይኩኑ አምላክ ትውልድ ዛይ ነውI እኛም የዚህ ንጉስ ወገኖች ነን የሚል ይመስላል። በሌላ በኩልም የሰለሞን ስርወ መንግስት በድጋሚ እንዲያንሰራራ በማድረግ ቀዳሚ ሚና ያለንና አገር በማስተዳደር በኩልም የተዋጣልን ነን የሚል ሀሳብ ለማፅናት የቀረበ ነው ማለት ይቻላል።

### 4.2.2. የዛይ ማህበረሰብና አጼ ምኒሊክ

የዛይ ማህበረሰቡ አባላት ከነገስታት ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንደነበራቸው በተረኮቻቸው አማካኝነት ይገልፃሉ። የጠበቀ ግንኙነት ነበረን ከሚሏቸው ውስጥም አጼ ምኒሊክ ይገኛሉ። የአጼ ምኒሊክንና የማህበረሰቡን ግንኙነት በሚመለከትም ከቀረበው ተረክ በመነሳት ትንታኔ ለመስጠት ይሞከራል። የማህበረሰቡ አባላት ከአጼ ምኒሊክ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት አስመልክተው አቶ ሽጉ ገ/ማርያም በተረክ ሁለት ላይ እንደሚከተለው ይተርካሉ።

> አጼ ሚኒሊክ ኢትዮጵያን ሁሉ አንድ አድርገው አልገዛ ያላቸው የደቡብ ጦና ነበርና ጦናን ተዋግተው ሲመለሱ የዝዋይን ሃይቅ አዩት። ይህ ሃይቅ ምንድን ነው ብለው ሲጠይቁ የዝዋይ ደሴት ነው አሏቸው። አጼ ምኒሊክም ኢትዮጵያን አንድ አድርገን ስንጨርስ ምን ተፈጠረ? ይህንማ ሳላይ አልሄድም ብለው ከነሰራዊታቸው ወደ ደሴቱ ከመጡ በኋላ በምን ይግቡ? ከነሰራዊታቸው እዛው ቆሙ በኋላም እዛ ያለው ህዝብ ሰው አይቶ አያውቅም ነበርና ሊወጋቸው ጠበቃቸው።
>
> ከዚያም አጼ ሚኒሊክ መግባት ስላልቻሉ በቃ ምንም ላደርጋችሁ ሳይሆን ምን አይነት ሰዎች እንደሆናችሁ ልያችሁ በማለታቸው ከአምስቱ ደሴያት አንድ አንድ ሽማግሌ ተውጣጥቶ ከእሳቸው ጋር ተገናኙ። ከዛ ሲገናኙም የአክሱም መንግስት እንደነበሩና በታሪክ ምክንያት እዚህ ደሴት እንደቀሩ ሲሰሙ አጼ ሚኒሊክ አለቀሱ። ለካ እናንተ ለኢትዮጵያ ህዝብ ብላችሁ እዚ ውሃ ውስጥ ቀርታችኋል? ብለው በጣም አዘኑ። ከዛ በኋላ በሉ አሁን ውጭ ወጥታችሁ ስፈሩ። የአገር ታሪክ ለመጠበቅ እስካሁን እዚህ ደሴት ኖራችኋልI ከዚህ በኋላ ውሃ ውስጥ መኖር የለባችሁም አሏቸው። አዲስ አበባ ጃንሜዳ እንዲሠፍሩ ተፈቅዶላቸው ነበር። ከዚያም በደሴቱ ውስጥ ያለውን ቤተክርስቲያን እሰራላችኋለሁ ብለው ቃል ገቡ። በኋላም ለእያንዳንዱ የደሴቱ ሰው አንዳንድ ከብት ሰጡ። እስካሁን ድረስ የሚኒሊክ ከብቶች የሚባሉ አሉ። ለእነሱም አካባቢውን እንዲገዛ ስልጣን ሰጡትና ሄዱ። ከዚያም ከመሞታቸው በፊት ዘውዲቱን «ያን ደሴት እሰራለሁ ብዬ ነበርI ስላልሆነልኝ አንቺ ስሪው» አሏት። በኋላም ዘውዲቱ

ደብረ ፅዮንን ሰርተዋት ነበር። ከዚያም ለገዳሙ መተዳደሪያ የሚሆን 150 ጋሻ መሬት ከዝዋይ ሃይቅ ጀምሮ እስከ አሰላ ድረስ ርስት ሰጡ። ከዛም ህዝቡ እምነቱን እንዳይቀይር እንዲሁም ስልጣኔውን እንዲቀጥል ከበጌ ምድር አስተማሪ እያመስጡ ትምህርት ይሰጥ ነበር።

(መጋቢት 27 ቀን 2004 ዓ.ም፣ ደብረ ጽዮን ደሴት)

ይህ ተረክ አጼ ሚኒሊክ ዝዋይ ደሴትን ከተመለከቱ በኋላ ማህበረሰቡ ታሪክ ለመጠበቅ ሲል ወደ ደሴቱ መጥቶ በመኖሩ ማዘናቸውን፣ የህዝቡም ስልጣኔና እምነት እንዳይጠፋ ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጉ እንደነበር፣ እንዲሁም የማህበረሰቡ አባላት የኢትዮጵያን ህዝብ ታሪክ ለመጠበቅ ሲል በደሴቱ ላይ በመኖሩ አፄ ምኒሊክ ከደሴቱ ውጭ ወጥተው እንዲሰፍሩ በማለት ቦታ መስጠታቸውን የሚናገር ነው።

ጸሀፌ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ (1959፣ 202) ዳግማዊ ምኒሊክ ወደ ዝዋይ ሀይቅ በመሄድ ሄራራ በሚባል አካባቢ ላይ የዛይ ህዝብ አስተዳዳሪ የነበረውን አሊቦን ማግኘታቸውንና የዛይ ሰዎችን ገንዘብ እንዳይነካና ወታደርም ወደ ደሴቱ እንዳይገባ ማደረጋቸውን፣ ከዚህ በኋላም የዛዮች በፈለጉት መንገድ እንዲወጡና እንዲገቡ ማዘዛቸውንና የዛይ ህዝብን የነካብኝ ጠላቴ ነው ብለው አውጀው መመለሳቸውን ይገልጻሉ።

ከተረኩም የማህበረሰቡ አባላት ከአጼ ምኒሊክ ጋር የጠበቀ ዝምድና ነበረን ብለው እንደሚያምኑ መረዳት ይቻላል። ተረኩ ማህበረሰቡ በደሴቱ ውስጥ ሊኖር የቻለው የአገር ታሪክ ለመጠበቅ ሲል እንደሆነና ከሌሎች የህበረተሰብ ክፍሎች በተለየ ሁኔታ ታሪክ ለመጠበቅ መስዋእትነት ሊከፍል የሚችል ማህበረሰብ ነው ብሎ ለሌሎች ምላሽ ለመስጠት የቀረበ ይመስላል። እንዲሁም ነገስታትም የማህበረሰቡን ታሪክ ጠባቂነት ስላመኑበት ሃላፊነት ሰጥተውታል የሚል ነው።

በሌላ በኩል በተረኩ ውስጥ ማህበረሰቡ ስልጣኔውን እንዲቀጥልና እምነቱን እንዳይቀይር ትምህርት ይሰጠው እንደነበር ተገልጿል። በመሆኑም የማህበረሰቡ አባላት ቀደምት ስልጣኔ ነበረን፤ ይህም ስልጣኔያችን እንዲቀጥል ነገስታት ድጋፍ ያደርጉልን ነበር የሚል ይዘት ያለው ነው። እንዲሁም ማህበረሰቡ ቀድሞም ቢሆን በእምነቱ እንዲያጠነክር ጥረት ሲደረግለት እንደነበር በመግለጽ አዲስ ትውልድም እምነቱን ይዞ እንዲቀጥል ለማስተማር የቀረበ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም

ማህበረሰቡና አጼ ምኒሊክ የጠበቀ ግንኙነት እለው ብለው በመተረክ የነገስታት ወገን እንደሆኑ ለማሳየት ይጠቅማቸዋል።

ከዚህ ሌላ የዛይ ማህበረሰብ አባላት ከአጼ ምኒሊክ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት አስመልክቶ አጠናክረው ለመግለጽ መምሬ ተላፊኖስ ሚቾ በተረክ ሰላሳ አራት ላይ

> «አጼ ሚኒሊክ ለሙግት ይሄዱ ለነበሩ የዛይ ማህበረሰብ አባላት ቤት ይሰጧቸው ነበር። ለሙግት የሚሄዱትም የማህበረሰቡ አባላት የአሳ ቋንጣ በጆንያ ይዘው ይሄዱ ነበር። በዚህ የተነሳም ወደ ምኒሊክ ቤተመንግስት አሣ እንዲገባ ያደረጉት ዛዮች ናቸው።»
> (መጋቢት 27ቀን 2004 ዓ.ም ደብረ ጽዮን ደሴት)

በማለት ይተርካሉ።

ይህ ተረክ የማህበረሰቡ አባላት ከአጼ ሚኒሊክ ጋር የነበረው ግንኙነት በምን መልኩ እንደነበር የሚያሳይ ነው። ተረኩ የዛይ ማህበረሰብ አባላት ወደ ምኒሊክ ቤተ መንግስት አሣን ለመጀመሪያ ጊዜ አስገብተዋል መባሉ አሣ ከሚገኝባቸው ሌሎች ቦታዎች በቀዳሚነት ለቤተ መንግስት ሰዎች አሳን በማስተዋወቅና ለምግብነት እንዲጠቀሙ በማድረግ ቅድሚያ ያለን ነን የሚል ነው።

በሌላ መልኩ አጼ ምኒሊክ ለማህበረሰቡ አባላት ይሰጡት የነበረው እንክብካቤ ከነበራቸው ወገናዊነት የመነጨ ነው የሚል ይመስላል። ይህን ተረክ በአካባቢው ላይ በመተረክም የነገስታት ወገን ነን የሚለውን እምነታቸውን ለመትከል፣ ማንነታቸውን ለመገንባትና እራሳቸውን የነገስታት ወገን አድርገው ለማሳየት እገዛ ያደርግላቸዋል።

### 4.2.3. የዛይ ማህበረሰብና አጼ ኃይለስላሴ

የዛይ ማህበረሰብ አባላት ከነገስታት ጋር የነበራቸውን ግንኙነት በሚመለከት ሲጠየቁ አፄ ኃይለስላሴ ማህበረሰቡ ይወዱት እንደነበር ይናገራሉ። ይህን አስመልክቶም ወልደጊዮርጊስ ፉሮ በተረክ ሀያ ስምንት ላይ እንደሚከተለው ይተርካሉ።

> አጼ ኃይለስላሴ ወደ እዚህ ደሴት ብዙ ጊዜ ይመጡ ነበር።ምክንያቱም ህዝቡ ታማኝና በእምነቱ የጸና ነው። ህዝቡንና ደሴቱን በጣም ይወዱታል። ህዝቡን ማንም እንዲያጠቃው አይፈልጉም። የዛይን ህዝብ ያጠቃ እንኳ ቢኖር እሳቸው ሞት ነበር የሚፈርዱበት።

(መምሬ ወልደጊዮርጊስ ፉሮ፣ መጋቢት 14 ቀን 2004 ዓ.ም፣ደብረ ጽዮን ደሴት)

ከተረኩ እንደምንረዳው አጼ ኃይለስላሴ በዝዋይ ደሴት ላይ ብዙ ጊዜ ይመላለሱ እንደነበርና ከህዝቡም ጋር በነበራቸው ወዳጅነት የተነሣ ጥቃቱን እንደማይወዱ ነው።

ከዚህ ሌላ አጼ ኃይለስላሴ ለአምስቱም ደሴቶች ስያሜ መስጠታቸውን አስመልክቶ አቶ ነገዎ ጎሮ በተረክ ሀያ ላይ እንደሚከተለው ይተርካሉ።

> ዝዋይ የሚለውን ጃንሆይ ናቸው የሰየሙት። አምስቱንም ደሴቶች ጠየቁ ደብረ ፅዮን፣ ፉንድሮ፣ ጠዴቻና ደብረ ሲና ሲሏቸው አምስቱም አጠቃላይ ስም የለውም ወይ አሉ። አምስቱም ዛይ ነው የሚባለው ሲሏቸው እንግዲያውስ ዝዋይ ይባል አሉ።
>
> (ሚያዝያ 1 ቀን 2004፣ ደብረጽዮን ደሴት)

ከተረኮቹ ይዘት መረዳት የሚቻለው ማህበረሰቡና አጼ ኃይለስላሴ የጠበቀ ዝምድና እንደነበራቸውና አጼ ኃይለስላሴም ከሌሎች ቦታዎች ሁሉ ደሴቱንና ህዝቡን ይወዱት እንደነበር ነው። ተረኩም የማህበረሰቡ አባላት የሚኖሩበት ደሴት ነገስታትም ጭምር የሚወዱት ነው የሚለውን ሀሳብ ለማፅናት የተነገረ ነው። የማህበረሰቡ አባላት ነገስታት በሚወዱትና አዘውትረው የሚመርጡት ቦታ የሚኖሩ መሆናቸውን ለመትከል ታስቦ የቀረበ ነው ማለት ይቻላል።

ከላይ በቀረቡትና ትንታኔ ሊሰጥባቸው ከተሞከሩት ከሶስቱ ተረኮች ይዘት የምንረዳው የዛይ ማህበረሰብ አባላት ከነገስታት ጋር የጠበቀ ዝምድና አለን ብለው እንደሚያምኑ ነው። ይህን ሀሳባቸውን ለማጠናከርም አጥቀ ስላሴ ህዝቡን አስከትሎ ወደ ደሴቱ ከገባ በኋላ ቀድመው ከነበሩ ህዝቦች ስልጣን ሊያገኝ ቻለ የሚሉትን ተረክ ሲተርኩ «ትክክለኛ የነገስታት ወገን መሆናችን የሚታወቀው...» የሚለውን ሀሳብ በማስቀድም ነው።

በተረኮቹ የቀረቡት ነገስታት በታሪክ የሚታወቁት በሰለሞን ስርወ መንግስትነታቸው ነው። በተረኮቹ እነዚህን ነገስታት ከማህበረሰቡ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበራቸው ተብሎ መነሳቱ ነገስታቱ በደሴቱ ውስጥ ለሚገኙ የማህበረሰብ አባላት የሚያሳዩት ቅርበት ወገን መሆናችንን በማመናቸው ነው የሚል ይመስላል። እንዲሁም ነገስታቱ የሰሎሞን ዘሮች ናቸው፤እኛም የሰሎሞን ዘሮች ነን ብለው አምነው እንደሚኖሩ ነው። በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ እንዲህ አይነቱን ተረክ በመተረክ የእኛ ዘር ከፍ ያለ ነው የሚለውን

ሀሳብ ለማስረጽ ይጠቅማቸዋል። በጥቅል የራስን ዘር አመጣጥ፣ የራስን ዘር የበላይነት፣ የራስን ዘር ምርጥነት በማስረጽ ማህበራዊ መሰረትን በማደላደል ከፍ ያለ የስነልቡና መረጋጋትን ለማግኘት እገዛ ያደርግላቸዋል ማለት ይቻላል።

የማህበረሰቡ አባላት ጥንተ አመጣጣቸውን አስመልክተው ከሚተርኳቸው ተረኮች ይዘት መረዳት የሚቻለው የዘር ሀረጋችን ያእቆብ ነው፤ ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ የመጣነውም ከቀዳማዊ ምኒሊክ ጋር ታቦተ ጽዮንን ይዘው ከመጡት ከእስራኤል ነገዶች ከተውጣጡት የበኩር ልጆች መካከል የአንዱ ወገን ነን ብለው እንደሚያምኑ ነው። በዚህም የማህበረሰቡ አባላት ጥንተ መገኛችን አገረ እስራኤል፣ የዘር ሀረጋችንም ያእቆብ ነው ብለው እንደሚያምኑ ከተረኮቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል። በተጨማሪም ከአክሱም ወደ ዝዋይ ደሴት ልንመጣ የቻልነው በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን በዮዲት አማካይነት በተነሳ ጦርነት ከታቦተ ጽዮን ጋር ነው ተብሎ እንደሚታመን መገንዘብ ይቻላል።

በሌላ በኩል በደሴቱ ላይ የሰፈርነው ቦታው በፈጣሪ ተመርጦልን ነው ብለው አምነው እንደሚኖሩ፣ ከነገስታት ጋር የነበራቸው ግንኙነትን አስመልክተውም በተለይ በሰለሞን ስርወ መንግስት ስር ከሚታወቁ ነገስታቶች ጋር የጠበቀ ዝምድና አለን ብለው እንደሚያመኑና ነገስታቱም ለማህበረሰቡ ተቆርቋሪ ነበሩ ብለው እንደሚያምኑ የተረኮቹ ይዘቶች ያሳያሉ።

## 4.3. ከሐይቁ ጋር ተያይዘው የሚተረኩ ተረኮች

ከሀይቁ ጋር ተያይዘው የሚተረኩ ተረኮች በሚለው ርእስ ስር ስለ ዝዋይ ሐይቅ አፈጣጠርና ቅድስናን በሚመለከት በማህበረሰቡ የሚተረኩ ተረኮች በንኡስ ርእስ ተከፋፍለው ትንታኔ ይሰጥባቸዋል።

### 4.3.1. የዝዋይ ሐይቅ አፈጣጠር

የማሕበረሰቡ አባላት የዝዋይ ሀይቅ ጥንት እንዳልነበርና ከጊዜ በኋላ ግን ከጥንቃቄ ጉድለት መፈጠሩን ይናገራሉ። ይህን ሀሳብ አስመልክቶም በተረክ 39 አቶ ነገዎ ሸጎሮ እንደሚከተለው ይተርካሉ።

> ድሮ ቦታው ለጥ ያለ ሜዳ ነበር። ቡርቃ የሚባል ቦታ አለ። እዚህ ቦታ ላይ ዙሪያው በቤት ተከቧል። ውሃውን ቀድተው ሲጨርሱ ይከድኑት ነበር። ከውሃው ቤቷ ቅርብ የሆነች ሴት ህፃን አስተኝታ ውሃ ልትቀዳ ወደ ቡርቃው ትሄዳለች ከዚያ በኋላ ውሃውን እየቀዳች እያለች ልጇ በማልቀሱ ውሃውን ሳትከድን ወደ ቤቷ ሄደች። በዚህ ጊዜ ውሃው

ገንፍሎ መፍሰስ ጀመረ። አጠገቡ ያሉ የገበሬ ልጆች የሚባሉ ውሃው ፈሰሰልን ብለው ደስ ብሏቸው ጨፈሩ። ከበሮ ይዘው ሲጨፍሩ ውሃው ቀስ በቀስ እግራቸው ላይ ሲደርስ፣ ወገባቸው ላይ ሲደርስ፣ ከዚያም ሙሉ በሙሉ ውሃው ዋጣቸው። ለዚህ ነው የገበሮ ልጆች ሲስቁ ውሃ ወሰዳቸው የሚባለው።
(መጋቢት 18 ቀን 2004 ዓ.ም፣ ደብረ ጽዮን ደሴት)

ከላይ በቀረበው ተረክ ሀይቁ እንዴት ሴት የልጇን ለቅሶ ቅድሚያ በመስጠት የከፈተችውን ውሃ ሳትዘጋ በመሄዱ ውሃው ስለፈሰሰ በአካባቢው ላይ ሐይቅ ሊመሰረት መቻሉ ተነግሯል። የማህበረሰቡም አባላት 1620 ሜርት ከባህር ጠለል በላይ የሚሆነው የዝዋይ ሀይቅ የተፈጠረው በዚህ መንገድ ነው ብለው ያምናሉ።

በተረኩ ውስጥ ሀይቁ ሊፈጠር ችሏል ተብሎ የቀረበው ሀሳብ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሲታይ እውነትነት ያለው ባይሆንም የሀይቁን ኬት መጣነት በሚመለከት ለሚነሳባቸው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ይጠቅማቸዋል። በአንድ ምክንያት ጥፋት ከመከሰቱ በፊት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባውን ነገር ቅድሚያ በመስጠት ከጥፋት መዳን እንደሚያስፈልግ ለማስተማርም እገዛ ሊያደርግላቸው ይችላል። እንዲሁም የማህበረሰቡ አባላት ስርአት አለማክበር ሊያስከትል ከሚችል ጉዳት እንዲጠበቁ የሚያስተምሩበት ነው ማለት ይቻላል።

### 4.3.2. የዝዋይ ሐይቅ ቅድስና

የዛይ ማሕበረሰብ አባላት በተረኮቻቸው አማካኝነት በዙሪያቸው የከበባቸውን ሐይቅ ቅዱስ ነው ብለው ያምናሉ። ቅድስናውንም ክርስቶስ ሲሰቀል በመስቀል ላይ ካፈሰሰው ደም ጋር በማገናኘት ይናገራሉ። «ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ አይሁዶች ጐኑን ይወጉት ነበር። ኡራኤል የተባለ መልአክ ደሙ መሬት እንዳይንጠባጠብ በዋንጫ ይቀበለው ነበር። ደሙን የተቀበለበት ዋንጫ የተለቀለቀው በዚህ ሐይቅ ነው።»
(መምሬ ዘርአጽዮን ሀብተማርያም፣ መጋቢት 27 ቀን 2004 ዓ.ም ፣ ደብረ ጽዮን)

በተመሳሳይም መምሬ መላኩ በተረክ አርባ ላይ «ጌታችንን አይሁዶች በሰቀሉት ጊዜ መላእክት የአለም መድሀኒት ነው ብለው ደሙ መሬት እንዳይፈስ በፅዋ ተቀብለው ደሙን በአለም ላይ ሲያፈሱ ደሙን የተቀበሉበትን ፅዋ እዚህ ዝዋይ ባህር ላይ መላእክት አጥበውበታል።» በማለት ይተርካሉ።

ከተረኩ እንደምንረዳው የዝዋይ ሐይቅ ላይ የእየሱስ ክርስቶስ ደም ማረፉን ወይም ውሃው የክርስቶስን ደም መንካቱን ነው። ተረኩ በድርሳነ ኡራኤል ላይ ከቀረበው ታሪክ ጋር ተዛምዶ ያለው ነው። ይህም ቅዱስ ኡራኤል በተለያዩ አካባቢዎች ላይ ሲዘዋወር ከቆየ በኋላ ወደ ዝዋይ ሀይቅ በመምጣት ከሐይቁ ውሃ ቀድቶ በአንድ ክንፉ ከያዘው ከእየሱስ ክርስቶስ ደም ጋር ቀላቅሎ ከከንባታ እስከ አናሪያ አረብ ወሰን ድረስ መርጨቱን የሚተርክ ነው (ዓ.ም ያልተጠቀሰ፣ 24)

ተረኩ ከየትኞቹም ሐይቆች የዝዋይ ሐይቅ የተለየና ቅዱስ እንደሆነ፣ በዚህም ልዩና ቅዱስ ስፍራ ላይ የምንኖር ነን የሚል ነው። ከዚህ ሌላ ሀይቁ የክርስቶስ ደም የተቀላቀለበት ነው ተብሎ መተረኩ የክርስቶስ ደም ባረፈበት ሀይቅ ዙሪያ የምንኖር በመሆናችን ከሚመጣው መቅሰፍት እንድናለን ብለው እንዲያምኑ ታስቦ የቀረበ ይሆናል። እንዲሁም የማህበረሰቡ አባላት በአካባቢያቸው ያለውን የሀይቅ ውሃ ሳይጠራጠሩና ሳይጸየፉ እንዲጠቀሙበት ለማድረግ እገዛ ያደርግላቸዋል።

ይህን ጥናት ለማድረግ ወደ አካባቢው በተጓዝኩበት ጊዜም ከ1፡30 እስከ 2፡00 ሰአት በፊጀው የሀይቅ ላይ ጉዞዬ የሞተር ጀልባ ላይ የተሳፈሩ የማሕበረሰቡ አባላት ከሐይቁ ላይ በጠርሙስ ውሃ እየቀዱ ሲጠጡ ተመልክቻለሁ። የሀይቁን ውሃ ያለምንም ጥርጣሬ ሲጠጡ የተመለከትኳቸውን የማህበረሰቡ አባላት ስለ ሀይቁ በጠየኳቸው ጊዜ የሰጡኝ ምላሽ የሀይቁ ውሃ ከምንም ነገር የጸዳና ለጉዳት የማይዳርግ በመሆኑ አዘውትረው ለመጠጥነት እንደሚጠቀሙበት ነው።

የማህበረሰቡ አባላት በሚኖሩበት ደሴት ላይ ለመጠጥነት እንዲያገለግል ታስቦ የተተከለ የውሃ ቧንቧ ቢኖርም ከቦታው አንጻር ውሃው ሙቅ በመሆኑ የተነሳ ለመጠጥነት እንደማይጠቀሙበት፣ ከተጠቀሙበትም ውሃውን መሬት ላይ ቀብሮ በማቀዝቀዝ ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ፣ አዘውትረው ግን የሀይቁ ውሃ ምንም ጉዳት ስለማያስከትል ሊጠጡት እንደሚችሉ በተለይ መረጃ አቀባዬ አቶ እንዳለ ከፈኔ ነግረውኛል። ተረኩም በደሴቱ ላይ ለሚኖሩ የዛይ ማህበረሰብ አባላት ያለው ፋይዳ ምንድ ነው የሚለውን መመልከት የሚቻል ይመስለኛል። በሌላ በኩልም የማህበረሰቡ ኑሮ የተመሰረተው በእሳ ማስገር በመሆኑና ከደሴቱ ወጥተው ወደ ሌሎች ቦታዎች የሚሄዱት ይህንኑ ሀይቅ ተሻግረው ስለሆነ እንደልባቸው በሀይቁ ላይ ለመንቀሳቀስ እንዲችሉ በማሰብ ሀይቁ ፍጹም ቅድስና ሰላማዊ ነው የሚል ሀሳብ ለማጽናት ጠቅሟቸዋል። እንዲሁም ሀይቁ ፍጹም ቅድስና

ያለውና ለጉዳት የማይዳርግ ነው ብለው አምነው እንዲቀበሉና በሀይቁም ላይ የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ አግዟቸዋል።



አቶ ነገዎ ሸጎሮ በትረካ ላይ( መጋቢት 18 ቀን 2004 ዓ.ም)

## 4.3.3 የዝዋይ ሀይቅና «ባእድ አምልኮ»

የዛይ ማሕበረሰብ አባላት የሐይቁን ቅድስና በሚመለከት ከሚተርኳቸው ተረኮች መካከል ሌላው እንዳለ ከፋኔ በተረክ አርባ ሁለት ላይ የገለፀው ነው።

> እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የሰጣቸው ቦታዎች አሉ። ይህ ውሃ ምንም አይነት ጉዳት እንዳያመጣ ቃል ኪዳን ስላለው አይተናኮልም። የሞተር ጀልባ በሌለበት ጊዜ እንኳ የታመመ ሰው ተሸክመን በጀልባ እየቀዘፍን በውሃ ውስጥ ስንሄድ ምንም አልሆንም። ቃል ኪዳን የሌለባቸው ቦታዎች ለባእድ አምልኮ ይጋለጣሉ። ይህ ቦታ ግን ከእንደዛ አይነት ነገር የፀዳ ነው። ሰዎች ሊያመልኩበት ቢፈልጉ እንኳ መልሶ እራሳቸውን ያጠፋቸዋል። አንድ ቀን አንዱ ፈረንጅ ዶሮ ይዞ እውስጡ አስቀምጦ ሊወጣ ሲል እዛው ነው ያስቀረው። ሌላ ቦታ ቢሆን ባእድ አምልኮ ያከናውኑበታል። እዚህ ውሃ ውስጥ የሚተናኮል አውሬ የለም። ውሃው ሲጠጣ አያሳምም ከሁሉም ነገር የፀዳ ነው። (መጋቢት 23 ቀን 2004 ዓ.ም፣ ደብረ ጽዮን ደሴት)

ከተረኩ እንደምንረዳው በሐይቁ ላይ "ባእድ አምልኮ" ለማከናወን የመጣ የውጭ ዜጋ ይዞ ከመጣው ዶሮ ጋር እዛው ሀይቁ ውስጥ ሊሞት መቻሉን ነው። እንዲሁም በሀይቁ ውስጥ የሚተናኮል አውሬ እንደሌለና የሀይቁን ውሃ ለመጠጥንት ቢቀጠሙበት ምንም አይነት ጉዳት እንደማያደርስ ነው።

በተረኩ በሐይቁ ላይ ባእድ አምልኮ ለማከናወን መጥቶ እዛው መቅረቱ የተገለጸው ፈረንጅ መሆኑ ተጠቅሷል። ለምን ኢትዮጵያዊ ባእድ አምልኮ ሊያከናውን መጣ አልተባለም? የሚለውን ሀሳብ በመያዝ የተረኩን ይዘት ስንመለከተው አንድም በሃይቁ አካባቢ ያሉትን የማህበረሰብ ክፍሎች እንኳን እናንተ እና ከውጭ አገር ድረስ "ባእድ አምልኮ" ለማከናወን ወደ ሃይቁ የሚመጣ ሰው ሃይቁ ቅዱስና ለ"ባእድ አምልኮ" የማይመች በመሆኑ እንዲሁም ከሌሎች ሃይቆች ተለይቶ ቃል ኪዳን የተሰጠው ስለሆነ ሀሳቡን ከግብ ሳያደርስ ሊሞት ችሏል፤ ስለዚህ ማንም ሰው ቢሆን በሃይቁ ላይ እንዲህ ያለ ተግባር ከመፈጸም ቢሞክር እጣ ፈንታው ሞት ነው የሚል ይመስላል። ከዚህ በመነሳትም ሐይቁ ላይ ምንም አይነት "ባእድ አምልኮ" እንዳይካሄድ ለመቆጣጠር የሚጠቀሙበት ነው ማለት ይቻላል።

ከዝዋይ ሀይቅ ጋር ተያይዘው ከሚተረኩት ተረኮች ይዘት መረዳት የሚቻለው የዝዋይ ሀይቅ ጥንት እንዳልነበረና በአንዲት ሴት ቸልተኝነት ምክንያት ሀይቁ ሊፈጠር መቻሉን አምነው እንደሚኖሩ ነው። በሀይቁ ላይ የክርስቶስን ደም የያዘው ዋንጫ ተለቅልቆበታል የሚል እምነት እንዳላቸውና ሀይቁ ምንም አይነት ጉዳት አያደርስም ብለው ስለሚያምኑም በሀይቁ ላይ ሰላማዊ እንቅስቃሴ እንደሚደርጉ የተረኮቹ ይዘቶች ያሳያሉ። እንዲሁም በሀይቁ ላይ እነሱ "ባእድ አምልኮ" ብለው የሚያምኑት ድርጊት እንዳይፈጸምና ሀይቁ ቅዱስ ነው የሚለውን እምነታቸውን ፀንቶ እንዲቆይ ለማድረግ ተረኮቹ የራሳቸው ሚና አላቸው።

## 4.4. የዝዋይ ደሴትና ቅድስና

ቅዱሳን መካናት ከቦታ ሁሉ ተለይተው እግዚአብሔር በራሱ ወይም በወዳጆቹ እያደረ ታላላቅና ልዩ ልዩ ሥራዎች የሰራባቸው ናቸው (ያረጋል፣1993፡14)። የደብረ ጽዮን ደሴትን አስመልክቶ የዛይ ማህበረሰብ አባላት ቅዱስ ስፍራ ነው የሚል ሀሳብ ለማስረገጥ በየጊዜው በደሴቱ ላይ ተፈፅመዋል ተብለው የሚታመንባቸውን ልዩ ልዩ ተግባራት በቃላዊ ዝርው ተረኮች አማካይነት ያቀርባሉ።

በዚህ ክፍል ትንታኔ የሚሰጥባቸው ተረኮች የቦታውን ቅድስና ለመግለጽ የሚተረኩ ተረኮች ሲሆኑ መካን መውለድ፣ «እርኩስ መንፈስ»ና ፈውስ እንዲሁም የዛይ ደሴትና የአልጋ ቁራኛ ፈውስ የሚል ርእስ ተሰጥቷቸዋል።

### 4.4.1. የመካን መውለድ

በደብረ ጽዮን ደሴት በየአመቱ ጥር 21 ቀን የአስተርዮ ማርያም በአል እንደሚከበርና በዚሁ እለትም ከተለያዩ ቦታዎች ምእመናን እንደሚመጡ መረጃ አቀባዬ መርጌታ ሰምረ ግደይ ነግረውኛል። በእለቱ በደሴቱ ላይ የተለያይ ፈውሶችን ማየት የተለመደ እንደሆነም አያይዘው ተርከውልኛል። መርጌታ ሰምረ ግደይ በተረክ ስምንት ላይ በደሴቱ ላይ ስለተከናወነ ተግባርና የደሴቱን ቅድስና አስመልክተው እንደሚከተለው ይተርካሉ።

> አንዲት አሜሪካ የምትኖር ሀኪም ነች ልጅ የላትም። በአለም ሁሉ ዞራ ልጅ ልታገኝ አልቻለችም። የሀኪሟ እናት የሚኖሩት አሰላ ነው። ልጃቸውን ከአሜሪካ ስትመጣ ለምን ደብረ ፂዮን አንሳለምም ብለው ለአስተርዮ ማርያም ይዘዋት መጡ ። በኋላም ይህን ደሴት ረግጣ በሄደች በአመቷ ልጅ ልትወልድ ችላለች።
> (መጋቢት 19 ቀን 2004 ዓ.ም፣ ደብረ ጽዮን ደሴት)

ከተረኩ የምንረዳው አሜሪካ አገር የምትኖርና ልጅ ለመውለድ ፈልጋ የተለያዩ አገራትን ዞራ አልሳካ ያላት ሀኪም አሰላ በሚኖሩ እናቷ አማካኝነት ደብረ ፅዮን ደሴትን ረግጣ በመሄዷ አልሳካላት ያለው የልጅ መውለድ ፍላጓቷ መሳካቱን ነው።

በተረኩ ልጅ እንቢ አላት የተባለችው ሴት ኑሮዋ አሜሪካ ነው ተብሎ መገለፁ በኢኮኖሚም ሆነ በቴክኖሎጂ አድጋለች የምትባለዋ አሜሪካ ልትሰጥ የማትችለውን መፍትሔ ደብረ ጽዮን ደሴት ግን ቅዱስ ስፍራ በመሆኑ የሰውን ፍላጐትን በአጭር ጊዜ ሊያሳካ የሚችል ነው የሚል ነው። በሌላ በኩል ደሴቱ በሳይንስ መፍትሄ የማይገኝላቸው ችግሮች ሁሉ መፍትሄ የሚገኝበት፣ በአለም ላይ ከሚታወቁ ቅዱስ ቦታዎች ሁሉ በቅድስና ብልጫ ያለው ነው የሚል ነው።

በሌላ በኩል የማህበረሰቡ አባላት አዳኝ ስፍራ ላይ ነው የምንኖረው ብለው እንዲያስቡ፣ የሚኖሩበትንም ስፍራ ቅዱስ ነው ብለው አምነው በመቀበል ስፍራውንም የተለየ አድርገው እንዲመለከቱ ተረኩ እገዛ ያደርግላቸዋል። እንዲሁም ስፍራው ቅድስና

ያለው ስለሆነ ቅድስና ያላቸው ሰዎች ነው የሚኖሩበት፣ ወይም ማህበረሰቡ ቅዱስ በመሆኑ ቦታውም የተቀደሰ ነው የሚል ሀሳብ ለማጽናት የቀረበ ነው ማለት ይቻላል።

ከዚህ ሌላ ልጅ መውለድ ፈልጋ አለመቻሏ የተነገረላት ሴት የህክምና ሙያ ያላት እንደሆነችና በአለም ሁሉ ዞራ ለፈለገችው የመውለድ ፍላጐቷ መፍትሄ ማግኘት አለመቻሏ በተረኩ ተጠቅሷል። ደብረ ጽዮን ደሴት በአለማዊ እውቀታቸው ለሰው ልጅ መፍትሄ ይሰጣሉ ተብለው የሚታሰቡት የህክምና ባለሙያዎች ሳይቀሩ መፍትሄ የሚያገኙበት ቦታ ነው የሚል ይዘት ያለው ነው። እንዲሁም የልጅ ፍላጎት ኖሯቸው መካን የሆኑ ሰዎችን ወደ ደሴቱ ለመሳብ የሚጠቀሙበትና ደሴቱ ልጅ መውለድ ፈልገው አልሳካ ያላቸው ሰዎችን ፍላጎት ሊያሟላ ይችላል የሚል ሀሳብ ለመትከል የቀረበ ነው ማለት ይቻላል።

## 4.4.2. «እርኩስ መንፈስ»ና ፈውስ

የማህበረሰቡ አባላት የሚኖሩበትን ደሴት አስመልክተው ከሚተርኳቸው ተረኮች ውስጥ ሌላኛው ቦታው እርኩስ መንፈስ እንደሚፈወስበት የሚናገር ነው።

> አንድ ሴት አስተርዮ ማርያምን ለማክበር እዚህ ደሴት መጣች። ሴትየዋ ገና ደሴቱ ውስጥ ስትገባ መጮህ ጀመረች። የበአሉ እለት አብረዋት የመጡ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን ወሰዷት። እዛም እንዲሁ እየወደቀች እየተነሳች ትጮህ ነበር። ታቦቱ ወጥቶ ንግሱ ሲያልቅ ማንም ሰው በመስቀል ሳይነካና ፀበል ሳይረጫት ብዙ ከጮኸች በኋላ ሰባት ጊዜ አጓርታት ልትድን ችላለች።
> (ወ/ሮ ብርዝነሽ ከፈኔ፣ ተረክ አርባ አራት፣መጋቢት 16 ቀን 2004 ዓ.ም፣ ደብረ ጽዮን ደሴት)

ከተረኩ እንደምንገነዘበው በ«እርኩስ መንፈስ» የምትሰቃይ ሴት ገና ደብረ ፅዮን ደሴት እግሯ ሲረግጥ መጮህ እንደጀመረችና ከብዙ መጮህ በኋላም ያለምንም መንፈሳዊ አገልግሎት መዳን መቻሏን ነው። የማህበረሰቡ አባላት ደብረ ጽዮን ደሴት ቅዱስና ፈውስ የሚገኝበት ነው ብለው እንደሚያምኑ ከተረኩ መገንዘብ ይቻላል።

የማህበረሰቡ አባላት የሚኖሩበት ደሴት «እርኩስ መንፈስ» የሚወገድበት ነው፤ የማህበረሰቡ አባላት የሚኖሩበት ደሴት «እርኩስ መንፈስ» ያላባቸው ከደሴቱ ውጭ ካሉ ቦታዎች ይመጣሉ እንጂ በደሴቱ ውስጥ የሚኖሩት የማህበረሰቡ አባላት ግን ቅዱስ ስፍራ ላይ የሚኖሩ በመሆናቸው "እርኩስ መንፈስ" አይጠናወታቸውም የሚል ይዘት ያለው ነው ። እንዲሁም

ቦታው አዳኝ ስለሆነ በ"እርኩስ መንፈስ" የሚሰቃይ ሰው ወደ ደሴቱ ቢመጣ በቀላሉ ይድናል ለማለት የቀረበ ነው።

በሌላ በኩል ስፍራው አዳኝ ነው የሚል ሀሳብ ለመትከልና ደሴቱን በመርገጥ ብቻ ድነት ይገኛል የሚል ሀሳብ ለማጽናት የቀረበ ነው ። እንዲሁም የቦታው ቅድስና የመስቀል ሃይልንና የጸበልን ጉልበት የተካ ነው የሚል ይዘት ያለው ነው። የማህበረሰቡ አባላትም በቅዱስ ስፍራ ላይ ነው የምንኖረው ብለው እንዲያስቡና ለደሴቱም የተለየ ፍቅር እንዲኖራቸው እገዛ ያደርግላቸዋል።

## 4.4.3. ደብረ ጽዮን ደሴትና የአል ጋ ቁራኛ ፈውስ

ሌላው የማህበረሰቡ አባላት የደብረ ፅዮን ደሴት ድነት የሚገኝበት ስፍራ ነው በማለት ወ/ሮ ብሪቱ ደሜ በተረክ አርባ አምስት ላይ ይገልፃሉ። «የአስተርዮ ማርያም ሲከበር ብዙ እስላሞች እዚህ ደሴት ይመጣሉ። አንድ እስላም በጣም ታሞ በአል ጋ ተሸክመውት መጡ በደሴቱም ለሶስት ቀን ከቆየ በኋላ ከበሽታው ድኖ አልጋውን ተሸክሞ ሄዷል።» (መጋቢት 20 ቀን 2004 ዓ.ም፣ ደብረ ጽዮን ደሴት)

ይህ ተረክ በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ እየሱስ ክርስቶስ በአል ጋ የተኛ ሽባን ተነስተህ አል ጋህን ተሸክመህ ሂድ (ማቴ፣ 9፣ 1-10) ብሎ መፈወሱን ከሚናገረው ታሪክ ጋር ቅርርብ አለው። ልዩነቱ በማቴዎስ ወንጌል የተገለፀውን የማዳን ተግባር ያከናወነው እራሱ ክርስቶስ በአካል ተገኝቶ ሲሆን በተረኩ ውስጥ ግን በሽተኛው ተፈወሰ ተብሎ የተገለጸው ደብረ ፂዮን ደሴት ላይ ለሶስት ቀናት በመቆየቱ ነው።

በተረኩ ፈውስ አግኝቶ አልጋውን ተሸክሞ ሄደ የተባለው የእስልምና እምነት ተከታይ መሆኑ ተጠቅሷል። የተረኩም ይዘት የምንኖርበት ደሴት ቅድስና ያለው ነው፤ ከኃይማኖቱ ውጭ ያሉትን ሁሉ ሊያድናቸው ይችላል፣ እንዲሁም የሌላ እምነት ተከታዮች ስለ ደሴቱ አዳኝነት እውቅና ሰጥተውታል የሚል ነው። ተረኩ የማህበረሰቡ አባላት ፈውስ የሚገኝበት ቦታ ላይ ነው የምንኖረው ብለው እንዲያስቡና የመንፈስ እርካታ እንዲያገኙ አገዛ ያደርግላቸዋል።

በሌላ በኩል መረጃ አቀባዮቹ በደሴቱ ላይ የሚኖሩት ዛዮች ከሙስሊሞች ጋር ምንም አይነት ማህበራዊ ግንኙነት እንደሌላቸውና ማንኛውም የማህበረሰቡ አባል በተለይ

ከሙስሊም ማህበረሰብ ጋር ጋብቻ እንደማይፈጽም ነግረውኛል። በመሆኑም ተረኩ የእስልምና እምነት ተከታዮችን ቀልብ ለመሳብና የእኛ አምላክ እናንተንም ይወዳችኋል፤ እኛም እንወዳችኋለን በማለት ሰላም ለመፍጠር እገዛ ያደርግላቸዋል። እንዲሁም የእናንተ አምላክ ያላዳነውን በሽተኛ የእኛ አምላክ ያድናልና ወደእኛ ተቀላቀሉ የሚል ይመስላል። በተጨማሪም የደሴቱን አዳኝነት በመግለጽ እምነታቸውን ለማስፋፋት ያግዛቸዋል።

ከላይ የቀረቡት ከቦታው ቅድስና ጋር ተያይዘው የሚተረኩት ተረኮች ይዘታቸው ሲታይ ተረክ ስምንት መውለድ ሳትችል ቀርታ ደብረ ፂዮን ደሴት በመምጣቷ መውለድ ስለቻለች ሴት የሚናገር ሲሆን ተረክ አርባ ሶስት በእርኩስ መንፈስ ስትሰቃይ የነበረች ሴት በደሴቱ ላይ በመገኘቷ ከበሽታዋ እንደተፈወሰች የሚተርክ ነው። ተረክ አርባ አራት ደግሞ በአልጋ ተሸክመውት መጥተው በደሴቱ ላይ ለሶስት ቀናት በመቆየቱ ድኅነት አግኝቶ አልጋውን ተሸክሞ ስለሄደ ሙስሊም የሚያወራ ነው። የማህበረሰቡ አባላት ደሴቱ ቅዱስ፣ አዳኝና መካን ሊወልድበት የሚችል እንዲሁም ማንኛውም ሰው በደሴቱ ላይ ፈውስ ያገኛል የሚል እምነት እንዳላቸው የተረኮቹ ይዘቶች ያሳያሉ።

## 4.5. ስነ ምግባርና የዛይ ማህበረሰብ

በዚህ ርእስ ስር የዛይ ማህበረሰቡ አባላት ትእዛዝ ካለማክበርና ከትእቢት ወይም ፈጣሪን ካለማወቅ የተነሳ ሊመጡ ይችላሉ የሚሏቸውን ችግሮች አስመልክተው የሚተርኳቸው ተረኮች ትንታኔ ይሰጥባቸዋል።

### 4.5.1. ትእዛዝ አለማክበር

የማህበረሰቡ አባላት በደሴቱ ውስጥ ቀደም ሲል ፍየል፣ በግና አህያ ብቻ ይገኙ እንደነበር ይናገራሉ። ጦጣና ከርከሮ ግን እንዳልነበሩና እንዴት ወደ ደሴቱ ሊገቡ እንደቻሉ መርጌታ ሰምረ ግደይ በተረክ ሰላሳ ሰባት ላይ

> ቀደም ሲል የነበሩት የቤክርስቲያን አስተዳደር አቡነ ሉቃስ በወይዘሮ ተራራ ላይ እያሉ ወይን ተክለው ነበር። ወይኑም በደረሰ ጊዜ በየቤቱ አንዳንድ ዘለላ ይሰጡ ነበር። በኋላ ላይ ግን ህዝቡ ፍየሎቹን እየለቀቀ ፍየሎቹም ወይኑን እየበሉ ሲያስቸግሩ አቡነ ሉቃስ ፍየሎቻችሁን እሰሩ ቢሉም የሚሰማቸው ሰው ስላልነበር በአገራችሁ አውሬ ይደርበት ፍየሎቻችሁን እሰሩ ቢሉም የሚሰማቸው ሰው ስላልነበር በአገራችሁ አውሬ ይደርበት ብለው በመራገማቸው ጦጣና ከርከሮ በደሴቱ ሊገኙ ችለዋል። (መጋቢት 30 ቀን 2004 ዓ.ም ደብረ ጽዮን ደሴት) በማለት ይናገራሉ።

ከተረኩ እንደምንረዳው ቀደም ሲል በደሴቱ ውስጥ ያልነበሩት ጠጣና ከርከሮ የማህበረሰቡ አባላት ምክር አልሰማ በማለታቸው በእርግማን ምክንያት መግባታቸውን ነው። በመሆኑም ተረኩ ትእዛዝ በማክበር ከቁጣ መዳን እንደሚቻልና የማህበረሰቡ አባላትም እርግማን እንዲፈሩ ለማስተማር የቀረበ ነው። ከዚህ ሌላ አዲሱ ትውልድ የቅዱሳንን ቃል በማክበር ከእርግማን እንዲጠበቅ በማድረግ ረገድ የራሱ ሚና አለው።



የቡድን ውይይት እየተካሄደ(መጋቢት 29 ቀን 2005 ዓ.ም፣ ደብረ ጽዮን ደሴት)

## 4.5.2 እግዚአብሔርን መፍራትና ከቁጣ መዳን

የዛይ ማህበረሰብ አባላት ወደ ደሴቱ ከመግባታቸው በፊት ብሩክና ሎጥ የሚባሉ ወንድማማቾችና በወቅቱ ደሴቱን ሲያስተዳድር ነበር ስለሚሉት ፈርኦ አቶ ኡርጌሳ ፉሮ በተረክ ሰላሳ ስምንት ላይ እንደሚከተው ይተርካሉ።

> ብሩክና ሎጥ የሚባሉ በፈርኦ አስተዳደር ጊዜ የነበሩ ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ። እነዚህ ወንድማማቾች ፈርኦ በእኔ እመኑ፣ ለእኔም ስገዱ በሚልበት ጊዜ እነሱ ግን በአፋቸው እሱን እሺ እያሉ በልባቸው ደግሞ እሱንስ ከደው እግዚአብሔርን በማምለካቸው በፈርኦ ላይና እሱን በሚያመልኩት ላይ መአት ሲወርድባቸው እነሱ ግን ከመጣው መአት ሊድኑ ችለዋል።
>
> (አቶ ቆፒያ በራርሶ፣ መጋቢት 21 ቀን2004 ዓ.ም)

ተረኩ ፈርኦ የሚባለው አስተዳደር እግዚአብሔርን ንቆ ህዝቡ እንዲሰግድለት ማድረጉንና ለእሱ እንስግድም ብለው እግዝአብሔርን የፈሩት ወንድማማቾች ከቁጣ ሲድኑ ፈርኦ ግን ከነ ተከታዮቹ ማለቁን የሚናገር ነው።

በተረኩ ሁለቱ ወንድማማቾች እግዚአብሔርን በማመናቸው ከሞት ሊድኑ እንደቻሉ መጠቀሱ የማህበረሰቡ አባላት እግዚአብሔርን እንዲፈሩና ለእግዚአብሔር እንዲታመኑ ለማድረግ ታስቦ የቀረበ ነው ማለት ይችላል። እንዲሁም እግዚአብሔርን ያመነ ከሞት መቅሰፍት ሊድን ይችላል የሚል ይዘት ያለው ነው።

በሌላ በኩል በተረኩ ለእኔ ስገዱ በማለቱ በመጣበት መአት በሞት ስለተቀጣው ፈርኦ ተጠቅሷል። ትእቢት የትም አያደርስም፣ ከትእቢት ይልቅ ለእግዚአብሔር መገዛት ያስፈልጋል፣ ትእቢተኞችም መጨረሻቸው ሞት ነው የሚል ሀሳብ ለመትከልና የማህበረሰቡ አባላትም ከትእቢት እንዲጠበቁ ለማድረግ እገዛ ያደርግላቸዋል። በተጨማሪም ትእቢተኛና እግዚአብሔርን የማያከብር መጨረሻው ሞት ነው ብለው እንዲቀበሉና እግዚአብሔርን ብቻ እንዲያመልኩ ለማድረግ ታስቦ የቀረበ ይመስላል። እንዲሁም እግዚአብሔርን ያመነ ከሞት ሊድን ይችላል በሚል የማህበረሰቡ አባላትም ይህን ተግባር በማከናወን መንፈሳዊነትን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ለማድረግ እገዛ ያለው ነው።

ከዚህ ሌላ ትሁትና ከትእቢት የጸዳ ማህበረሰብ ለመፍጠር፣ በማህበረሰቡ ውስጥም ለእግዚአብሔር የማይገዛና አፈንጋጭ ሰው እንዳይወጣ ለማድረግ እንዲሁም በማህበረሰቡ አባላት መካከልም በጉልበት የመበላለጥ ሀሳብ እንዳይኖር የራሱ ድርሻ ይኖረዋል።

በአጠቃላይ ከስነ ምግባር ጋር ተያይዘው የሚተረኩት ተረኮች የቅዱሳን ቃል መደመጥ አለበት፤ የቅዱሳኑ ቃል ባይደመጥ ግን ርግማን ሊመጣ ይችላል ብለው እንሚያምኑና በደሴቱ ላይ የሚገኙትን ጠጣና ከርከሮም የእርግማን ፍሬዎች ናቸው የሚል ይመስላል። እንዲሁም እግዚአብሄርን መፍራት ከሚመጣ መአት ያድናል፣ ትእቢት ግን ለሞት ይዳርጋል የሚል እምነት በማሳደር ማህበረሰቡን በስነ ምግባር እንጸው እንደሚኖሩ ተረኮቹ ያሳያሉ።

## ምእራፍ አምስት

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የዛይ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረክ ላይ የይዘት ትንተና ማድረግ የሚል ዋና አላማ ይዞ የተነሳ ሲሆን ንኡሳን አላማዎቹም ተረኮቹ ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ መመርመር፣ ማህበረሰቡ በተረኮቹ ውስጥ ጥንተ አመጣጡን፣ ሀይቁንና ደሴቱን እንዴት እንደሚገልጽ ማሳየት፣ በተረኮቹ ውስጥ የሚተላለፉ ጉዳዮችን መተንተን እንዲሁም ማህበረሰቡ ተረኮቹን ለቀጣዩ ትውልድ የሚያስተላልፍበት ምክንያትን መፈተሽ የሚሉ ናቸው።

ዋናና ንኡሳን አላማዎቹን ከግብ ለማድረስ ከርእሰ ጉዳዩ ጋር የሚዛመዱ የጽሁፍ ሰነዶች፣ ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታና የተተኳሪ ቡድን ውይይት በማድረግ መረጃዎቹ ተሰብስበዋል። በመቅረጸ ድምጽና ማስታወሻ በመያዝ ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች ከርእሰ ጉዳያቸው ጋር ተዛምዶ ያላቸውን የማጣቀሻ ጽሁፎችንና ተግባራዊ አቀራረብን መሰረት በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል።

ተረኮቹ የማህበረሰቡ አባላት ስለ ራሳቸው የሚተርኳቸው ናቸው።ከመረጃው በመነሳት በተሰጠው ትንታኔ መሰረት በማህበረሰቡ የሚነገሩ ዝርው ቃል ተረኮች የማህበረሰቡ ጥንተ አመጣጥን፣ የሀይቁን አፈጣጠርና ቅድስና እንዲሁም የደሴቱን አዳኝነትና ስነ ምግ ባር የመግለጽ ፋይዳ ነበራቸው። የማህበረሰቡ አባላት ሙሉ በሙሉ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች በመሆናቸው ተረኮቻቸውም መንፈሳው ይዘት አላቸው።

ከመረጃዎቹ በመነሳት በተሰጠው ትንታኔ መሰረት የማህበረሰቡ የዘር ሀረግ ያእቆብ እንደሆነና ይህን እምነታቸውን አጠናክረው ለመለገለጽና ሌሎችን ለማሳመን የሹሉዳ ስጋ አለመብላትን በመጽሀፍ ቅዱስ ከተቀመጠው የያእቆብ ታሪክ ጋር አጣምረው እንደሚገለጹ በጥናቱ ተመልክቷል። በዚህም በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ የሚታወቅ ሰው ወገን ነን ብለው አምነው እንዲኖሩና ማንነታቸውንም ለመገንባት ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸውን እንደሚጠቀሙባቸው ጥናቱ ያሳያል።

ሌሎች ተረኮች ደግሞ ማህበረሰቡ ከእስራኤል አገር ከቀዳማዊ ምኒሊክ ጋር በመሆን ታቦተ ጽዮንን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት ከአስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች

የአንዱ ወገን መሆናቸውን የሚገልጹ ሆነው ተገኝተዋል፤ በዚህም ክርስትናን ለመመስረት ቀዳሚ ህዝቦች ነን ብለው እንደሚያሚኑና ቀጣዩ ትውልድም እምነቱን እንዳይቀየር ለማድረግ እንደሚጠቀሙባቸው በጥናቱ ተመልክቷል።

አንዳንዶቹ ተረኮች በደሴቱ ላይ የሰፈሩት ታሪክን ከዮዲት ጦርነት ጋር አጣምረው የሚገልጹባቸውና ታቦተ ጽዮንን ከጥቃት ለማዳን ሲሉ በደሴቱ ላይ ለመስፈር መቻላቸውን የሚያሳዩ ሆነው ተገኝተዋልቷል። እንዲሁም የታቦተ ጽዮን ብቸኛ ባለቤቶች ነን ብለው እንደሚያምኑ ጥናቱ ያመለክታል።

ከታዋቂ ነገስታት ጋር ማለትም ከአጼ ይኩኑ አምላክ፣ ከአጼ ምኒሊክ እንዲሁም ከአጼ ሃይለ ስላሴ ጋር የጠበቀ ቅርበት እንደነበራቸው በዝርው ቃል ተረኮቻቸው ይገልጻሉ። ይህም ማህበረሰቡ የሰለሞን ስርወ መንግስት እንዲያንሰራራ በማድረግና በስርወ መንግስቱ ከሚጠቀሱት ነገስታት ጋር የነበራቸውን ቅርበት እንደሚገልጹባቸው በጥናቱ ተመልክቷል።

ሌሎች ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸው ደግሞ ሀይቁ ጥንት እንዳልነበርና በቸልተኝነት ምክንያት ሊፈጠር መቻሉን፣ በሀይቁ ውሃ የእየሱስ ክርስቶስን ደም የያዘው ዋንጫ መለቅለቁን የሚያሳዩ ሆነው ተገኝተዋል። በዚህም ሀይቁን ከሌሎች ሀይቆች በቅድስና የተለየ እንደሆነ አድርገው ለማሳየት፣ እንዲሁም ሀይቁን ካልተገባ ተግባር ለመጠበቅ እንደሚጠቀሙባቸው ተረጋግጧል።

ደሴቱን አዳኝነት በተመለከተ የሚተረኩት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ደግሞ ደሴቱን ፈውስ የሚገኝበት ስፍራ አድርጎ ለማሳየት፣ የሌሎች እምነት ተከታዮችን ቀልብ ለመሳብና እምነታቸውን ለማስፋፋት እንደሚጠቀሙባቸው ጥናቱ ያሳያል። በዚህም የማህበረሰቡ አባላት የደሴቱን አዳኝነት አምነው እንዲኖሩ ለማድረግ ጠቅሟቸዋል።

ቀሪዎቹ ተረኮች ደግሞ በደሴቱ ላይ የሚገኙት ጠጣና ከርከሮ የእርግማን ፍሬዎች መሆናቸውን፣ እንዲሁም እግዚአብሄርን በመፍራት ከሚመጣው ቁጣ መዳን እንደሚቻል፣ የሚያሳዩ ናቸው። ይህም አዲሱ ትውልድ ከእርግማን እንዲጠበቅ፣ የቅዱሳንን ቃል እንዲያከብር ለማድረግና በማህበረሰቡ ውስጥም አፈንጋጭ እንዳይኖር ለመቆጣጠር እንደሚጠቀሙባቸው በጥናቱ ተመልክቷል።

# ዋቢ ጽሁፎች

## ሀ. የአማርኛ ምንጮች


ሀብተ ማርያም አሰፋ። *የኢትዮድያ ታሪክ ጥያቄዎች እና ባሕሎች*። አዲስ አበባ፥ (ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ) 1986 ዓ.ም።

ሙሉቀን ታሪኩ።(ተርጓሚ)። *የጽላተ ሙሴ እውነተኛ ምስጢር(ከሲና ተራራ እስከ አክሱም ጽዮን*።አዲስ አበባ፤ፋር ኢስት ትሬዲንግ ፣2005 ዓ.ም።

ማንያለው አባተ። «የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው»። በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999።

ምንዳ ገብሬ። «የጌዲኦ ልማዳዊ ሥርዓትና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው»። በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ 2000።

ተስፋዬ ኤዴቶ። *የሃይ ሕዝብ ታሪክ*። አዲስ አበባ፤ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣2000።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ። *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል*። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፣ 1951 ዓ.ም።

አማረ ሞላ። «የሸክቾ ብሔረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና»። በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999።

አባይነህ ካሤ። *የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት(አንደኛ መጽሐፍ)*። አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም።

ከሁሉም በላይ «የነገደ ወይጦ ቃላዊ ዝርው ተረኮች እና ባህላዊ ስርዓቶች»። በኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 2003 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር። *መጽሐፍ ቅዱስ*፡ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980።

የኢትዮድያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን። *ድርሳነ ዑራኤል በግዕዝና በአማርኛ*። አ ዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1991ዓ.ም።

__________። *ገድለ ተክለሃይማኖት*። አዲስ አበባ፤ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም።።

ያረጋል አበጋዝ። *ፍኖተ ቅዱሳን*። አዲስ አበባ፤ (ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ)፣ 1993።

ገብረ ስላሴ ወ/አረጋይ። *ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒሊክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ*። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1959።

ፈቃደ አዘዘ። *የስነ ቃል መምሪያ*። አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጽሐፍት ማዕከል፣ 1991።

## ለ. የእንግሊዝኛ ምንጮች

Abdulkadir Haji Jima. "Some Cultural Elements as Reflected in Somali Folktales." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1982.

Abraham Alemu. "Jimma Oromo Oral Prose Narratives: A Preliminary Desc riptive Analysis." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 2000.

Ambaw Demissie. "The Phonology of Zay: Generative approach." M.A. Thesis, Addis Ababa University, (1990).

Bascom, William R.. The Forms of Folklore: Prose Narrative. In Segal, Robert A. (Ed.) *Anthropology, Folklore and Myth*. New York and London: University of Lancaster, Garland Publishing, 1996.

____________ "The Forms of Folklore: Prose Narrative". The Journal of American Folklore, Vol.78, No.307 (Jan.-Mar., 1965).

Bayileyegn Tasew. "Anyuaa Oral Prose Narratives: Ethnic Genres and Social Functions." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1999.

Ben Amos, Dan. Folktale. In Bauman, Richard (Ed.).*Folklore, Cultural Performance, and Popular Entertainments*. Oxford University Press, New- york,1992.

Cormick, Charlie T. Mc, kim kennedy White. *Folklore: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art*. V.1 (Second dition),2011.

Degh, Linda. "Oral Folklore: Oral Narratives." In Dorson, Richard M. (Ed.) _Folklore and Folk life: An Introduction_. Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Dorson, Richard M. (Ed.) _Folklore and Folk Life: An Introduction_. Chicago: The Univeristy of Chicago Press, 1972.

Endashaw W/michael. "A study of the Ethno linguistic Attitudes of Zay People: An Investigation of the Language Ethnicity Relationship Among Zay". M.A.Thesis, Addis Ababa University, Linguistic Thesis,2007.

Getu Shikur. "Morphology of Zay". M.A. Thesis, Addis Ababa University, (1999).

Goldstin, Keneth. _Guide for field workers in folklore._ Pennsylvania: folklore associates inc, 1964.

Henze, B.Paul. _Lake Zway and its Islands: An Ethiopian Lake where a Unique Christian Culture has Survived since Medieval Times_. Ethiopia Observer Vol. 16 No. 1, Britain and Ethiopia (1973).

Jordan,Linda and Others, _A Sociolingustics Survey of Zay People in Ethiopia_. SIL Electronic Servey Report, November 2011.

Melakneh Mengistu. "The Major Themes and Motifs of Southern Agaw Folktales." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1990.

Monika Fludernik. _An Introduction to Narratology_.Taylor &Francis e-USA & Canada, 2009.

Oring, Elliot. _Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction_: Logan, Utah: Utah University Press, 1986.

Prince Geraled. Narrative Theory. In Mike Bal (ed). _NARRATIVITY_.

New York, 2007.

Sahilu kidane. "Borana Oromo Prose Narratives: A Contextual Study." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1996.

Sergaw Hable sillase. *Ancient and Medieval Ethiopian History to 1970*. Addis Ababa, United printers,1972.

Sims, Martha C. and Martine Stephens. *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Traditions*. Logan, Utah: Utah State University Press, 2005.

Tesfaye Edetto. "Socio-Economic Life of The Zay with Special Emphasis on The Fishing Industry". BA Thesis, Department of History,Addis Ababa University, 1988 .

Tesfaye Gebre Mariyam. "A Study of Major Themes in Jablawi Folktales." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1990.

Tuma Nadamo. "A History of The Zay In The 19th And Early 20th Centuries". B.A. Thesis, Department of History,Addis Ababa University, 1982.

Yihenew Jembere. "A Generic Classification of Amharic Oral Prose Narratives of West Gojjam." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1996.

Zelalem Assefa. "A brief History and activities of Zeway Debere Tsion Monaste." BA Thesis, Trinity Theology College, 2001.

Zerihun Doda. "Culture, Belief & Mental illness among the Zay". M.A Thesis, Department of Sociology and Social Administration, Addis Ababa University, (2001).

# አባሪ አንድ፡- የተረኮች ስብስብ

## ተረክ 1

አፄ ይኩኖ አምላክ የተወለደው በዝዋይ ደሴት ላይ ሲሆን የክርስትና ስሙም ተስፋ እየሱስ ነው። ወደ ኃይቅ እስጢፋኖስ ለትምህርት ሄደ። ተክለሀይማኖት አግኝተውት ከየት እንደመጣ ሲጠይቁት ከዝዋይ ደሴት መምጣቱን ነገራቸው በዚህ ጊዜ ለጥያቄያችን መልስ ተገኘ አሉ። በቃ አንተን መንግስት አደርግሀለው አሉት። ከዚያም ሊያደራርሩት ይዘውት ሄዱና አባቶቻችን ታቦተ ፅዮንን በእግዚአብሔር ኃይል ያመጧትን ያለ መንግስት መቀመጥ የለባትም። ይህች ታቦት እንዳትዘረፍ ማን ይጠብቃታል በማለት እግዚአብሔር ኃይል ይሁንህ ብለው ቀብተው አነገሡት። ከዚያም በኋላ ይኩኑ አምላክ የኢትዮጵያ ንጉስ ሆነ።

## ተረክ 2

አፄ ሚኒሊክ ኢትዮጵያን ሁሉ አንድ አድርገው አልገዛ ያላቸው የደቡቡ ጠና ነበርና ጠናን ተዋግተው ሲመለሱ የዝዋይን ሃይቅ አዩት። ይህ ሃይቅ ምንድን ነው ብለው ሲጠይቁ የዝዋይ ደሴት ነው አሏቸው። አፄ ምኒሊክም ኢትዮጵያን አንድ አድርገን ስንጨርስ ምን ተፈጠረ? ይህንማ ሳላይ አልሄድም ብለው ከነሰራዊታቸው ወደ ደሴቱ ከመጡ በኋላ በምን ይግቡ? ከነሰራዊታቸው እዛው ቆሙ በኋላም እዛ ያለው ህዝብ ሰው አይቶ አያውቅም ነበርና ሊወጋቸው ጠበቃቸው።

ከዚያም አፄ ሚኒሊክ መግባት ስላልቻሉ በቃ ምንም ላደርጋችሁ ሳይሆን ምን አይነት ሰዎች እንደሆናችሁ ልያችሁ በማለታቸው ከአምስቱ ደሲያት አንድ አንድ ሽማግሌ ተውጣጥቶ ከእሳቸው ጋር ተገናኙ። ከዛ ሲገናኙም የአክሱም መንግስት እንደነበሩና በታሪክ ምክንያት እዚህ ደሴት እንደቀሩ ሲሰሙ አፄ ሚኒሊክ አለቀሱ። ለካ እናንተ ለኢትዮጵያ ህዝብ ብላችሁ እዚ ውሃ ውስጥ ቀርታችኋል? ብለው በጣም አዘኑ። ከዛ በኋላ በሉ አሁን ውጭ ወጥታችሁ ስፈሩ። የአገር ታሪክ ለመጠበቅ እስካሁን እዚህ ደሴት ኖራችኋል፤ ከዚህ በኋላ ውሃ ውስጥ መኖር የለባችሁም አሏቸው። አዲስ አበባ ጃንሜዳ እንዲሠፍሩ ተፈቅዶላቸው ነበር። ከዚያም በደሴቱ ውስጥ ያለውን ቤተክርስቲያን እሰራላችኋለሁ ብለው ቃል ገቡ። በኋላም ለእያንዳንዱ የደሴቱ ሰው አንዳንድ ከብት ሰጡ። እስካሁን ድረስ የሚኒሊክ ከብቶች የሚባሉ አሉ። ለእነሱም አካባቢውን እንዲገዛ ስልጣን ሰጡትና ሄዱ። ከዚያም ከመሞታቸው በፊት ዘውዲቱን

«ያን ደሴት እሰራለሁ ብዬ ነበር፤ ስላልሆነልኝ አንቺ ስሪው» አሏት። በኋላም ዘውዲቱ ደብረ ፅዮንን ሰርተዋት ነበር። ከዚያም ለገዳሙ መተዳደሪያ የሚሆን 150 ጋሻ መሬት ከዝዋይ ሃይቅ ጀምሮ እስከ አሰላ ድረስ ርስት ሰጡ። ከዛም ህዝቡ እምነቱን እንዳይቀይር እንዲሁም ስልጣኔውን እንዲቀጥል ከበጌ ምድር አስተማሪ እያመሰጡ ትምህርት ይሰጥ ነበር።

## ተረክ 3

ወደ እዚህ ደሴት ከደብረ ዝቋላ እየመጡ ነበር አባቶች/ካህናት ያገለግሉ የነበሩት። አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከግብፅ ሲገቡ መጀመሪያ የገቡት ዝዋይ ደሴት ነው። አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ መጀመሪያ ገብተው የፀለዩት እዚህ ደሴት ሲሆን ቦታም አባ ዋሻ ይባላል።

## ተረክ 4

ደብረ ፅዮን የላሊበላ መንግስት ሲፋለስ የሰፈረባት ቦታ ነች፤ ሁለተኛ አክሱም ነች። በጣም ጥንታዊ ቦታ ነች፣ ከዚያም ገዳሙ ተስፋፋ፤ ብዙ ርስት ስላለ ብዙ ሊቃውንት እዛ ተቀመጡ። ዝዋይ ገዳምም ታዋቂ ቦታ ሆነ። ሁሉም ዕላት ከዛ ነው የሚወጡት። ለብዙ ገዳማትም አከፋፋይ ሆነ።

## ተረክ 5

አንድ እስላም ተነስቶ ከቤተ ክርስቲያኑ ሰባት ፅላቶችን ሰርቆ እቤቱ ወስዶ ይደብቃቸዋል። ከዚያም የአህዛቡ ቤተሰቦች እንዳሉ ያልቃሉ። በመጨረሻ ላይ ካህናቱን አስጠርቶ ያደረገውን ሁሉ ነግሮ ታቦቱ ሊመለስ ችሏል።

## ተረክ 6

ለጥምቀት በአል እዚህ ደሴት ላይ ታቦቶች ይወጣሉ። ከዚያም ቄሶቹ ታቦት ተሸክመው ምእመናኑ እየጨፈረ ሲከታላቸው በድንገት የአንድ ምዕመን ጋቢ ታቦቱ ነካው። ከዚያም የሰውየው ጋቢ ተቃጠለ። ሰውየው አሁንም ድረስ አለ።

## ተረክ 7

አንዲት አሜሪካ የምትኖር ሀኪም ነች ልጅ የላትም። በእለም ሁሉ ዞራ ልጅ ልታገኝ አልቻለችም። የሀኪሟ እናት የሚኖሩት አሰላ ነው። ልጃቸውን ከአሜሪካ ስትመጣ ለምን ደብረ ጊዮን አንሳለምም ብለው ለአስተርዮ ማርያም ይዘዋት መጡ ። በኋላም ይህን ደሴት ረግጣ በሄደች በአመቷ ልጅ ልትወልድ ችላለች።

## ተረክ 8

እኛ ከሌላው የምንለየው ሃቀኛ እና እምነት ያለን በመሆኑ ነው። እኛ ማንንም ነው የምናምነው የውጭ ሰው ከፉ ነው። አሁን እንግዳ ቢመጣ አልጋዬን ለቅቄ ላሳድረው እችላለሁ። በማመኔም ደግሞ ሊያርደኝ ይችላል። እኛ ሰው እናምናለን። የዛይ ህዝብ ሲወለድም እንደዚህ ነው። እግዚአብሔር ልዩ አድርጎ ነው የፈጠረን። ሰው አሁን ከፉ ያስባል፤ እኛ ግን አናስብም። በኪሳችን ያለውን ሁሉንም ቢወስዱት እኛ ምንም አይመስለንም።

## ተረክ 9

ዛይ ውስጥ ወርቅም ሆነ ገንዘብ ቢጠፋ ለጠፋበት ሰው ይመለስለታል። ይሄ ደግሞ ዝዋይም ይሁን አዲስ አበባ የሚታይ አይደለም። አንድ ልጅ ለንግስ መጥታ ሞባይሏ ጠፍቶባት ተመልሶላታል። አሁን ከዚህ ደሴት ውጭ  የሚመጡ ናቸው እንጂ የሚሰርቁት የኛ ህብረተሰብ ስርቆት አያውቅም። ይሄ ደግሞ ረድኤት ነው። እምነቱ አንድ ስለሆነና የቤተክርስቲያንም ሰው ስለማይሰርቅ ነው። የቤተክርስቲያን ሰው አይሰርቅም ህጋችን ነው።

## ተረክ 10

ከአርሲዎች ጋ የዛይ ሕዝብ ሁልጊዜ ይጣላል። ፀቡም እኛ ክርስቲያን እነሱ እስላም በመሆናቸው ነው። ከመቂ በኩል አንድ ሰው አንነካም፤ እነሱም አይነኩም። ሁላችንም ክርስቲያን ነን። ከአሩሲዎቹ ጋ ግን በጣም እንቃረን ነበር። የእኛ ህዝብ ትንሽ ሆነ እንጂ ይህን ውሃ መጠጣት ከልክለን ነበር። የኛ ህዝብ ሌሊት ሄዶ ረግረግ ውስጥ ተደብቆ ይጠብቃል። እነሱ ከብቶቻቸውን ውሃ ሊያጠጡ ሲመጡ እንወጋቸዋለን። የእኛ ህዝብ ሁሉም አንዳንድ መሳሪያ ነበረው። እነሱ ግን አንድም መሳሪያ አልነበራቸውም። የእነሱ ህዝብ ብዙ ነው፤ ነገር ግን ይሸነፋሉ። የእኛ ሶስት አራት ሆኖ ከወጣ ሳይገድል

አይገባም። እነሱ ደግሞ በክህደት ይገድሉን ነበር። ዘመድ ነን ብለው ጠርተው አታለው ይገድሉናል።

## ተረክ 11

በዚህ ደሴት ላይ እቃ ቢጠፋ የማነው ተብሎ ይሰጣል እንጂ ያገኘው ሰው አይወስድም። ለምን 20 ሺ. ብር አይሆንም ቤተክርስቲያን ተኪዶ የማነው ተብሎ ይሰጣል። የዛይ ህዝብ ከዚህ ደሴት ውጭ እንኳ ቢሄድ ታማኝ ነው። አሁን ወጣቶቹ ለትምህርት ወደ ሌሎች ቦታዎች ሄደዋል። የሄዱበት ቦታም ታማኝ ናቸው። የሚሰረቀው የላቂ እንጂ የእኛ ሰው የሌሎችን አይሰርቅም። እንደውም የዛይ ህዝብ ከተማ ወጥቶ ስራ ልቀጠር ቢል ዋስ አምጣ አይባልም። በጣም ታማኝ ነው።

## ተረክ 12

የዛይ ህዝብ የሚጋባው ከዛይ እንጂ ከሌሎች ጋ አይጋባም። ቢጋባ እንኳ የእኛን ባህል ይዘው ነው የሚኖሩት። የእኛ ባህል በእውነት መፅናት፣ የሰው አይፈልግም። በቃሉ ይፀናል። እንግዳ ያከብራል፣ እኛ ወደ ከተማ ስንሄድ ባህላችንን ጠብቀን ነው።

## ተረክ 13

በዛይ ደሴት እቃም ሆነ ከብት ከጥንት ጀምሮ እደጅ ነው የሚያድረው መጤ የለበትም። ሁሉም ተፋቅሮና ተቻችሎ ነው የሚኖረው። ጋብቻን በሚመለከትም እርስ በራሱ እንጂ ከሌሎች ጋር አይጋባም፣ በተለይ ከኃይማኖቱ ውጭ ከሆኑ ጋር አይጋባም።

## ተረክ 14

እዚህ ደሴት ላይ እቃ ጠፍቶ አይቀርም። ባለፈው ጊዜ ለአስተርዮ ማርያም የመጣ ሰው ፍል ውሃ ታጥቦ ኮትና ሱሪ አስቀምጦ እረስቶ ሄደ። እኔም ያንን አግኝቼ በአመቱ ሲመጣ ቤተክርክስቲያን ላይ ልብስ የጠፋበት ብዬ መለስኩለት።

## ተረክ 15

ዋቂ በዳኔ የሚባል ሰው ነበር። ደሴቱ ትንሽ ነው። ለአበዬዎች እህቱን ዳረ። ከዚያም መሬት ስጡኝ ህዝቤን ላውጣ አላቸው። ከዚያም ሰባት ጋሻ መሬት ባላባቱ ሰጠው። ከዚህ በኋላ አበዬዎቹ በሙሉ ባላባቱን መሬት ሽጧል ብለው ነጥቀው ወሰዱበት። ዋቂን ለመግደልም ፈለጉ። የላቂ ህዝብ ደግሞ በጦር እንደኛና ጀግና ነው። አደን ከወጡ

ላቂዎች ሳይገድሉ አይገቡም፤ አበዬዎቹ ግን ባዷቸውን ይገባሉ። አንድ ቀን ዋቄን አደን ካልመጣህ ይሉታል። ዋቄም ከሰባት ሰዎች ጋር ሆኖ አደን ይወጣል። አበዬዎቹ ግን እነ ዋቄን ለመግደል አንዳንድ ሰው መድበውላቸው ነበር። እነ ዋቄም አደን የወጣችሁት ለአውሬ ሳይሆን ለእኛ ነው ለካ ብለው እነሱን ለመግደል የተመደቡትን ሰዎች አባረሩ። በኋላም ዋቄ በዳኔ ከእኛ ሰው ይሙት እንጂ መግደል የለብንም፤ አትግደሉ ብሎ ከለከለ። ከዛይ ስድስት ሰው ሲሞት ከአበዬዎቹ ግን ሁለት ሰው ብቻ ሞተ። ከዚህ በኋላ ዋቄ አንድ ሽማግሌ ይዞ ጩኸቱን ወደ አዲስ አበባ አነሳ። ሽማግሌው ኃይለኛ ነው፤ ልጁም ሞቶበታል። ሽማግሌው አቤት ጃንሆይ አለ። ጃንሆይ ያኔ ገና ልጅ ነው። ስልጣንም መያዙ ነበር። አንተ በተሾምክበት ጊዜ፣ በአንተ ንጉስነት ጊዜ አሩሲዎች በአንድ ቀን ስድስት ሰው ገደሉብን አንተ እንደሌለህ አደረጉ። መንግስትም የሌለ አስመሰሉ። አደን የወጡ ሰዎች አልቀዋል። ደሜን አውጣልኝ አለ። ጃንሆይም ምንም ጣጣ የለም ብለው ወታደር አዘዙ። ባላባቱን ይዘው አሰሩ። ገዳዮችንም ቶሎ አምጡ አሉ። ለስድስት ሰው ዘጠኝ ሰው አስያዙ። ከዚህ በኋላ ለፍርድ ይቅረቡ ተባለ። በፍርዱ ቀንም ሽማግሌዎች ቀረቡ። ጃንሆይም ሽማግሌውን ለመሰለል የሞተ ሞተ እነኚህን ሰዎች በምህረት እንልቀቃቸው ይላቸዋል። ዋቄ ሲናደድ እኔ ልናገር የመጨረሻ ቀን ስለሆነ እኔ ልናገር ለኔ ልቀቅልኝ አለ። ሽማግሌውም አንተ እንደሌለህ፣ ንጉስ እንደሌለ ይህን ያህል የጨረሱብንን ሰዎች ልቀቁ ትለናለህ? እነዚህን ከመልቀቅ እኛ እዚህ የመጣነውን ሽማግሌዎች ጨርሰን። አንዳቸውም መለቀቅ የለባቸውም። መንግስት እያለ አደን የወጡ ሰዎችን የጨረሱ ሰዎችን መልቀቅ የለብህም አሉት። ትንሽ ቆየና ከአሩሲዎቹ አንዱ ተነስቶ እባካችሁ በስህተት ነው ይህን የሰሩት አለ። ድሮ ፍርድ የሚሰጠው ዛፍ ስር ነበር። የኢትዮጵያ ባላባት በሙሉ ተጠርቶ ተሰብስቧል። እባካችሁ ማሩልኝ አለ የአሩሲዎቹ ሽማግሌ። ጃንሆይም እሺ ጉባኤ ምን ትላለህ አለ። ይሄ ማሩልኝ ይላል ያ ግደሉልኝ ይላል ምን ትላለህ ጉባኤ? አለ። አንዱ ተነስቶ ጃንሆይን አንተ እያለህ ካንተ ፊት ፍርድ አንሰጥም አለው። አንተ ፈርደህ ያልከውን እንስማማለን አለ። ጃንሆይም የላቂው ሽማግሌ ያለው ቃል ትክክለኛ ነው። እኔ እያለሁ፣ መንግስት እያለ አደን ወጥቶ እንደ አውሬ ሰውን መግደል ስህተት ነው። እነዚህ ሰዎች መለቀቅ የለባቸውም አሉ። በየገበያው እያንዳንዳቸው እንዲሰቀሉ አዝዣለሁ አለ። እነኚህ ላቂዎች ደግሞ ይለቀቁ ቢሉ ኖሮ እራሳቸውን እስትላቸው ነበር። እነሱ ግን አወቁ። ማሩልኝ ያለው ሰውዬም ይሰቀል፣ እኔ መኖሬን አላወቀም?

ለምን ምህረት መጥቶ አልጠየቀም? መሬቱ እኔን ለምን አይጠይቀኝም፣ ሰው ከመግደል አለ። ከዚያም ጭብጨባ ተጨበጨበ ዋቂም አሸንፎ ገባ።

## ተረክ 16

አጥቀ ስላሴም ወደ ደሴቱ ከገባ በኋላ ሹመት ስጡኝ አላቸውና እናንተ አንድ ዘለላ ዘንጋዳ፣ እኔ ደግሞ አንድ ፍሬ ዘንጋዳ ይመዝናል ብለን እንወራረድ ያሸነፈ ስልጣን ይያዝ አላቸው። ከዚያም ፍሬው በእግዚአብሔር ፈቃድ መዝኖ ስልጣን ያዘ። በዚህም ተቆጭተው ሊገድሉት ጉማርጌ የሚባል ቦታ ላይ ድግስ ደግሰው ጠሩት። እሱም ላባ በፀጉሩ ላይ ሰክቶ ነበር። ብዙ ከተጨፈረ በኋላ ኩራዟን ሲያጠፉ በፀጉሩ ላይ ያለውን ላባ ከላዩ ላይ አንስቶ አንዱ ላይ ሲያደርግ፣ እሱ ነው ብለው ሲገድሉ ሌላውንም እንዲህ ሲያደርግ ብዙ ሰው አለቀ። ቦታውም ሰው መረጃ ይባላል።

## ተረክ 17

የዛይ ሕዝብ ወደ ደሴቱ የመጣው በዮዲት ጉዲት ጊዜ ነው። በዛ ጊዜ ዮዲት ጉዲት ቤተ ክርስቲያን ታቃጥል ስለነበር አልቻልናትም ብለው ሸሹ። ከሰሜን ተነስተው እንኮበር የሚባል አገር ተቀመጡ ጦርነቱ ከሰሜን ወደ መሐል አገር ሲመጣና ዮዲትም እየደረሰች ነው ሲባል ከሷ ለማምለጥ ሲሉ ወደ ደሴቱ መጡ። ከእንኮበር ተነስተው ብዙ ሕዝብ አስከትለው የመጡት ሦስት ወንድማማቾች ናቸው። መቂ ሲደርሱ አንዱ አቡራ (ሰንጐ) የሚባል ቦታ ቀረ። አንዱ ደግሞ ወደ ጉራጌ አገር ሄደ። እነ አጥቀ ሥላሴ ግን ረግረግ ቆርጠው በረግረጉ ላይ ተቀምጠው በንፋስ እየተገፉ ታቦተ ጽዮንን እንደያዙ ደሴቱ ገቡ። ደሴቱ ውስጥ እንደገቡም መቀመጫቸው የት እንደሆነ ለማረጋገጥ እስቴ ሰበቁ መጀመሪያ ያረፉበት ተራራ ላይ እሳት እምቢ አላቸው ከዚያም ወደሌላኛው ተራራ ላይ ወጥተው እስቴ ሲሰብቁ እሳት አገኙ። መቀመጫችን ይህ ነው ብለው ለ40 አመታት ታቦተ ጽዮንን ይዘው ተቀመጡ።

## ተረክ 18

ከአጥቀ ስላሴ ጋር ከመጡት አንዱ አምሃ ስላሴ የሚባለው ሰንጎ የሚባል ቦታ ላይ ዋሻ ውስጥ ተደብቆ ቀረ። በአካባቢው ያሉ ሰዎችም ዋሻ ውስጥ ሲመለከቱት እዚህ ዋሻ ውስጥ ሰው አለ ይሉና እንዴት አድርገን ነው የምናገኘው በማለት ዘዴ መፍጠር ጀመሩ። በኋላም ምሳ አዘጋጅታ የምትሰጠው የደረሰች ቆንጆ ልጅ ፈለጉ። እሷም ምሳ

እየያዘች ስትሄድ እሱም ምግቡን እየሰጠችው እብረው ይመገቡ ነበር። በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲቀራረቡ በኋላ ልጅቷ አንተ እኮ ብቻህን ከምትኖር ከዚህ ውጣና ትዳር ይዘን ብንኖር ይሻላል ትለዋለች። እሱ ግን ፍርሃት አድሮበት ከዚህ ከወጣሁ ይገሉኛል ይላታል። አይ ግዴልም ከእኔ ጋር ትዳር ከመሰረትክ አይገድሉህም ትለውና ሰው ወዳለበት አውጥታው ባልና ሚስት ሆኑ። እዛ አገር ተዋልደው አሁንም ድረስ የእሱ ወገኖች እዛው አገር አሉ። የአካባቢው ሰው ግን የሚከተለው የእስልምና ኃይማኖትን ነው። እሱም እስልምናን ተከትሎና እነሱን መስሎ ቀረ ይባላል።

## ተረክ 19

ሌላው ከአጥቀ ስላሴ ጋር የመጣው ትእምርተ መስቀል የሚባለው ነው። እሱ ደሞ መቂ ከደረሱ በኋላ ለብቻው ወደ ጉራጌ አገር ሄደ። ጉራጌ አገር ሰባት ወንድማማቾች ነበሩ። ሰባቱ ወንድማማቾች ከሰሜን ተነስተው ወደ ጉራጌ አገር ገቡ። እዛ ሲገቡም ሰባት ቤት ጉራጌ ተባሉ። ጉራጌ አገርም ተራብተው ሲኖሩ ሰባት ቤት ተባለ። የትእምርተ መስቀል ዘር ናቸው።

## ተረክ 20

ዝዋይ የሚለውን ጃንሆይ ናቸው የሰየሙት። አምስቱንም ደሴቶች ጠየቁ ደብረ ፅዮን፣ ፉንድሮ፣ ጠዴቻና ደብረ ሲና ሲሏቸው አምስቱም አጠቃላይ ስም የለውም ወይ አሉ። አምስቱም ዛይ ነው የሚባለው ሲሏቸው እንግዲያውስ ዝዋይ ይባል አሉ።

## ተረክ 21

የዛይ ህዝብ ሹሉዳ አይበላም። ያእቆብ ከመላእክ ጋር ሲታገል ቊኑን ይዞ አደነዘዘው። በዛ ጊዜም አንተ ከእግዚአብሔር ጋር ታግለህ አሸንፈሃል ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል አለው። በዚህ ምክንያት እስራኤላውያን ሹሉዳ አይበሉም። እኛም የእስራኤል ወገኖች በመሆናችን ሹሉዳ አንበላም።

## ተረክ 22

እኛ አክሱማዊያን ነን። አክሱማውያን መሆናችንን የሚታወቀው ደግሞ የአክሱም ቀሳውስት እዚህ ደሴት ለንግስ ሲመጡ ቂጣ ይዘው ይመጣሉ። ከዚያም ያንን ቂጣ ተቀብለን በታቦቱ ስር እንንዘጉዛለን። ቂጣ ለምለም ነው። እኛም ወደ አክሱም

ለንግስ ስንሄድ ከዚህ የአሳ ቋንጣና ጥጥ ይዘንላቸው እንሄዳለን። እንደዚህ እያልን እስካሁን ግንኙነታችን አልተቋረጠም።

## ተረክ 23

የዛይ ማህበረሰብ የመጣው ከእስራኤል ነው። የመጣውም ማክዳ የምትባል ሴት ነበረች። አባቷ አንጋቦስ ነው። አንጋቦስ የተባለውም በደቡብ ክፍል ዘንዶ ስለገደለ እሱንሸሙት ይላል። ማክዳ የምትባለዋ እስላም ነች። አንጋቦስ ሲሞት እጿ ነገሰች ታምሬን የሚባል እስራኤል አገር የሚነግድ አንቺ ዝም ብለሽ ተቀምጠሻልᎢ ኸረ ባክሽን የሰለሞንን ጥበብ ተመልከቹ ብሎ ሲጐተጉታት ህዝብ አስከትላ ከኢትዮጵያ ወርቅ ጭና ወደ ሰለሞን ሄደች። ከዚያም ቤተ መንግስት ከገባች በኋላ ሁሉንም አዙሮ አሳያት። ሰለሞን ፈልጓት ነበርና ጨው የበዛበት ምግብ እንድትመገብ አደረጋት። በኋላም ውሃ እንድትጠጣ መሀላ አስገብቷት ነበር። ይህ ውሃ ከጠጣሽ መሃላሽን አፈረሽ ማለት ነው አላት ካልጠጣሽ ግን እኔም አልፈልግሽም አላት ጨው የበዛበት ምግብ በመብላቷ ውሃ ጥሙ አላስተኛ ሲላት ውሃውን ለመጠጣት ወደ እሱ ክፍል ስትገባ ተገናኛት ከዚያም ትንሽ ቆይቶ ምን አላት በአጋጣሚ እግዚአብሔር ልጅ ከሰጠኝ ብሎ ፎቶ ግራፍ አንስቶ ሰጣት በዛ ጊዜም ንግስት አዜብ ወይም ንግስት ሳባ የተባለችው ከሱ ጋር ከተገናኘች በኋላ ነው። ከዛ በፊት ማክዳ ነው ስሟ። ከሚያም እዚህ/ኢትዮጵያ ስትገባ መፀነሷን ስታውቅ ምን ይለኝ ኢትዮጵያ አለች። ሚኒሊክ የተባለው በኋላ ነው ቀዳማዊ ሚኒሊክን ከወለደች በኋላ እዚህ ያደረገው የሰለሞንን ፎቶ ግራፍ እያየ ነው ሳደቅ የሚባል መምህርት ኦሪት እስራኤል አገር ታቦተ ፅዮንን የሚያጥን ልጁ አዛሪያስ የሚባል ጋ እንደሚኖር ሚኒሊክ ይላካል። እዛም ከ12ቱም ነገደ እስራኤል በሰለሞን ላይ ሰላማዊ ሰልፍ ያደርጋሉ ድንገት አንተ ብትሞት ይህ ኢትዮጵያዊ እስራኤልን ሊገዛ ስለሚችል ወደ እናቱ አገር ወደ ኢትዮጵያ ላከው ይሉታል። እሱም ጥበበኛ ስለሆነ የበኩር ልጃችሁን እናንተ አምጡ አላቸው ቀዳማዊ ሚኒሊክ እዛ ላለመኖር እነሱም የበኩር ልጃቸውን ይሰጣሉ። ሳዱቅል አዛሪያስን ሰጠ። አዛሪያስ ደግሞ ታቦተ ፅዮን ያለችበት ቦታን ያውቃል። በኋላ ታቦተ ሚካኤልን ነገ ይዛችሁ ትሄዳላችሁ ሲባሉ በጠፍ ጨረቃ ገብተው የሚካኤልን ለታቦተ ፅዮን ያለብሱና የታቦተ ፅዮንን ደግሞ ለሚካኤል ያለብሱና ለሊት ጠፍተው አክሱም ይገባሉ። እየሩሳሌም በንፋስ አውታር ስትታመስ ታድራለች። ሳዱቅ ተጠሪ ነውና ሰለሞን ጠርቶት አንተ ዛሬ እኮ እየሩሶሌም በንፋስ አውታር ስትታመስ አደረች። ያችን ፅላት ሰርቀዋት ሄደው ይሆን እንዴ? አለው። ሳዱቅም ሄዶ ሲመለከት ልብሱ

የታቦተ ፅዮን ነው፤ ፅላቱ ግን የሚካኤል ነው።ከዚያ በኋላ አክሱም ገብተው ለረጅም ጊዜ ኖሩ ይባላል።

## ተረክ 24

ዛይ የተባለው ሀሩር ፀሀይ ስለሆነ ትግሬዎች ዝ ዋእይ አሉት። ዝ ዋእይ ማለት የመከራ ቦታ ማለት ነው። ዋእይ ማለት ቃጠሎ፣ ንዳድ ማለት ነው። በመዝሙረ ዳዊት ላይ ደግሞ ዛይ ብሔር ዝኩር እግዚአብሔር። እግዚአብሔር በስራው ሲመሰገን የሚኖር ፈጣሪ ማለት ነው። እነሱ እግዚአብሔር ነግሯቸው ነው ዛይ ያሉት። የእኛ ብሔር ስም የተገኘው ከመፅሀፍ ቅዱስ ነው። ዝዋይ ከተማ ያሉት ስሙን ከእኛ ወስደው ነው። ዝዋይ የተመሰረተው ከእኛ በኋላ ነው።

## ተረክ 25

ኤዴዋቆ የሚባል የዛይ ተወላጅ ነበር። መንግስት ዝመቱ ሲል አማራዎች ይዘምታሉ። ያን ጊዜ በእርስት ነው የሚዘመተው ባላባት ነው የሚዘምተው መንግስት ፀብ ተነስቷልና ዝመቱ ብሎ ትእዛዝ ያስተላልፋል። እነዛን ባለመሬት ሲያዛቸው መንግስት ያዘዛቸው ቦታ ድረስ ይሄዳሉ። እነሱ ሲዘምቱ ኦሮሞዎች ይነሱና የአማራዎችን ንብረት ይዘርፋሉ። እነዛም ድል አድርገው ሲመለሱ ንብረታቸው ተዘርፏል። ማነው የዘረፈው ሲሉ ኦሮሞዎች ይባላሉ። እነሱ እዚህ መንደር ቀርተው ነው እንደዚህ የሚያደርጉት ይሉና አማራዎቹ ተመካክረው ይነሳሉ። እነዚህን እስላሞች እናጥፋ ብለው ከላይ ኦሮሞዎችን እየገደሉና እየዘረፉ በመምጣት እስከ ጉራጌ አገር ሄደዋል። በዛ ጊዜ የዛይ ተወላጅ የሆነው ኤዴዋቆ የሚባለው ከደሴቱ ወጥቶ አማራ ሲያባርራቸው የሸሹትን ኦሮሞዎች ገድሎና አትግደለኝ ማርከኝ ያሉትንም አሳዝነውት ይዟቸው መጥቷል።

## ተረክ 26

የዛይ ህዝብ በሀይቁ ውስጥ ከሚኖሩት የአሣ ዝርያዎች መካከል አምባዛን አይበላም። ምክንያቱም በመፅሀፍ ቅዱስ ከአሣ ዝርያዎች ግልፋፊና ክንፍ የሌለውን አትብሉ ይላል። የዛይ ህዝብም ይህን በመስማት አምባዛን አይበላም። በብዛት ቆሮሶውን ብቻ ነው የሚበላው። ወደ ውጭ እውጥተን ግን እንሸጠዋልን። ምክንያቱም በዚህ ደሴት ላይ ያለው ህዝብ ንፁ ክርስቲያን ስለሆነ የታዘዘውን ያከብራል።

## ተረክ 27

በዚህ ደሴት ማስቀየም የለም፣ መጣላት የለም፣ ሌብነት የለም። ቢጣሉም መደባደብና መጋደል የለም። በርህን ከፍተህ ብትተኛ ሌባ ያጠቃኛል ወይም አውሬ ይበላኛል አትልም። እኛን ከሌላው የሚለየን ይሄ ነው። ቋንቋችንን እንኳ ብትወስድ የተቀላቀለ ነው። ቋንቋችንም እንዲህ እንዲሆን ያመቻቸልን ፈጣሪ ነው።

## ተረክ 28

እዚህ ደሴት ላይ አንድ ገዜ ፈረንጆች መጡ። በደንብ አድርገን አስተናገድናቸው። ከዚያም በሌላ ቀን ተመልሰው ሌሎች ሰዎችን ይዘው መጡ። እኛም ፍየል አርደን በደንብ አስተናገድናቸው። እንዴት ብትሰሩት ነው እንዲህ የሚጣፍጠው ጥብሱ እራሱ የተለየ ሆነብን አሉ። እዚህ የሚሰራውና ከተማ የሚሰራው ጣእሙ ይለያያል። ምክንያቱም የከተማው ወዝ የለውም። እዚህ የሚሰራው ግን በረከትም ወዝም አለው። ምክንያቱም ቦታው የበረከት ነው።

## ተረክ 29

ኃይለስላሴ ወደ እዚህ ደሴት ብዙ ጊዜ ይመጡ ነበር።ምክንያቱም ህዝቡ ታማኝና በእምነቱ የጸና ነው። ህዝቡንና ደሴቱን በጣም ይወዱታል። ህዝቡን ማንም እንዲያጠቃው አይፈልጉም። የዛይን ህዝብ ያጠቃ እንኳ ቢኖር እሳቸው ሞት ነበር የሚፈርዱበት።

## ተረክ 30

እዚህ ደሴት ላይ ቀድሞ ታቦተ እየሱስ ነበር። መምሬ ገ/ማርያም(አቡነ ጴጥሮስ) ያስተማሯቸው ዘጠኝ ቄሶች ነበሩ። እነዚህ ቄሶች ቤተ መቅደስ ሄደው ሲቀድሱ ሚስቶቻቸው ደግሞ ቃልቻ ያመልኩ ነበር። ታቦቱም በዚህ ተቀይሞ ዘጠኙንም ፈጃቸው።

## ተረክ 31

ማርያም በስደቷ ጊዜ ተጨንቃ ወደ ግብፅ በምትሸሽበት ጊዜ ሸማኔ አግኝታ እባክህ መንገድ አሳየኝ ብትለው እሱም ቆይ አንድ ቀሰም ልጨርስ ብሎ ሊያሲዛት ነበር። ከዚያም ባህር ላይ ደርሳ ባለ መርከቡን አሻግረኝ አለችው። ገንዘብ አምጪ አላት።

ገንዘብ የለኝም ስትለው አላሻግርሽም አላት። በዚህ ጊዜ ጢር ከሚባል ቦታ ላይ ሶስት ድንጋዮችን አምጥቶ ህጻኑ ልጇ ክርስቶስ በድንጋዩ ላይ አስቀምጦ አሻግሯታል። ጢር የሚባለው ቦታ ደግሞ እኛ አሁን ቤተክርስቲያን የሰራንበት ቦታ ነው።

## ተረክ 32

የዛይ ህዝብ ስራ ወዳድ ነው። የሚሰራውን ሁሉ ለነገ ብሎ አያስቀምጥም። እንደ ወፍ ሁሉን ለዛሬ ነው የሚያደርገው። ሰፌ እርሻ የለንም፤ ነገር ግን ፈጣሪ አገራችንን ስለባረከልንና ቃል ኪዳን ስለገባልን ሳንቸገር እንኖራለን። ሰፌ እርሻ ካላቸው አገሮች እኛ የበለጠ እንኖራለን። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው።

## ተረክ 33

አቡነ ጴጥሮስ ከዚህ ደሴት ወጥተው ነው አለምን ሁሉ ያዳኑት። በሶስት አምድ የተጻፈውን ገድለ ቅዱሳት የሚገኘው እዚህ ደሴት ላይ ብቻ ነው። ይህን መጽሀፍም አቡነ ጳውሎስ አሜሪካ ወስደው ተሸልመውበታል። ሀይለስላሴ ሰውቤት ህብረት፣ እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ ቻይና ወስደው ተሸልመውበታል። ሌላ መጽሀፍ በአለም ላይ የለም። እዚህ ደሴት ላይ ብቻ ነው የሚገኘው። ይሄ የታሪክና የቃልኪዳን ቦታ ስለሆነ ዮዲትም ግራኝም አልገቡም።

## ተረክ 34

አቡሽሬ የሚባል ሰው ልጁን ሲድር ጠርቶን ሄደን ነበር። ከዚህ ደሴት ላይ ስንሄድ ሰውየው ዛሬ ነው የተወለድኩት፤ የዛሬዋን ቀን መቼም አልረሳትም አለ። ከዛም በቀጥታ ወደ ላንጋኖ ወሰዱን። እኛም ከመኪናችን ሳንወርድ እቃውን አናምነውም፤ ጨርሱና ውጡ አልናቸው። ሰውየውም አብዛኛው ህዝብ የእናንተ ነው አሉን። ጠቅላላ ህዝቡ ለካ ክርስቲያን ነው። ለሙስሊም ለብቻው ነው የተሰራው። በመኪናችን ውስጥ ተቀምጠን የሚጠጣ አምጡልን አልን። አራት ሳጥን ቢራ አመጡልን። ሌሎቹ በ30 መኪና ነው የሄዱት። እኛ ግን 15 ሰዎች ብቻ ሆነን ነው የሄድነው። ከመኪናችን ወርደን ቤት ውስጥ ሳንገባ ጊቢ ውስጥ ብቻ ሆነን እየተዝናናን፣ እየተጫወትን ሌሎቹ ሲያዩን እነዚህ ከፈረንጅ እኩል ናቸው ተባልን። ሰርጉን ሰርግ ያስመሰለው ከዚህ የሄደው ህዝብ ነው። እኛ ባህላችንን ስንጫወት ሌሎቹ የራሳቸውን ትተው ከኛ ጋር ዘለሉ። እንዳጋጣሚ ደግሞ ሌላ የምናውቀው ሰው ልጁን እዛ ይድር ነበር። እነሱም የራሳቸውን ትተው ወደ

እኛ መጥተው ተቀላቀሉ። ላንጋኖ ውስጥ ብቻ ከ40 በላይ ሰርግ ነበር። የሁሉም ተጠሪ ህዝብ ሙሽራውን እየተወ ከእኛ ጋር ይቀላቀል ነበር። የሌሎቹም ሰርግ አይመስልም ነበር። ባህልም ያላቸው አይመስሉም ነበር። ከዚያም የኦሮሞ ልጆች የእኛና የእናንተ ግንኙነት መጠናከር አለበት አሉ። እኛም እሺ ብለናቸው ተለያየን። ሰው እንዲህ ፍቅር መስርቶ መኖር አለበት።

## ተረክ 35

አፄ ሚኒሊክ ለሙግት ይሄዱ ለነበሩ የዛይ ማህበረሰብ አባላት ቤት ይሰጧቸው ነበር። ለሙግት የሚሄዱትም የማህበረሰቡ አባላት የአሳ ቋንጣ በጆንያ ይዘው ይሄዱ ነበር። በዚህ የተነሳም ወደ ምኒሊክ ቤተመንግስት አሣ እንዲገባ ያደረጉት ዛዮች ናቸው።

## ተረክ 36

ደብረ ፅዮን በዝዋይ ደሴቶች ውስጥ ከሚገኙት አንዱና ዋነኛው ነው። ትልቁ ደሴትም ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ታሪክና ቅርስ የሚገኝበት እንዲሁም የሃይማኖታችን መገኛ የሆነና የታሪክ አሻራ ያለበት፣ ንፁህ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ብቻ የሚመለክበት ቦታ ነው።

## ተረክ 37

ቀደም ሲል የነበሩት የቤክርስቲያን አስተዳደር አቡነ ሉቃስ በወይዘሮ ተራራ ላይ እያሉ ወይን ተክለው ነበር። ወይኑም በደረሰ ጊዜ በየቤቱ አንዳንድ ዘለላ ይሰጡ ነበር። በኋላ ላይ ግን ህዝቡ ፍየሎቹን እየለቀቀ ፍየሎቹም ወይኑን እየበሉ ሲያስቸግሩ አቡነ ሉቃስ ፍየሎቻችሁን እሰሩ ቢሉም የሚሰማቸው ሰው ስላልነበር በአገራችሁ አውሬ ይደርበት ብለው በመራገማቸው ጦጣና ከርከሮ በደሴቱ ሊገኙ ችለዋል።

## ተረክ 38

ብሩክና ሎጥ የሚባሉ በፈርኦ አስተዳደር ጊዜ የነበሩ ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ። እነዚህ ወንድማማቾች ፈርኦ በእኔ እመኑ፣ ለእኔም ስገዱ በሚልበት ጊዜ እነሱ ግን በአፋቸው እሱን እሺ እያሉ በልባቸው ደግሞ እሱን ክደው እግዚአብሔርን በማምለካቸው በፈርኦ ላይና እሱን በሚያመልኩት ላይ መአት ሲወርድባቸው እነሱ ግን ከመጣው መአት ሊድኑ ችለዋል።

## ተረክ 39

ድሮ ቦታው ለጥ ያለ ሜዳ ነበር። ቡርቃ የሚባል ቦታ አለ። እዚህ ቦታ ላይ ዙሪያው በቤት ተከቧል። ውሃውን ቀድተው ሲጨርሱ ይከድኑት ነበር። ከውሃው ቤቷ ቅርብ የሆነች ሴት ህፃን አስተኝታ ውሃ ልትቀዳ ወደ ቡርቃው ትሄዳለች ከዚያ በኋላ ውሃውን እየቀዳች እያለች ልጁ በማልቀሱ ውሃውን ሳትከድን ወደ ቤቷ ሄደች። በዚህ ጊዜ ውሃው ገንፍሎ መፍሰስ ጀመረ። አጠገቡ ያሉ የገበሬ ልጆች የሚባሉ ውሃው ፈሰሰልን ብለው ደስ ብሏቸው ጨፈሩ። ከበሮ ይዘው ሲጨፍሩ ውሃው ቀስ በቀስ እግራቸው ላይ ሲደርስ፣ ወገባቸው ላይ ሲደርስ፣ ከዚያም ሙሉ በሙሉ ውሃው ዋጣቸው። ለዚህ ነው የገበሮ ልጆች ሲስቁ ውሃ ወሰዳቸው የሚባለው።

## ተረክ 40

ጌታችንን አይሁዶች በሰቀሉት ጊዜ መላእክት የአለም መድህኒት ነው ብለው ደሙ መሬት እንዳይፈስ በፅዋ ተቀብለው ደሙን በአለም ላይ ሲያፈሱ ደሙን የተቀበሉበትን ፅዋ እዚህ ዝዋይ ባህር ላይ መላእክት አጥበውበታል።

## ተረክ 41

አንድ ሾፌር በቦቴው ነዳጅ ጭኖ ሲሄድ የጫነው ነዳጅ እየፈሰሰ ያልቅበታል። ከዚያም ዝዋይ አካባቢ አቁሞ ሲመለከት ቦቴው ባዶ ሆኖበት ነበር። ከዚያ በኋላ አንድ ሆቴል ይገባና መኝታ ይዞ ትንሽ ከቆየ በኋላ የተደፋበትን ነዳጅ መተካት እንደማይችል ሲያውቅ እራሱን ሊያጠፋ ፈለገ። ከዚያም ቀጥ ብሎ ወደ ሀይቁ መጣ።በወቅቱ ሀዳር 24 ካህናት ሰማይ ይነግስ ነበር። ወደ ሀይቁ ሊገባ ሞከረ። ነገር ግን አልቻለም። አንድ እሱ ብቻ የሚያየትው ሰው ከፊት ከፊት እየመራው ውሃውን በእግሩ እየተራመደ ወደ ደሴቱ ገባ። በዚህ ጊዜ አሳ ያጠምዱ የነበሩ የደሴቱ ሰዎች ምን ተአምር ነው ብለው ከፊሉ ሲሸሽ ከፊሉ ደግሞ ቆሞ ይመለከተው ነበር። ይህ ሰው በደሴቱ ላይ ቆይቶ የሆነውን ሁሉ ተናግሮ ወደ አገሩ ተመልሷል።

## ተረክ 42

እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የሰጣቸው ቦታዎች አሉ። ይህ ውሃ ምንም አይነት ጉዳት እንዳያመጣ ቃል ኪዳን ስላለው አይተናኮልም። የሞተር ጀልባ በሌለበት ጊዜ እንኳ የታመመ ሰው ተሸክመን በጀልባ እየቀዘፍን በውሃ ውስጥ ስንሄድ ምንም አልሆንም። ቃል ኪዳን የሌለባቸው ቦታዎች ለባእድ አምልኮ ይጋለጣሉ። ይህ ቦታ ግን ከእንደዛ

አይነት ነገር የፀዳ ነው። ሰዎች ሊያመልኩበት ቢፈልጉ እንኳ መልሶ እራሳቸውን ያጠፋቸዋል። አንድ ቀን አንዱ ፈረንጅ ዶሮ ይዞ እውስጡ አስቀምጦ ሊወጣ ሲል እዛው ነው ያስቀረው። ሌላ ቦታ ቢሆን ባእድ አምልኮ ያከናውኑበታል። እዚህ ውሃ ውስጥ የሚተናኮል አውሬ የለም። ውሃው ሲጠጣ አያሳምም ከሁሉም ነገር የፀዳ ነው።

## ተረክ 43

ፈርኦ የሚባል ንጉስ ነበር። እንግዲህ መቼም በክፉ መንግስት የተያዘ ህዝብ መጉዳቱ አይቀርም። ህዝቡን ድንጋይ በድንጋይ ላይ እንዲከብ ያዝ ነበር። ህዝቡም የንጉስ ቃል ነውና ያንን ለመፈፀም የማይችለውን ለመሸከም ሲታገል ብዙ ሰው አልቋል። በመጨረሻም ፈርኦ ህዝቡን በድንጋይ ጨርሶታል። እሱ ተሸከሙ ብሎ ያልተሸከመ ይተኮስበትና ይገደላል። ይህንን ያደረገውም ከአምስቱም ደሴት ላይ ልብሱ ታጥቦ ሲሰጣ እንዲታይለት ነው። እንዲሁም ይህ የማን ነው ሲባል የፈርኦ እንዲባልና ስሙን ለመትከል ነው።

## ተረክ 44

አንዲት ሴት አስተርዮ ማርያምን ለማክበር እዚህ ደሴት መጣች። ሴትየዋ ገና ደሴቱ ውስጥ ስትገባ መጮህ ጀመረች። የበአሉ እለት አብረዋት የመጡ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን ወሰዷት። እዛም እንዲሁ እየወደቀች እየተነሳች ትጮህ ነበር። ታቦቱ ወጥቶ ንግሱ ሲያልቅ ማንም ሰው በመስቀል ሳይነካና ፀበል ሳይረጫት ብዙ ከጮኸች በኋላ ሰባት ጊዜ አጓርቷት ልትድን ችላለች።

## ተረክ 45

የአስተርዮ ማርያም ሲከበር ብዙ እስላሞች እዚህ ደሴት ይመጣሉ። አንድ እስላም በጣም ታሞ በአልጋ ተሸክመውት መጡ በደሴቱም ለሶስት ቀን ከቆየ በኋላ ከበሽታው ድኖ አልጋውን ተሸክሞ ሄዷል።

## ተረክ 46

ኢትዮጵያ ከእስራኤል ጋር ተዋለደ የሚባለው ቀዳማዊ ሚኒሊክን ተከትለው ከመጡት ጋር ነው። እንደ ሌላው እኮ አይደለንም መሬትም ጭምር እስራኤል ውስጥ አለን። ለመቀበርም ሆነ ለመቀመጥ እንችላለን። የአፅቀ ስላሴ ዘሮች የመጡት ከእስራኤል ነው።

# አባሪ ሁለት

## 1.የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

### 1.1. ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | ዕድሜ | የትምህርት ደረጃ | መኖሪያ | ስራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መምሬ ገ/መስቀል ሂርጳ | ወ | 68 | የሀይማኖት ትምህርት | ደብረ ጽዮን ደሴት | የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ |
| 2 | መምሬ ዘርአጽዮን ሃ/ማርያም | ወ | 75 | የሀይማኖት ትምህርት | ደብረ ጽዮን ደሴት | ________ |
| 3 | መምሬ መላኩ ገ/ማርያም | ወ | 68 | የሀይማኖት ትምህርት | ደብረ ጽዮን ደሴት | ________ |
| 4 | አቶ ነገዎ ሽጎሮ | ወ | 67 | ያልተማሩ | ደብረ ጽዮን ደሴት | ሽመና |
| 5 | አቶ እንዳለ ከፌኔ | ወ | 47 | ያልተማሩ | ደብረ ጽዮን ደሴት | አሳ ስራ |
| 6 | መርጌታ ሰምረ ግደይ | ወ | 27 | ዲፕሎማ | ደብረ ጽዮን ደሴት | አስተብ'ኒና የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ |
| 7 | አቶ አራርሶ ኦሬሶ | ወ | 50 | ያልተማሩ | ደብረ ጽዮን ደሴት | ሽመና |
| 8 | አቶ ኮፒያ በራርሶ | ወ | 67 | ያልተማሩ | ደብረ ጽዮን ደሴት | የላቸውም |

## 1.2. ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | ዕድሜ | የትምህርት ደረጃ | መኖሪያ | ስራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መምሬ ተላፊኖስ ሚቾ | ወ | 50 | የሀይማኖት ትምህርት | ደብረ ጽዮን ደሴት | ግብርናና አሳ ማስገር |
| 2 | አቶ ኡርጌሳ ፋሮ | ወ | 58 | ያልተማሩ | ደብረ ጽዮን ደሴት | አሳ አስጋሪ |
| 3 | ወ/ሮ ብርዝነሽ ከፊኔ | ሴ | 60 | ያልተማሩ | ደብረ ጽዮን ደሴት | የላቸውም |
| 4 | ወ/ሮ ብሪቱ ደሜ | ወ | 45 | ያልተማሩ | ደብረ ጽዮን ደሴት | ________ |
| 5 | አቶ ሽጉህ ገ/ማርያም | ወ | 91 | ያልተማሩ | ደብረ ጽዮን | የላቸውም |
| 6 | አቶ አብሳ ናዳሞ | ወ | 87 | ያልተማሩ | ደብረ ጽዮን ደሴት | ________ |
| 7 | አቶ ንጉሴ ገብሬ | ወ | 36 | 10ኛ ክፍል | ደብረ ጽዮን ደሴት | ንግድ |
| 8 | አቶ ስሜ ካዮ | ወ | 65 | ያልተማሩ | ደብረ ጽዮን ደሴት | አሳ ማስገር |
| 9 | ዲያቆን ፍሬው አስፋው | ወ | 28 | 12ኛ ክፍል | ደብረ ጽዮን ደሴት | የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ |
| 10 | አቶ በዳሶ ደሜ | ወ | 60 | ያልተማሩ | ደብረ ጽዮን ደሴት | ግብርና |

## 1.3. ተተኳሪ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች


| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | ዕድሜ | የትምህርት ደረጃ | መኖሪያ | ስራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መምሬ ገ/መስቀል ሂርጳ | ወ | 68 | የሀይማኖት ትምህርት | ደብረ ጽዮን ደሴት | የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ |
| 2 | መምሬ መላኩ ገ/ማርያም | ወ | 68 | የሀይማኖት ትምህርት | ደብረ ጽዮን ደሴት | ________ |
| 3 | መምሬ ዘርአጽዮን ሃ/ማርያም | ወ | 75 | የሀይማኖት ትምህርት | ደብረ ጽዮን ደሴት | ________ |
| 4 | መምሬ ተላፊኖስ ሚቾ | ወ | 50 | የሀይማኖት ትምህርት | ደብረ ጽዮን ደሴት | እርሻና አሳ ማስገር |
| 5 | አቶ ነገዎ ሽጎሮ | ወ | 67 | ያልተማሩ | ደብረ ጽዮን ደሴት | ሽመና |
| 6 | አቶ አራርሶ ኦሬሶ | ወ | 50 | ያልተማሩ | ደብረ ጽዮን ደሴት | ________ |

## 1.4. አባሪ ሶስት የፎቶ ግራፍ ዝርዝር





የማህበረሰቡ አባላት በጽዋ ማህበር ላይ





ሰንበቴ ማህበር



ከአቶ በዳሶ ደሜ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ



ታቦተ ጽዮን ለ40 አመታት የተቀመጠችበት ቦታ



መምሬ ዘርአጽዮን ሃ/ማርያም



መምሬ መላኩ ገ/ማርያም



ወ/ሮ ብርዝነሽ ከፋኔ



ወ/ሮ ብርቱ ደሜ



የፊርኦ ድንጋይ